# ምእራፍ ስምንት

"የምፈልገውን እስከማገኝ ድረስ ስቃይህ ሊበዛ ይችላል። ያም ሆኖ ብዙ ልጎዳህ ፍላጎቱ የለኝም" አለው ዘሩባቤል።

"የምትለኝን የምፈጽመው አይመስለኝም። በጭራሽ የማላውቀው ጉዳይ ነው።"

ገብረክርስቶስ የመለሰለት በሲቃ ድምጽ ነበር።

"በፈቃድህ የማትመልስልኝ ከሆነ ሲሰቃዩ ከምደሰትባቸው ሰዎች አንዱ ሆንክ ማለት ነው።" በጥርሶቹ መካከል ሲናገር የማንባሩ ጅማቶች እየተገታተሩ መዘረጋጋት ጀመሩ።

"ቃላቶችህ እንደ መርፌ እየጠለቁ ሲገቡ በፍርሃት ያሽማቅቃሉ። ከአሁን በፊትም አስፈራርተህ ታውቅ ነበር?" በፌዝ ሲመልስለት የበለጠ በሽቀና የሽጉጡን አፈ-ሙዝ ወደ ሽንጡ አስጠጋበት።

"ምርጫህ ከሆነ ላደርገው እገደዳለሁ።"

ስሜቱን ለማጥናት በጨረቃዋ ብርሃን ትኩር ብሎ ዓይኖቹን ተመለከታቸው። ገብረክርስቶስ። .

ወደ ዳር ወጥተዋል። የመለሰለት ቃል እንዳበሳጨው ተረዳው። ትክክል አልነበረም። ይህን ዓይነት መልስ መስጠት ከእብደት የተለየ አይደለም። ተሳስተሃል አለው ራሱን ለራሱ።

"የምትፈልገው ምንድነው?" ሊያረጋጋው ሞከረ።

"ምላጩን ከመሳብ የሚያግደኝ ያለ ይመስልሃል?" በሚሰረስር አኳኋን ተመለከተው ዘሩባቤል።

"ለምንድነው የምታስገድደኝ?" ስሜቱን ለማጥናት እየሞከረ ነበር።

"ትናንት ምሽት የሆኑ ሰዎች በመኪና ከቤትህ መቃረቢያ ድረስ አምጥተውህ ተመልሰዋል። ከዚያ በፊትም ለተወሰኑ ቀናቶች ከቤትህ አልነበርክም።" በሽጉጡ አፈሙዝ ሽንጡን ገፋ አደረገው።

"ድንገት ከኋላዬ ደርሰው ከቤቴ አቅራቢያ ድረስ አድርሰውኛል።" ደም የጐረሰው አፍንጫው ተንተፋተፈ። ደህና ቡጢ ነበር ያቀመሰው።

"በስምምነት አንድ ሥራ ሠርተህላቸዋል" አለ ዘሩባቤል።

"ከሰዎቹ መገናኘቴ ወንጀል ነው እንዴ?" ጠየቀ ገብረክርስቶስ።

"አብረሃቸው ወንጀል ፈጽመሃል።"

"አንደኛው እኮ የውጭ አገር ዜጋ ነው።" አለው ነገሩን ለማምታታት እየሞከረ።

"የውጭ አገር ዜጋ ቢሆንም ወንጀለኛ ነው። የአሜሪካን ዶላርን ጭምር እያስመሰለ በመሥራት የብዙ ሰዎችን ሀብትና ሕይወት ከአደጋ ላይ ሲጥል ቆይቷል። ምናልባትም በሙያህ አንድ ሥራ ሲያሠራህ ቆይቷል።"





እንዳለውም በቀለም የተነከሩ ዶላሮችን በኬሚካል ውስጥ በመክተት አጥቦ ለሚፈለገው ሰው ያሳያል። እነዚህ ታድያ ማስመሰያዎች ናቸው።

"አንተ ምንድን ነህ?" ግራ የተጋባ በሚመስል አመለካከት አስተዋለው።

"የሀገር ውስጥ የጸጥታ ሠራተኛ አባል ነኝ።" ትከሻውን በግራ እጁ ያዝ በማድረግ ጉንበስ ብሎ ተመለከተው።

"ለምን ወደ ሕግ አልወሰድከኝም ታድያ?" ጥያቄው ትክክል ነበር።

"ኃላፊነቱ የራሴ ስለሆነ የትኛውም ስፍራ ላነጋግርህ እንደምችል ልታውቅ ይገባሃል።"

"ለሀገርህ እየሠራህ ያለኸው ብቻህን ነው ማለት ነው?" ሲለው አንድ ቡጢ ደገመው።

"አንተን የሚመለከት አይሆንም። የሚመለከትህ የተጠየቅኸውን በተገቢው ሁኔታ መመለስ ብቻ ነው።"

ወፍራም የጠቆረ ደም ከአፍንጫው ወረደ።

"የበላይ ባለሥልጣኖችን አታምንም ማለት ነው?"

"እሱ አንተን አይመለከትም።" ሲል አፈጠጠበት።

"የምትጠይቀኝን ለመመለስ መተማመኛዬስ ምንድን ነው?"

የሽጉጡን አፈ-ሙዝ ወደ አፉ አቀረበና አሳየው። "ለወንጀለኛ ምንም መተማመኛ የለውም።"

"እንዳልከው ሕይወቴ ያለችው በእጅህ መዳፍ ውስጥ ነው። የሕይወቴ አንድ አራተኛውን አንተ ልትወስነው እንደምትችል ምንም ጥርጥር የለኝም። ምናልባትም እውነት ቢኖረኝ ሕይወቴን እንደማድናት አምናለሁ። ያም ሆኖ ግን..." አቋረጠው።

"እንዳልከው ብትነግረኝ ሕይወትህን አትርፈህ በሰላም መኖር በቻልክ ነበር።"

"ባውቅስ ምን አምኜህ ነው የምነግርህ? ወደ ሕግ ወስደኸኝ ብንነጋገር አይሻልም?"

"የምፈልገውን ከማግኘቴ በፊት ወደ ህግ እንደማልወስድህ ነግሬሃለሁ ከጀርባህ ብዙ ሰዎች ሊኖሩ እንደሚችሉ እጠረጥራለሁ።"

"አለቆችህን ትጠራጠራቸዋልህ ማለት ነው?" የተደነቀ በሚመስል አስተያየት ተመለከተው አንጥረኛው።

"በምሠራው ሁሉ አለቆቼን አማክሬ አላውቅም። ለምን እንደሆነ ታውቃለህ?" በምጸት ዓይነት ሳቅ አለ።

"ለምንድን ነው?" አንጥረኛውም ጠየቀው።

"አላፊነት መሸከም ተስኗቸዋል። የሀገርና የወገንን ጥቅም አሳልፎ መሸጥ በባለሥልጣኖቻችን የተለመደ ሆኗል።"

"ከአሁን በፊት የደረስክበት የወንጀል ክትትል ተቋርጦብህ ነበር ማለት ነው?"

"እንደዚያ ይመስለኛል።" ሲል መለሰለት።

"የተበላሸ አሠራር ስለመኖሩ አልገምትም ነበር።"

በአካሉ ላይ ኃይል እንዲጠቀምበት አልፈለገም። እንደማይለቀው ስለተረዳ በሰላም ሁሉንም ሊነግረው ወሰነና ከስረመሠረቱ ጀምሮ ይናዘዝ ጀመር።

"ፈረንጁን የምታስታውሰው ይመስልሃል።" በዝግታ ጠየቀው።

"አላወቀውም።" ራሱን ጭምር እየነቀነቀ ሊያውቀው እንደማይችል አረጋገጠለት።

"ቼኩን የፈረመልህን ሰው ስም ታውቀዋለህ?"

"ሥራውን ከአሠሩኝ ሰዎች አይደለም የተቀበልኩት። ቼኩ የተፈረመው በሌላ ሰው ነው።"

"ገንዘቡን ከባንክ ስትወስድ ምንም አልተቸገርክም?" አለው።

"ምንም የገጠመኝ ችግር አልነበረውም።"

"ቼኩን ፈርመህ ስትሰጣቸው ተቀብለው ክፍያውን ወዲያው ፈፀሙልህ።"

"ለገንዘብ ከፋዩ እንዳስተላለፍኩለት ከምፒውተር ላይ መዝግቦ እንደ ጨረሰ ብሩን ከፍሎኛል።"

"ቼኩን የፈረመልህ ሰው ለባንኩ ታማኝ ደንበኛ መሆን አለበት። ይህ ባይሆን ኖሮ ሥራ-አስኪያጁ አይቶ ሳያረጋግጥ አይከፍሉህም ነበር።"

"በወቅቱ የተረዳሁት ይህንኑ ነበር። ምንም ማረጋገጫ ሳያስፈልገው ካሸሩ እንደ ከፈለኝ አውቃለሁ።"

"ሂሳቡን የከፈለህ በስንት ቁጥር ላይ የተቀመጠው ገንዘብ ከፋይ ነው?" ዓይኖቹን በመጠኑ ከፈታቸው።

"በአራት ቁጥር ያለው ገንዘብ ከፋይ ይመስለኛል።" አለ ገብረክርስቶስ።

"ሁሉ ነገር እስከ ሚለይ ድረስ የእኔ እስረኛ ሆነህ ትቆያለህ።"

"እንደዚያ ለማድረግ ያስፈለገህ ምንድነው? ለቀቅኸኝ በውጭ ሆኜ ብረዳህ አይሻልም።"

"ይህንን የማደርገው አንተን ባለማመን ብቻ እንዳይመስልህ?። ለሕይወትህ ያለሁህ ብቸኛው መንገድ እኔ በመሆኔ ነው። ካገኙህ በጣጥሰው ይገድሉሃል። እያንዳንዱ እርምጃህን የሚከታተሉ በርካታ ሠራተኞቻቸውን በአንተ ዙሪያ ያሰማራሉ።"

አደጋው ከፊት ለፊቱ የታየው ይመስል ሽምቅቅ አለና መናገር ጀመረ።

"በጉዳዩ ከሚስቴም ጋር መነጋገር እንደሌለብኝ አስጠንቅቀውኛል። ያም ሆኖ እኔን የሚከታተል ሰው ይመድባሉ የሚል ግምት አልነበረኝም።"

"ከዚህ ላይ ነው ትልቅ ስህተት የሰራኸው። ስላልፈለጉ እንጂ ሥራውን አጠናቅቀህ እንደ አስረከብካቸው ሊያስወግዱህ ይችሉ ነበር። ያንን





ባለማድረጋቸው ዕድለኛ ነህ። አሁን ለሕይወትህ የምትሰጋበት ነገር የለም።"

እያንዳንዱን ቃል በነገረው ቁጥር ሰውነቱን ነጭ ላብ እያጠመቀው እንደነበር ተረድቷል። ሙሉ እምነት እንዲጥልበት አለሁህ ሊለው ይገባል። የቸገረው ዱቄት ... እንደ ተባለው ተረት ነው።

ሁሉም ነገር የተዘበራረቀበት መሰለ። እንጥረኛው ወስዶ ከአንድ ነገር ውስጥ ቢጨምረው በወደደም ነበር። ሁሉን ነገር ሲያስበው ልቡ ክፉኛ ተረብሾበታል። ፍርሃት ያቀለጠው ገላው ላብ እያጠመቀው ነው።

"ለጊዜው በአንድ ቦታ እንድትቆይ አደርጋለሁ። ትክክለኛ ቦታህን የምወስነው ከአንተ ጋር በብዙ ጉዳዮች ላይ ከተነጋገርን በኋላ ይሆናል።"

"ሌላ ምክንያት ፈጥረህ ልታስረኝ ትችላለህ እኮ።" የመንፈሱን መሰበር ድምጹ ስላበሰረው መርማሪው ከልቡ አዘነለት። ለገብረክርስቶስ።

"የምትሰጋበት ነገር አይኖርም። የተቻለኝን ሁሉ አደርጋለሁ። ነገሮችን ማየት ያለብህ ከብዙ አቅጣጫ ነው በዚህ ወንጀል ጀርባ የፖሊስ እጅ ስላለመኖሩ ምንም ማረጋገጫ የለኝም።"

"የተቻለውን ሁሉ አብሬህ ለመሥራት እሞክራለሁ።" ሳይታወቀው በእጁ ጉልበቱን ደገፍ አድርጐ ያዘው ምርኮኛው።

"ይህንን ታደርጋለህ የሚል ተስፋ አለኝ።" እሱም በተራው ትከሻውን መታ አደረገው።

"በሙሉ ፈቃደኝነት እንድተባበርህ ሕይወቴን ታደጋት።" በመለማመጥ ቀና ብሎ አስተዋለው እንጥረኛው።

"ሽጉጡን ከቀበቶው ላይ ከተተውና በርከክ ብሎ ተመለከተው።"

"ወዴት ይዘኸኝ ልትሄድ ነው?" ጥያቄው ልዳን እንጂ ጀሃነብም ይሁን የሚል ይመስላል።

"ለተወሰኑ ቀናቶች በኔ ቤት አቆይሃለሁ። በራሴ ቤት ብትቆይ ሳይሻል አይቀርም።"

"አሳልፈህ እንደማትሰጠኝ ተስፋ ልጣልብህ?" አይኖቹን እያስለመለመ ተመለከተው።

"ሳትጠራጠር እመነኝ።" በወዳጅነት ትከሻውን በድጋሚ መታው።

"ሌላ አማራጭ ያለኝ አይመስለኝም። አንተኑ የሙጥኝ ማለት ሳይሻለኝ አይቀርም። እየመጣ ያለው የመከራ ቀን አንተን መማጠን እንዳለብኝ እያሳመነኝ ነው።"

"ቀጣዩ ሁኔታ የረበሸህ ይመስለኛል ብዙ አታስብ። 'ለነገ ክፋቱ ይበቃዋል።'

የጸጥታ ሠራተኛው የተናገረው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ አስገርሞታል። እነዚህ ሰዎች የፈጣሪን ቃል ያውቃሉ ማለት ነው። "ለነገ ክፋቱ ይበቃዋል"። ቃላቶቹን በልቡ ውስጥ በትክክለኛው ለማስቀመጥ እየደጋገመ አነበነባቸው።

"ፍልስፍናህ መልካም ይመስላል::" ቃላቱ ከአፉ የወጡለት በስንት ትግል ነበር።

"የነገርኩህ የክርስቶስን ጥቅስ ነው።" ሳቅ አለ መርማሪው።

"መጽሐፍ ቅዱስ ታነብባለህ እንዴ?"

"ስለ ጎራዴው አሠራር አልነገርከኝም። በሱ ዙሪያ የተወሰነ ማብራሪያ እንድትሰጠኝ እፈልጋለሁ። ስለ መጽሐፍ ቅዱሱ በኋላ እናወራለን።" ትከሻውን በእጁ ተጫነው።

"ምን ዓይነት ማብራሪያ ነው የምትፈልገው?" ሲል ጠየቀው።

"ስለ ሰራኸው ጎራዴ::" ትከሻውን የበለጠ ተጫነው።

"ከእውነተኛው ጎራዴ በምንም አይለይም። ወርቁ እየቀለጠ በተዘጋጀው ሸክላ ውስጥ እንዲረጋ ይደረጋል። የሸክላው ዕቃ የጉራዴውን ቅርጽ ተመሳስሎ የተዘጋጀ ነው። ሸክላው ሲሰበር የጎራዴውን ቅርጽ ይዞ ይወጣል። የኔ የሙያ እገዛ የነበረው ወርቁን አቅልጦ በተዘጋጀው ቅርጽ ማውጫ ሸክላ ላይ ማፍሰስ ሲሆን የአልሙንየሙን የማልበስ ሥራ የተከናወነውም በፈረንጁ ነበር። በስሱ የተቀጠቀጠውን አልሙንየም በሁለት በኩል ከጉራዴው አካል ላይ ሲለጥፈው የእውነተኛውን ጉራዴ ቅርጽና መልክ ይይዛል። በዚህ መልኩ እንደተጠናቀቀም ተሞርዶ ስለት ይኖረዋል። የጎራዴው እጀታም ወርቅ ሲሆን ለመሸፈኛ ያህል ብር የፈሰሰበት ነው።"

"የጎራዴዎቹ ብዛት ስንት ይደርሳል?" አለ ዘሩባቤል

"አሥራ ስድስት ናቸው።"

"ስንት ኪሎ ግራም የሚመዝኑ ይመስልሃል?" ስሜቱን እያጠና ጠየቀው።

"ትኩረቴ የነበረው ሥራውን በማጠናቀቁ ላይ ስለ ነበር ክብደታቸውን እያሰብሁ አልነበረም የምሠራው።"

የተናገረው እውነት እንደ ነበር የተረዳለት ለመሆኑ አንገቱን አወዛወዘ ዘሩባቤል።

"እነዚህ ሁሉ ጎራዴዎች እንዴት በአጭር ጊዜ ውስጥ ተጠናቅቀው ሊሠሩ ቻሉ?" በመገረም ጠየቀው።

"ለኔም ያስገረመኝ ሥራ ነበር።"

"በረጅሙ ተነፈሰ እንጥረኛው።"

"እያንዳንዳቸው ቢያንስ አንድ ኪሎ እንኳን ቢመዝኑ አሥራ ስድስት ኪሎ ግራም ወርቅ ማለት ነው አይደለም እንዴ? አንተ ከነገርከኝ አንድ ኪሎ ያህል በመቀነስ።"

"የማቅለጥ ሥራው ብዙ የሚከብድ አልነበረም።"

ሁለተኛ ፎቅ ላይ ጊዜያዊ የማረፊያ ቦታ አስገብቶት አጠር ያለ ማብራሪያ ሲያደርግለት በትዕግሥት አደመጠው:: እንጥረኛው።

"መኝታህ የተዘጋጀ ስለሆነ ከደከመህ ሻወር ወስደህ ማረፍ





ትችላለህ። የሚያስፈልግህን ጠይቀኝ። መጥራት ስትፈልግ መጥርያውን ተጠቀም። ክፍልህ ሁሉም ነገሩ የተሟላ ነው። ለደኅንነትህ ስል እጆችህንና እግሮችህን ማሰር ይኖርብኛል። በመስኮት ዘለህ ለመውረድ ብትሞክር ከጉዳት ላይ ልትወድቅ ትችላለህ።"

ከወዲያኛው መስመር የመጣው የሴት ድምጽ ጠንከር ያለ እና ጥርት ያለም ነበር። ዜናውን ሊያበስራት ተጣድፎ ነው የደወለው።

"በአንተ እጅ እንዲቆይ ማድረግህ ከተለመደው አሠራር የወጣ ይመስለኛል።"

"ጠዋት ወደ ባንኩ ሥራ አስኪያጅ ሄጄ የሂሳቡን ባለቤት ማንነት መረዳት አለብኝ። ይህንን እስከ ማረጋግጥ እንጥረኛው በኔ እጅ ይቆያል::" ሲል መለሰላት።

"የባንኩን ዋና ሥራ አስኪያጅ ነው የምትጠይቀው?" ለማረጋገጥ ያህል ጠየቀችው።

"እንደዚህ ማድረግ አለብኝ። በትናንትናው ቀን የሃምሳ ሺህ ብር ቼክ የተከፈለው በሁለቱ ሰዎች ስም የተጠቀሰው ሌላ ሰው ላይኖር ስለሚችል በቀላሉ ልደርስበት እችላለሁ የሚል ግምት አለኝ።"

"የማንኛውም የባንኮች ደንበኛ ሰነድ በምሥጢር ነው የሚያዘው። ያለ መንግሥት ትእዛዝ እንደዚህ ያለውን ጥያቄ ሥራ አስኪያጅ የሚቀበል አይመስለኝም::" ሴትየዋ ትክክል እንደ ነበረች ያምናል።

"የፍርድ ቤት ትእዛዝ እንዳወጣ እየነገርሽኝ መሰለኝ።"

"ይመስለኛል::" ደከም ያለች መሰለች።

"የባንኩን ሥራ አስኪያጅ ልጠይቀው እፈልጋለሁ።"

"ፈቃደኛ ሆኖ ባይነግርህስ? ማንኛውም ባንክ የደንበኛውን ምሥጢር ለመጠበቅ የራሱ የሆነ የዲሲፕሊን ደንብ ስላለው መረጃ ሊሰጥህ አይችልም።"

"ጫና ላደርግበት እሞክራለሁ::" አለ ዘሩባቤል።

"ለማንኛውም አዳሬን ላስብበትና መልሱን ልስጥህ። ከደንብ ውጭ እየሠራህ ስለሆነ በትክክል እንድታስብበት እመክርሃለሁ::" ስትል ማስጠንቀቂያ ሰጠችው።

"የባንኩ የምሥጢር ሰነዶች በየትኛው ክፍል እንደሚቀመጡና ሰነዶቹን የሚከታተለው ማን እንደሆነ በቅድሚያ ማጣራት ካለብኝም እሱንም ጭምር ማረጋገጥ ስለሚገባኝ ሥራ አስኪያጁን ማግኘት እንዳለብኝ አምናለሁ።" የግል ባንኮች የሴኩሪቲ ባለሙያ ይኖራቸዋል የሚል ግምት አለሽ እንዴ?" በአስተሳሰብ የበለጠችው ስለመሰለው በውስጡ እየበሸቀ ነበር የጠየቃት።

"እንደዚያ እገምታለሁ። ማንኛውም ባንክ የራሱን ደኅንነትና ምስጢር የሚጠብቅበት የሴኩሪት አሠራር ይኖረዋል የሚል ግምት አለኝ።"

"አንቺ በምትይው መንገድ ምርመራውን እናጣራ ብለን ብንነሳ

በርካታ የሃምሳ ሺህ ብር ቼኮች እየተፈረሙ ይወጣሉ። ይህ ደግሞ ሂደቱን ያወሳስበዋል።"

"እንዳልከው ቀኑ በጨመረ ቁጥር ጉዳዩ ሊወሳሰብ ይችላል። ያም ሆኖ አሠራራቸው ከሆነ መታወቂያህን ስላዩ ብቻ ምሥጢር አውጥተው ለአንተ ያሳያሉ ብለህ እንዳትጠብቅ። ለጠየቃቸው ማንኛውም አካል ሰነድ አውጥተው ለማሳየት የሕግ አስገዳጅነት አይኖርም።"

"በግድ ከቢሮው ጋር መወያየት ሊኖርብኝ ነው። የአንቺ እርዳታም ያስፈልገኛል። ወሮበላ ነጋዴዎቹን ይዘው የት እንደተሰወሩ መታወቅ ይኖርበታል። ወሮበላዎቹንም ለሁሉም ነገር ጠዋት ላይ ሪፖርት አደርግልሻለሁ።"

"ትክክለኛ ምርጫ ነው።" ቀጭን ሳቅ ጋበዘችው።

"ምን አማራጭ ይኖራል? ንብረቱን ይዘው ከሀገር ይወጣሉ የሚል ስጋት ስለ ነበር ነው የተጣደፍኩት። ሥራውን ብቻዬን እወጣዋለሁ የሚል አሳብ የለኝም።"

"የምታስበው ገብቶኛል። አየር መንገድ ካሉት የጉምሩክ ሠራተኞች ጋር የጥቅም ግንኙነት ሊኖራቸው ይችላል የሚል ስጋት አድሮብሃል? እንደዚያ ከሆነም ዕቃውን በቀላሉ ይዘው መውጣት ስለሚችሉ እኔንም እንደ አንተው ያሳስበኛል።"

"የጸጥታ ኃላፊውን በተመለከተ የደረሰሽ መረጃ አለ?"

"የናጠጠ ሀብታም እየሆነ መጥቷል። ጠዋት ይዟት የወጣውን መኪና ከሰዓት ይቀይራታል። ኑሮው የቅንጦት ከሆነ ሰንበትበት ብሏል። ይህንን ጉዳይ ቢሮአችንም መጠነኛ ክትትል እያደረገበት እንደ ነበር ታውቃለህ?"

"እንደዚያ ይሆናል የሚል ጥርጣሬ አድሮብኛል።"

"የሚፈልገውን ነገር ከሀገር ለማውጣትና ለማስገባት መደለያ መስጠቱ የተለመደ ነው። የጸጥታ ሠራተኞቹ የሚታዘዙትም በዚሁ ሰው የቀጥታ ትእዛዝ በመሆኑ የሀብቱ ምንጭ በዚህ በኩል ሊሆን እንደሚችል አልጠራጠርም።" አለች ሴቷ።

"ክትትል እየተደረገበት ነው ያልሽኝ መሰለኝ።"

"በመጠኑ እየተደረገበት እንደሆነ እገምታለሁ። ያ ማለት ግን ትኩረት የተሰጠበት ክትትል ነው ማለት አያስደፍርም።"

"ጉዳዩን ለቢሮው ሪፖርት እያቀረብኩ መልሱን መጠበቅ ሊኖርብኝ ነው።" አላትና በረጅሙ ተነፈሰ ዘሩባቤል።

"እምነህ መቀበል እንዳለብህ አትዘንጋው።"

"የተፋጠነ እርምጃ እንደማይወሰድ ተረድተሽዋል ማለት ነው። ይህ ዓይነት አሠራር በአንድ እጅ ከማጨብጨብ የተለየ አይሆንም።"

"ትኩረት መስጠቱ አስፈላጊ ነው። በተስፋ መቁረጥ እንዳትመለከተው አሳስብሃለሁ።"





"ለሁሉም ነገር ጊዜ ወስጂ አስቤ እስከምነግርሽ ታገሺኝ።"

"የምትለው ግልጽ አልሆነልኝም። ለምን ይህንን ልታስብ እንደፈለግህ ማወቅ እፈልጋለሁ።"

"አሳባችንን ወደ ሌሎች ጉዳዮች መክተት የለብንም የሚለው እምነቴ እየተጫነኝ ነው ያለው። ጉዳዩን ማወሳሰብ ይሆናል ብዬ እገምታለሁ።"

"በርግጥ የምትለው ሁሉ ትክክለኛነት ይኖረዋል። ቢሆንም ድጋሚ አስብበት።"

"ጠዋት ላይ ወደ አንቺ እመጣለሁ። ስለ አንጥረኛው በጥልቀት መወያየትና መወሰን አለብን።"

"የአንተ መምጣት አስፈላጊ አይመስለኝም። ማክረሩን ተውና እኔ መጥቼ እንወያይ።" አለችው ከረር ብላ።

"አስፈላጊ ስለሆነ አይደለም የምመጣው እኔም አንቺን በትክክል መረዳት አለብኝ።" እሱም ከረር አለ።

"ምን መሰለህ ሰውየውን ማነጋገር ያለብህ እንደኔ እምነት ብቻህን አፍነህ ይዘህ አይመስለኝም።"

"የሰጋሽው በምን ምክንያት ነው?" ሲል ጠየቃት።

"የተወሳሰበ አሳብ ሊሰጥ ይችላል የሚል ጥርጣሬ ስላለኝ ነው። በሰውየው በኩል ያለውን ምርመራ ሁለታችን ብናደርገው የተሻለ ይመስለኛል። ለአንተ የሰጠህን ቃል በፍርድ ቤት ቢክድ ዋጋ የለውም።"

"የምፈልገውን እስከማገኝ ፍርድ ቤት አላቀርበውም። መረጃ ለመስጠት እንደሚተባበረኝ ቃል የገባልኝ የግሌን ጥበቃ ሳደርግለት ብቻ መሆኑን ነግሮኛል።" አለ የመረጃ መኮንኑ።

"የቃል አፍራሽነት ስሜት ተሰማህ ማለት ነው?" በስልክ ውስጥ ስስ የሆነ ሳቅ አሰማችው።

"እሱም ያስኬዳል።" አላት ዘሩባቤል።

"እድል ስጠኝና በአንተው ወዳጅነት ቀርቤ ላነጋግረው። ምንም እንደማልጎዳው ቃል እገባልሃለሁ። ወዳጅነቱ ከልብህ ድረስ ዘልቆ ወደ ደም ስርህ የገባ ይመስለኛል።" ስትል በድጋሚ ስስ ሳቅ ሳቀች።

"ምን አልሽ?" በመገረም ጠየቃት ዘሩባቤል።

"እዚያው ስመጣ እደግምልሃለሁ።" ያንኑ ሳቋን ደገመችው።

"ምንም ዓይነት ጥያቄ የሚቀበልሽ አይመስለኝም። ብትጠይቂው ትክክለኛ የሆነ መልስ አይሰጥሽም።"

ዘሩባቤል ደውሎ ማስታወቅ እንዳልነበረበት የተረዳው በዚህን ጊዜ ነበር። መንቻካ ሲል በውስጡ ደጋግሞ ረገማት።

"በሱ ፈቃድ ብቻ የሚጠየቅ ሰው ነው ብለህ ትገምታልህ እንዴ?" አለችው።

"የመሰለሽን ልታደርጊው ትችያለሽ፡፡" አላት በመሰላቸት፡፡

ሰማንኛውም በስልክ ላይ ከዚህ በላይ የሚደረግ ውይይት ጥሩ አይደለም፡፡ እዚያው ስመጣ ሌላም የምነግርህ ምሥጢር ይኖረኛል፡፡"

"ምንድነው የምትነግረኝ? ከዚህ የተለየ..." አላስጨረሰችውም፡፡

"እዚያው ስመጣ አልኩህ እኮ፡፡ ከሰውየው ብዙ ነገር ማግኘት እንደምችል እገምታለሁ፡፡ በምርመራዬ ጣልቃ እንዳትገባ ተጠንቀቅ፡፡"

"የሚያውቀውን ያህል የነገረኝ ይመስለኛል፡፡" ያመነታ መሰለ መርማሪው፡፡

"አንተን ያስጨነቀህ ወዳጅነቱ መሰለኝ፡፡ በጣም አጥብቀህ ተጠነቀቅህለት እሳ፡፡ ለልብ ወዳጅነት የምትመረጥ ዓይነት ሰው ትመስላለህ፡፡"

"የጀመርኩት የምርመራ ሂደት አንቺ ከምታስቢው የተሻለ ነው የሚል እምነት ስላለኝ ነው፡፡ ከመሰለሽም የምትፈልጊውን በፈለግሽው ጊዜ ልታደርጊው ትችያለሽ፡፡"

በዚያው ስልኩ ተዘጋ፡፡ ከመኝታው ላይ ሆኖ ያስብ የነበረው ልብን እየሰነጠቀ ወደ ደም ስር የሚገባውን የሳቅ ቅላጼ ነበር፡፡ የተረገመች የልብ ቀበኛ አለ በውስጡ ዘሩባቤል፡፡ እሷን ትቶ ስለ አለቃው ለማሰብ ሞከረ፡፡ ምን እየተፈጠረ እንደሆነ እየገባው አይደለም፡፡ ብዙ ነገሮች እየተበላሹ ናቸው፡፡ የጸጥታው መስሪያ ቤት ጉዳይም እያበቃለት ነው፡፡ ሙሉ በሙሉ እየታዘዘ ያለው በጠቅላይ ሚኒስቴር ጊዜያዊ የጸጥታው ማዘዣ ጣቢያ ሆኗል፡፡ የሕዝብ ደኅንነት ቢሮው ጥርስ የሌለው አንበሳ ከሆነ ውሎ አድሯል፡፡ ጥርስ የሌለው አንበሳ ለሆዱም አይሆንም እናም ሁሉም ነገር አከተመ ማለት ነው፡፡ ስለ ሴቷ አስቦ እንደ ሽማኔ መወርወሪያ ከመጠን ያለፈ ስለምትፈጥን ለልቅና የምትስማማ አይደለችም፡፡ያም ሆኖ አለቃው ሆናለች፡፡ ከጠቅላይ ሚኒስቴር ቢሮ ያለው የደኅንነት የመረጃ ቢሮን በሁለተኛነት እየመራች ያለችው እሷ ስለሆነች የግድ መስማማት አለበት፡፡





# ምእራፍ ዘጠኝ

የሚማርክ ተክለ ሰውነትና ውብ መልክ የነበራት ሴት በድንገት ደሟ ተለዋውጦ ወደ አውሬነት ስትቀየር ሲመለከት ሳይገርመው አልቀረም፡፡ እንደ ቆሰለች እመጫት ነብር ስትቅበጠበጥ ሲመለከት ልቡን የመረበሽ ስሜት ተሰማው፡፡ ገብረክርስቶስ፡፡

የፈለገችውን በአሰበችው መንገድ እየተረጎመች ስትዝትበት በትዕግሥት ማዳመጥ ነበረበት፡፡

"ከኔ ጋር እንሄዳለን፡፡" ቀጭን ሰንሰለት ከኪሷ ስታወጣ ተመለከተ፡፡ መግደርደር አልፈለገም፡፡ እጁን አስተካክሎ ሰጣት፡፡ ከዚህች አደገኛ ከምትመስል ሴት ጋር እልህ መጋባት አልፈለገም፡፡ የተቀባበለ ሽጉጥ በእጇ ላይ ነው ያለው፡፡ አእምሮዋንም ትንሽ ነካ ያደረጋትም መሰለው፡፡ ሁኔታዋ ሁሉ የጤነኛ አይመስልም፡፡ ከልክ ባለፈ ትፈጥናለች፡፡ ንክ ሳትሆን አትቀርም፡፡ ፈረንጆች ክሬዚ የሚሉት ዓይነት፡፡ እብድ ሲላት አልፈለገም፡፡ በሱ ግምት እብድ አይደለችም፡፡ እብድ የሚሠራውን አያውቅም፡፡ ይህች ግን የምትሠራውን ብቻ ሳይሆን ለምን እንደምትሠራም ታውቃለች፡፡ መመደብ ያለባት እብድ ተብሎ ከተሰየመው ሳይሆን ንክ ወይም ወፈፌ ከሚለው ነው፡፡ እንደ ፈለገች ለመተወን የተፈቀደላት ጥሩ ዘመናይ ነች፡፡ ሁኔታዋን እየተመለከተ አሰበ፡፡ ዘመናይ የፈለገውን ለማድረግ ይችላል፡፡ ስለዚህ መጠንቀቅ አለበት፡፡ የሚሰጣትን ምላሽ ከአፉ ከማውጣቱ በፊት ደጋግሞ ማሰብ ይጠበቅበታል፡፡

ዳሩ እብድ የታለና ነው፡፡ ኢንሳይክሎፒዲያ እንደሚለው ከሆነ በዓለም የተመዘገቡ ሁለት እብዶች ነበሩ፡፡ አንደኛው ከሳተ ጎሞራ ውስጥ ገብቶ በዚያው ተንጨርጭሮ ሲቀር ሁለተኛውም ህንድ ውቅያኖስ ውስጥ ገብቶ የአሳ ነባሪ ቁርስ ሆኗል የሚል ወሬ ሰምቷል፡፡ የማንበብ እድል ስለሌለው በወሬ የሰማውን ይይዛል፡፡ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ንክ አለዚያም ክሬዚዎች ይኖራሉ፡፡ የሚል አፈ-ታሪክ አለ፡፡ የእብድ ትርጉሙ ስለማይገባን ልብሳቸውን ስላወለቁ ብቱቶ ስለለበሱ "እብዶች" ተብለው ተጠሩ፡፡ ብዙ ስለሚያውቁና ስለሚያስቡ እብድ አልነበሩም አይደሉም፡፡ የራሳቸው ፍልስፍና በዝቶ አእምሮአቸውን ቢያስጨንቀውና እራሳቸውን ከዓለም አግልለው በራሳቸው ዓለም መኖር ቢጀምሩ እብድ ተብለው ተጠሩ፡፡ በማለት ይናገሩ የነበሩት አንድ የወርቅ ደንበኛው የዩኒቨርሲቲ አስተማሪ ነበሩ፡፡ በትክክል አድምጧቸዋል፡፡ ተምሮ ማንበብ ባይችልም ጥሩ አድማጭ ነው፡፡ በማድመጥ ታሪክ አዋቂ ነው፡፡ በቃ ስለ እብዶች እያሰበ ስለነበር ምን ያህል ርቀት እንደ ተጓዙ ትዝ አይለውም፡፡

ከመኪና ይዛው ወርዳ ወደ ልዩ የምርመራ ክፍል በምትወስደው ሰዓት ሁሉ በራሱ ፍልስፍና ውስጥ ስለ ነበር በደመነፍስ የሚገፋ ፍጡር

ይመስል ነበር። ወደ ውስጥ እንደገቡ ከሰመመኑ እንደ ነቃ ሕመምተኛ አካባቢውን በጥንቃቄ ለመቃኘት ሞከረ። በመስኮቶቹ ወደ ውስጥ እየገባ ከነበረው ከሩቅ ከሚመጣ ደብዛዛ ብርሃን በቀር ሰፊው ሳሎን ምንም የመብራት ዘር አልነበረበትም። በክፍሉ ውስጥ ያሉት እቃዎች በሙሉ በደብዛዛው ጨለማ ቅርጻቸውን ብቻ ይዘው ይታያሉ። በክፍሉ አንደኛው ጥግ በኩል በመጽሐፍ የተጨናነቀ ትልቅ መደርደሪያ ቆሟል። ብርሃን እንደ ልብ እንዳይሰጡ ዕድል የተነፈጋቸው የሚመስሉ አምፖሎች ተራርቀው በኮርኒሱ ተንጠልጥለዋል። ክፍሉ የጨለማ ድባብ እንዲውጠው የተደረገበት ምክንያት ለአንጥረኛው ግልጽ አልነበረም። ሊገምተው የቻለው ቢኖር በንጽሕና የተያዘው ሰፊ ሳሎን ለአንድ ነገር ብቻ የተዘጋጀ ሊሆን እንደሚችል ነው።

ሳሎኑ ከትንሽ ደቂቃዎች በፊት በብርሃን የተጥለቀለቀ እንደ ነበር ነው የገመተው። ደብዛዛ ጨለማ እንዲውጠው የተደረገበት ምክንያት የሱን ስነልቦና በማሸበር የቅድሚያ ምርመራ ዘዴ ለመጠቀም ተፈልጎ እንደሆነ ጠረጠረ። ምንነታቸውን ለመለየት በማይቻል ብርሃን አልባ ክፍል ውስጥ አስቀምጠው ሕሊናን ሊያሸብሩና ፍርሃትን ሊለቅቁ የሚችሉ ጥያቄዎችን ከግራና ከቀኝ እያከታተሉ ሊያጣድፉት መዘጋጀታቸውን ተረዳ። በረቀቀ የምርመራ ዘዴ ከጥልቅ ውቅያኖስ በአፍጢሙ የተጣለ እስከሚመስለው ድረስ የፍርሃት ቅዝቃዜ ከአእምሮው እየሄደ በመግባት ሰቅጦ ያስጨንቀዋል። ከዚያ በኋላ ያየውንና የሚያውቀውን አይደለም ያላየውንና ያልሰማውን፣ ያልተረዳውንና የማያውቀውን ጭምር እፉ እንደተፈታ የድንች ጆንያ ይዘረግፋል።

በአንደኛው ጥግ በኩል ከነበረው ሶፋ ላይ የሆነ ነገር ሲንቀሳቀስ ተመለከተ። አንድ ሰው ከሶፋው ላይ እንደ ተቀመጠ ሰውነቱን ሲያነቃንቅ ነበር ያየው። በነበረበት ሰውነቱን አስተካክሎ አንድ እግሩን ከአንደኛው ላይ ሲደርብ ነበር የተመለከተው። የዚህን የአቀማመጥ ዘይቤ የማን እንደሆነ ያውቅ ስለነበር ሰውነቱ በድን የሆነ እስከሚመስለው ድረስ በተቀመጠበት ድርቅ ብሎ ቀረ።

"በዚህ ክፍል ውስጥ የተቀመጡት እኔን ለመመርመር? አይደረግም። ምን ክብር ሰጥተውኝ ነው እኔን ለመመርመር ከጨለማ ክፍል ውስጥ የሚጠብቁኝ። ይህ የኔው የፍርሃት አሳብ ነው።" በራሱ ከንቱ ምኞት ቢስቅ እንዴት ደስ ባለው ነበር። ግን ለሳቅ የሚሆን የተረፈ ብናኝ ጽናት አልነበረውም። ተስፋው ጨርሶ ተሟጧል።

ልቡ ወጥታ ከመሬት የወደቀች ያህል ሰውነቱ ሲቀልለው እየተሰማው ክፉኛ ተዳክሟል። የራሱ በማይመስል እይታ ሰፊውን አዳራሽ ተመለከተው። በሌላው የኮሪደሩ ጥግ የተቀመጠ ሰው መኖሩን ልብ ያለው ከዚህ በኋላ ነበር። ለየብቻቸው ተራርቀው የተቀመጡ በርከት ያሉ ሰዎች ሊኖሩ እንደሚችሉ ገመተ። ከነበረበት ፊት ለፊት ሴቷ ተቀምጣለች። ሰፊው





አዳራሽ በጸጥታ የተዋጠ ስለ ነበር መርፌ ከመሬት ቢወድቅ መሰማት ይችላል። በመጀመሪያ ያየው ሰው ብድግ ብሎ ሲቆም በደብዛዛው ብርሃን እንደ ጥላ ግዙፍ ሆኖ ታየው። የገመተው ሰው እንደዚህ የገዘፈ ተክለ ሰውነት እንዳልነበረው ያውቃል። ሌላ ሰው ነው። ሰውዬው በዝግታ እየተራመደ ወደ እሱ አቅጣጫ ሲመጣ ሲመለከት ልቡ ተወጥራ ደረቱን ትደልቀው ያዘች።

"የቁርጡ ቀን መጣ።" ለራሱ ፍጻሜው መቃረቡን አበሰረው።

"እንደምን አመሸህ?" ከአጠገቡ ገደል መስሎ እየተገተረ ሰላምታ ሰጠው ሰውየው።

"እንደምን አመሹ ጌታዬ?" ቃላቶቹ እየተቆራረጡበት ስለነበር ተበሳጨ።

"ለፈረንጁ ጎራዴውን የሰራኸለት አንተ ነበርክ?" በተረጋጋ የድምጽ ቅላጼ በቀጥታ ፍሬ ጉዳዩን ጠየቀው ሰውየው።

"አዎን እኔ ነበርሁ።" ሲል መለሰለት።

"ጎራዴውን የሰራኸው ከወርቅ አቅልጠህ ነው።"

"አዎን።" ባጭሩ ተናገረ።

"ወርቅ የሀገራችን ሀብት መሆኑን እያወቅህ ለምንድን ነው ለባእዳን መሳርያ በመሆን አሳልፈህ የሰጠኸው?" እንደ መሳቅ አለ ግዙፉ ሰው።

"እኔ እኮ አይደለሁም ወርቁን የሰጧቸው። የማቅለጡን ሥራ ብቻ ነው የሠራሁት።" የድምጹ መርገብገብ ስለጨመረበት በራሱ ተበሳጨ አንጥረኛው። መጥፎ ፍርሃት በደም ስሬ ገብቶ ይዞኛል። ምን ዓይነት የማልረባ ውሻ ነኝ? ራሱን ሰደበ። ከፊቱ የቆመው ሰው የገዘፈበት ሰውነቱ ብቻ አልነበረም ድምጹም እንደ ሰውነቱ ወፍራምና እንደ ነጐድጓድ የሚቀረሻሽም ነበር።

"ከፍተኛ የሆነ ወንጀል ነው የሰራኸው። በማይታወቅ መንገድ የሀገሪቱ ውድ ንብረት ድንበር እንዲሻገር ተባብረሃል። ወርቁን ባትሰጥም ወርቁ ባልታወቀ መንገድ ወደ ሌላ ቁስ ተለውጦ እንዲወጣ መተባበርህ ወንጀል ነው።"

"በርግጥ እንደዚያ ማድረጌ ጥፋት ነው። ይህም የተከሰተልኝ ዘግይቶ ስለሆነ ኃዘን ተሰምቶኛል። የከፈሉኝ ገንዘብ ከፍተኛ ስለነበር በመጀመሪያ የጥፋተኝነት ስሜት አልተሰማኝም ነበር። አሁን ግን እጅግ አዝኛለሁ።"

"ማዘንህ ብቻ በቂ አይሆንም። ትክክለኛ ምሕረት የምትጠብቅ ከሆነ የምታውቀውን ማንኛውንም ነገር ትነግረኛለህ። ይህንን ከባድ ወንጀል ለመከታተል የአንተ መረጃ ይጠቅመናል።"

"ጎራዴውን ሠርቼ ከማስረከቤ በቀር ምንም የማውቀው ሌላ ምሥጢር የለኝም። የማውቀው ቢኖርና ተጨማሪ መረጃ ብሰጣችሁ የመንፈስ ደስታ በተሰማኝ ነበር።"

"እንደዚያ የምታስብ ኸሆነ ራስህን ከስህተት ውስጥ እየከተትከው

እንደ ሆነ ልትረዳ ይገባሃል፡፡ ለቀልድ ጊዜ የለኝም፡፡ የምጠይቅህን ብቻ ሳይሆን የምታውቀውን የምታስታውሰውን ሁሉ ልታስረዳኝ ግዳጅ አለብህ፡፡ ከወርቁም በስተጀርባ የምንፈልጋቸው በርካታ ነገሮች አሉን፡፡ ከነዚህ አንዱን መረጃ ብትሰጥ ለሕይወትህ እንደ ዋስትና ይያዝልሃል፡፡ የምንልህን በተገቢው መንገድ የምትተባበር ከሆነ ሽክምህን እንዳቀለልህ ቁጠረው፡፡"

ሰወዬው ከረር ባለ ድምጽ ያስተላለፈለት ማስጠንቀቂያም ጭምር ከመግዘፋ ጋር ተደማምሮ የፍርሃት ውቅያኖስ አስመጠው፡፡

"ምንም የተለየ ከዚህ ውጭ የማውቀው ምሥጢር የለም፡፡ የማላውቀውን ከየት እያመጣሁ ልናገር እችላለሁ ጌታዬ፡፡" ለመለማመጥ ሞከረ፡፡

"ብዙ በጣም ብዙ ነገሮችን ታውቃለህ፡፡ የምታውቀውን በመንገር እንድትተባበረን እንፈልጋለን፡፡ እደዚያ ከአደረግህ አንድ ውለታ ሰርተህ ከተጠያቂነት ትድናለህ ማለት ነው፡፡ እኛም ብንሆን በአንተ አንጨክንም፡፡"

"የማላውቀውን ብትጠይቁኝ ከየት ላመጣ እችላለሁ፡፡"

"ከአንተ የምንፈልገው ብዙ ምሥጢር አለን፡፡ ለምንጠይቅህ ቀጥተኛ የሆነ መልስ እንፈልጋለን፡፡" አለ ሰውየው በድጋሚ፡፡

"በጣም እየፈራሁ ይመስለኛል ጌታዬ ሆዴም ጥሩ ስሜት እየተሰማኝ አይደለም፡፡ በመጀመርያ ወደ ሽንት ቤት ደርሼ ብመለስ፡፡" እጁን ከፍ አድርጐ ጠየቀ፡፡

"እውነቱን እስከ ነገርከን ድረስ የምትፈራበት ምንም ምክንያት አይኖርም፡፡ የመንግሥት አካል ስለሆን ለሕይወትህ ጥበቃም ኃላፊነት አለብን፡፡ ወንጀለኛ ሆነህ ብትገኝም ዜግነትህ የሚጠይቀውን ነገር ሁሉ የመፈጸም ኃላፊነት አለብን፡፡"

"እሱን እንደምታደርጉልኝ አምናለሁ፡፡ ያም ሆኖ ከማውቀው ውጭ እንድናገር ማድረግስ ሰብአዊነቴን መንፈግ አይሆንም? እባክዎ ሆዴን ሕመም እየተሰማኝ ነው፡፡"

"አለማወቅህንም የምንረዳው ከምርመራ በኋላ ነው፡፡ መረዳት ያለብህ ነብይ አለመሆናችንን ነው፡፡ እውነትና ሐሰት መሆኑን የምናረጋግጠው በምርመራ ነው፡፡"

"ልታሰቃዩኝ እያሰባችሁ ናችሁ ማለት ነው?"

"ያንን የምትወስነው ራስህ ነህ፡፡ ካቀለልከው ይቀልላል፡፡"

በደብዛዛው ጨለማ የሰውየው ግዙፍ ሰውነት ተጨምሮ እንደ መቃብር ቢከብደውም መጠበቅ ያለበት ከሰውየው የሚመጣለትን ጥያቄ ብቻ ነው፡፡ እንደ አስፈላጊነቱ ይመለሳል፡፡ በመደናገጥ ብዙ ነገሮችን ማበላሸት እንደ ሌለበት ያምናል፡፡ ከሽንት ቤቱ ሳህን ላይ እንደተቀመጠ ብዙ አሰበ፡፡

"ከአሁን በፊትም ለፈረንጁ ሌሎች ጌጣጌጦችን ሠርተህለት እንደ ነበር መረጃው አለኝ፡፡ እነዚህንም ትክዳለህ?" አለ ከሽንት ቤት መልስ፡፡

"ሠርቼለታለሁ"፡፡ ያም ሆኖ ሁሉም ነገር በምሥጢር ሊያዝልኝ ይገባል፡፡ እንደዚያ ካላደረጋችሁልኝ የቤተሰቤ ሕይወት አደጋ ላይ ይወድቃል፡፡"

"ያልከው ትክክል እንደሆነ አምንበታለሁ፡፡ ሁሉም ነገር በምሥጢር ሊያዝልህ እንደሚገባም በእርግጠኝነት ልነግርህ እችላለሁ፡፡ ያንን እንድናደርግልህ የምንገደደው አንተ ለእኛ ከምትሰጠን የመረጃ ጥቅም አንፃር ብቻ ይሆናል፡፡ እንደዚያ ካልሆነ የቤተሰብህም ሕይወት አደጋ ላይ ይወድቃል ማለት ነው፡፡ እየተነጋገርንበት ያለው ጉዳይ የሕዝብና የአገር ጥቅም ስለሆነ ለግለሰቦች ደኅንነት የምንጨነቀውም ከዚህ አንፃር ይሆናል፡፡ በየትኛውም መንገድ ምቹ ሆነህ መቅረብ ይኖርብሃል፡፡"

"እናንተም ብትሆኑ የማላውቀውን ጉዳይ በግድ እወቅ ብላችሁ እንደማታስገድዱኝ ኅሊናችሁ ሊያዛችሁ ይገባል፡፡ እኔ የምናገረው እውነት መሆኑን የሚመሰክር የለምና በማላውቀው ጥያቄ እንዳታስገድዱኝ፡፡"

"በምታውቃቸው ምሥጢሮች እንጀምር፡፡ ለፈረንጁ ስለሠራኸው ጌጣጌጥ እኔ ከመጠየቄ በፊት እራስህ ልትነግረኝ ትችላለህ፡፡"

ከአጠገቡ ከነበረች አነስተኛ ጠረጴዛ ላይ ከፊት ለፊቱ ቁጭ አለ፡፡

"ቀደም ሲል ሁለት ትላልቅ የቤተክርስቲያን መስቀሎችን ሠርቼለት ነበር፡፡"

"በዚያን ጊዜ ምን ያህል ተከፈለህ?" በደበዘዘው ጨለማ ፊቱን እየተመለከተ ጠየቀው፡፡

"ሦላሳ ሺህ የኢትዮጵያ ብር፡፡" አለና በረጅሙ ተነፈሰ፡፡

"ቢመዘኑ ምን ያህል ኪሎ ግራም እንደሚሆኑ ገምተህ ነበር?"

"እያንዳንዳቸው ከሁለት ኪሎ ግራም የሚያንሱ አልነበሩም፡፡"

"የተከፈለህ ብር በቂ ነው ብለህ አምነህበት ነበር የተስማማኸው?"

"ከነበረኝ ገቢ ያሰላሁት ጥቅም ስለነበር ለጊዜው ከበቂ በላይ እንደሆነ ነበር የተሰማኝ፡፡"

ይህኛውን በዚሁ ተወውና ወደ ሌላ የመላምት ምርመራ ተሸጋገረ፡፡ በተናገረ ቁጥር ድምጹ እንደ እባብ እሬሳ ቢያስበረግገውም ፍርሃቱን ለመከላከል እየተጣጣረ ነበር፡፡

"ክፍያውን በቼክ ላይ ከሚፈርምልህ አንድ ኢትዮጵያዊ ነጋዴ ጋር የጠበቀ የጥቅም ትስስር ፈጥራችሁ እንደ ነበር ሰምቻለሁ፡፡ ይህስ ትዝ አይልህም?" ከሲኦል የጸና ጸጥታ ያሰፈነ ጥያቄ ነበር፡፡

ጥያቄዎቹ በቀላሉ የሚመለሱ አልነበሩም፡፡ የነገሮቹ ሁሉ ውል ያለው ከዚህ ጥያቄ ጫፍ ላይ ነው፡፡ መርማሪው በአጋጣሚ ውሉን ይዞ ሊጎትተው እየሞከረ ሲስበው ውስጡ ታወከበት፡፡

ሽምጥጥ አድርጎ በመካድና በማመን መካከል ነፍሱ ተጨምቃ ተይዛ እየቃተተችበት ከጥልቅ ውቅያኖስ ላይ የተጣለ ያህል ሰውነቱን ኃይለኛ የጭንቀት ቅዝቃዜ ተሰማው፡፡ የመረጃ መኮንኑ ጠይቆት ቼክ የፈረመለትን ሰው እንደማያውቀው ምሎለታል፡፧

"ምነው ተረበሽህ? አይዞህ ንገረኝ።" መርማሪው ወደ ትክክለኛው የነገሩ እምብርት እየገባ እንደሆነ ተረድቷል።

"ግን..." እውነቱን ከመናገሩ በፊት አቅማማ። "ቢሆንም እኮ ነጋዴና ባለሙያ..." መርማሪው አቋረጠው።

የማደናገሪያ አሳብ ማቅረብ በፍጹም ዕድል አይሰጠውም ውሉን አግኝቶታል።

"ማብራሪያ አያስፈልገኝም። እኔ ለምጠይቅህ ብቻ መልስ በመስጠት እንነጋገራለን። ከነጋዴው ጋር ቀደም ሲል የጠበቀ ደንበኝነት አለዚያም ወዳጅነት እንበለው ነበራችሁ። በወርቅ ሥራ ጥበብ የተካንህ ስለ ነበርህ በፈለገው ዓይነትና ቅርጽ ጌጣጌጦችን ትሠራለት ነበር። ለምትሠራቸው የጥበብ ሥራዎችህም ክፍያህን ሳያስቀር እየከፈለህ ቆይቷል። ይህ ጥያቄዬ እውነት ነው ወይስ አይደለም?" ከአንገቱ ወደሱ ሲጠጋው የበለጠ ገዘፈበትና ልቡ ክፉኛ ስትረበሽ ታወቀው።

"ከተነጋገርነው የክፍያ ውል ውጭ የከፈለኝ ወይም ቀንሶ ያስቀረብኝ ምንም ነገር አልነበረም።"

"ታማኝ ደንበኛህ ነበር ማለት ነው። አሁንም ቢሆን ደንበኝነታችሁ በዚሁ መንገድ መቀጠል ስላለበት በሁለታችሁ መካከል ገብተን አረግ የለበሰ ወዳጅነታችሁን ልንበጥስ አንከጅልም። አብራችሁ ብዙ መረጃዎችን ለዚህ መስርያ ቤት መስጠት ይጠበቅባችኋል። ወዳጅክንም እንፈልገዋለን ማለት ነው። በአገር ውስጥ ይገኛል ወይስ ውጭ ነው ያለው?" የመርማሪው ድምጽ ከረር እያለ የመጣ መሰለው።

አካባቢውም በደብዛዛ ጨለማ የተዋጠ ሆኖ ፊቱን ለማየት ባለመቻሉ እራሱን እንደ ዕድለኛ ቆጠረው።

"ይህ ሰው ስለ መብት የሚከራከር የፖለቲካ መሪ መሆኑንስ ታውቅ የለም እንዴ? ጥሩ ፖለቲከኛ በመሆኑም ለሰው ልጆች እኩልነትና ነጻነት የሚከራከር የተዋጣለት ፖለቲከኛ ጮሌ ሕገ ወጥ ነጋዴ። ቼኩን ይፈርምልህ የነበረው ቀጥታ በራሱ ስም ነበር? ከአንተ የምንፈልገው ስለዚህ ሰው ብዙ ነገር አለን። በቅርብ አግኝተኸው ስለማንኛውም ጉዳይ ትነጋገሩ ነበር።" የበለጠ ከአንገቱ ቀረበው።

"ቼኩ የሚፈረምልኝ በራሱ ስም ሳይሆን በልጁ ስም ነው።"

"የልጁ ዋና የሥራ ድርሻ ምንድነው?" ከተቀመጠበት ተነሳና ቆመ።

"በውል አላውቅም። ሆኖም ዶክተር መሆኑን ሰምቻለሁ።"

"ዶክተርነቱ በምን ዙሪያ እንደ ሆነስ ታውቃለህ?" ተመልሶ ከጠረጴዛዋ ላይ ተቀመጠ።

"እርሱንም በውል የማውቀው ነገር የለኝም። ዶክተር መሆኑን ግን አባቱም በተደጋጋሚ ነግሮኛል። ስለ ልጁ ያለኝ እውቀት ብዙ ባለመሆኑ ቼኩን ላስፈርም ስሄድም ንግግር የለንም።"





"ሰውየው ሌሎች ጥቅማጥቅሞችን ይሰጥህ ነበር። አይደለም እንዴ? ለምሳሌ ቤትክን በምትሠራበት ወቅት የተለያዩ ቁሳቁሶችን 'ረድቶህ እንደ ነበር ሰምቻለሁ?" ከተቀመጠበት እንደመነሳት እያለ ጠየቀው።

"አንዳንድ ነገሮችን ረድቶኛል። በገንዘብ በኩልም ድጋፍ ያደርግልኝ ነበር።"

"ከልጅየው ጋርስ ግንኙነት ነበራችሁ? ማለቴ ጥቅምን በተመለከተ።"

"እንደገለጽኩልዎት ብዙም ግብብነት የለንም። አባቱም ቢሆን ከልጁ ጋር እንድንግባባ አይፈቅድም። ልጁን እንደ ገራገር እና የዋህ አድርጎ ስለሚያስብ ይመስለኛል ምሥጢራዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ከሌሎች ሰዎች እንዲገናኝ የሚፈቅድለት አለመሆኑን በአጋጣሚ ነግሮኝ ነበር።

"የሜርኩሪ ንግድም እንደሚያካሄድ መረጃ አለን። ስለዚህስ የነገረህ የለም?" አለ መርማሪው።

"ምንም የማውቀው ነገር የለኝም።"

አንጀቱ ውስጥ እንደገባበት ሁሉ ውስጡ እንደ ውቅያኖስ ውኃ ሲተረማመስ የሆድ ሕመሙ እንደገና ሲቀሰቀስ ተሰማው። ሰውነቱ በሙሉ መናወጥ ጀምሯል።

"ለምን ይመስልሃል ያልነገረህ?" መርማሪው መልሶ ተቀመጠ።

"የኔን ሙያ የሚጠይቅ ባለመሆኑ ሊሆን ይችላል የሚል ግምት አለኝ።"

የሜሪኩሪም ሆነ የዩራኒዩም ንግዱ የወርቅ አንጣሪውን ሙያ የሚጠይቁ አልነበሩም። የነበራቸው ወዳጅነት የሙያ እስከሆነ ድረስ ሙያው በሚመለከተው እየተግባቡ በወዳጅነት ቀጥለው አሁን ላይ ደርሰዋል።

"ሌሎች ሙያው ያላቸውን ደንበኞች ማፍራት ስለሚችል አንተን ላይፈልግህ ይችላል። ሜርኩሪ እንደሚነግድ ሰምተሃል አይደለም እንዴ?"

"በወሬ ደረጃ እንደ ማንኛውም ሰው እሰማለሁ። እንደሚሉት ለተትረፈረፈው የሀብት ምንጩ የአልማዝና የሜርኩሪ ንግድ ነው የሚል ነው።"

"ግን እኮ እንደ ሀብታም እጁ ሰፊ የሚባል አይደለም። የሚከፍልህ ክፍያ በጣም ጥቂት ነው። ለምን ይመስልሃል?" አለ መርማሪው።

"በተፈጥሮው ያለው ስስት ካልሆነ በቀር የገንዘብ እጥረት የለበትም።"

በሁለቱ መካከል እንደ ገና ዝምታ ሆነ። ያለፉት የጸጥታ ደቂቃዎች ለሁለቱም ጥሩ የማሰቢያ ጊዜ ሆነው ነበር ያለፉት። ሰውየው ፊቱን በሁለት አቅጣጫ እየመላለሰ ወደ ሴቷ እና በአንድ ጥግ ወደ ተቀመጠው ሰው በደብዛዛው የጨለማ ብርሃን ሲመለከት "አለን" ለማለት ይመስላል ከተቀመጡበት በትንሹ ሲንቀሳቀሱ ለአንጥረኛውም ታዩት።

ፍልፈሎች። በያሉበት አንገታቸውን ቀብረዋል። ጆሮአቸውን አንቅተው

በሁለቱ መካከል የነበረውን ቃለ ምልልስ በመሳርያ እየቀረጹ ሊሆን እንደሚችል አልተጠራጠረም።

"በሁሉም ነገር የተስማማን ይመስለኛል። እንድንቀጥል የምትጠጣው ምን ይምጣልህ? ሻይ ወይስ ቡና?" ግብዣው ፍላጎቱ በመሆኑ ስሜቱን መግታት አልፈለገም።

"ቡና ይሻለኛል። እራሴን እያመመኝ ስለሆነ ቡና መጠጣት ይኖርብኛል።"

ከተቀመጠበት ተነስቶ በሳሎኑ በአንደኛው መዓዘን በኩል ያለውን መጋረጃ ሲሰበስበው ከወፍራም ጣውላ የተሰራው ትልቅ በር ለአንጥረኛው በደብዛዛው ብርሃን ታየው። በዓይኑ እየተከተለው ወደ ውስጥ ገባ።

ከተወሰኑ ደቂቃዎች በኋላ ሲመለስ አንድ የቡና ጀበናና አራት ሲኒዎችን በትሪ ላይ ደርድሮ ነበር።

ለአንጥረኛው አንድ ሲኒ ቡና ቀዳለትና ለሁሉም እንደሚፈልጉት ከአደላደለ በኋላ ለራሱም ቀድቶ በተለመደው አኳኋን ከጠረጴዛው ላይ ሲቀመጥ ለመጀመሪያ ጊዜ አንጥረኛው ፊቱን ለማየት ቻለ። ቡናቸውን ጠጥተው እስከ ጨረሱበት ሰዓት ድረስ ቃለ ምልልሱን አቁመው ነበር። ከቡና ፉትታ በቀር አዳራሹን ጸጥታ ውጦት ነው የቆየው። መብራቱ ወለል ብሎ በርቷል።

"የድርጅታቸውንስ ስም አታውቀውም?" ከቡና በኋላ የመጀመርያ ጥያቄ በመሆኑ አንጥረኛው በድጋሚ ተረበሸ።

"የነማንን ድርጅት?" ቀና ብሎ ፊቱን እየተመለከተ መልስ ጠየቀው።

"የወዳጆችህን" አለ ረጋ ብሎ።

"አላውቀውም። ድርጅት አላቸው እንዴ?" እንደ መገረም አለ አንጥረኛው ገብረክርስቶስ።

"ቢሮአቸው ገብተህ አታውቅም ማለት ነዋ?" ሳቅ አለ መርማሪው።

መብራቱ ጠፍቶ አዳራሹ ተመልሶ በጨለማ በመዋጡ የተለመደው ፍርሃት ነግሶበታል።

"እንደዚህ ያለው ነገር አልገጠመኝም።"

"እንግዲያው ዕድለኛ አልነበርክም ማለት ነው።"

"እንዴት?"አንጥረኛው ጠየቀው።

"ቀረብ ብለህ ቢሆን ቢያንስ የአቃቤ ሕግ ሥልጣንነቱን ሊሰጡህ ይችሉ ነበር ለማለት ነው።"

"የምን አቃቢ ሕግ?" ጆሮውን አቅንቶ መልሱን ተጠባበቀ።

"በፍርድ ቤታቸው ነዋ።" መርማሪው እንደ መሳቅ አለ።

"ፍርድ ቤትም አላቸው እያልከኝ ነው?" በመገረም አለዚያም በመደናገር ጠየቀው።

"ስህተት ብትፈጽም በሕጋቸው እንደምትቀጣ አስጠንቅቆህ እንደ ነበር





ልትክደኝ እየሞከርክ ነው ማለት ነው።" የተበሳጨ መሰለ መርማሪው።

"አስጠንቅቆኝ እንደ ነበር አውቃለሁ። የፍርድ ቤት ሕግ አላቸው ስለምትለው ጉዳይ የማውቀው ምንም ምሥጢር የለኝም።"

"እንደሚቀጡህ ያስጠነቀቁህ በምን ዓይነት ሕግ ነው ብለህ ገምተህ ነበር?" መርማሪው ለስለስ ያለ ሳቅ ሳቀ።

"በእውነቱ የራሳቸውን መንግሥትና ሕግ መስርተው እንደሚያስተዳድሩ የማውቀው ወይም የተነገረኝ ነገር የለም።"

የአንጥረኛው አግራሞት በጥፍ እየጨመረበት መምጣቱን ከድምጹ መረዳት በመቻሉ ምንም እንደማያውቅ ተረዳው።

"ሳይነግሩህ በመቅረታቸው ቅር ሊልህ ይገባል። የልብ ወዳጆችህ አልነበሩም ማለት ነው።" በፌዝ እንደሚናገር ገብቶታል።

"በርግጥ ልክ ነው። ያም ሆኖ እኔ የምፈራው ሌላ ነበር። አንተ ደግሞ ለየት ያለ ወሬ ነገርከኝ።" ቀና ብሎ በደብዛዛው ጨለማ ፊቱን ለመመልከት እየሞከረ መለሰለት።

"የምትፈራው ምን?" መርማሪው መልሱን ለመስማት ተቅበጠበጠ።

"የምፈራው?" ከመናገሩ በፊት አመነታ። "እሱ እንኳ ለእኔም ሆነ ለአንተ ጥሩ ስለማይሆን ባልነግርህ የተሻለ ነው። ትክሻውን ጭምር እየነቀነቀ መጥፎ ነገር መሆኑን ሊያስረዳው ሞከረ።

"ምንድነው ጥሩ የማይሆነው ይህንን ያህል ያስፈራል ማለት ነው?"

"ባልነግርህ አንተም ባትጠይቀኝ የተሻለ ነው።" ነገሩን ይበልጥ ለማክበድ እየሞከረ መለሰለት።

"ሁለታችንንም የሚያስጋ ከሆነ ነገሩን በምሥጢር ልይዘው እችላለሁ። የመንግሥት አካል ስለሆንሁ ማንኛውንም ችግር ለመቋቋም የሕግ ግዴታ አለብኝ።"

"መንፈስ ስለሆነ በምሥጢር ብነግርህም ያውቀዋል።" አለውና በረጅሙ ተነፈሰ አንጥረኛው።

"ስለየትኛው መንፈስ ነው የምትጨነቀው?" አለ መርማሪው።

"የወርቅ ጎራዴ የተሠራለት መንፈስ ነዋ። ሌላ ምን መንፈስ ይኖራል።" ድምጹን ቀንሶ አንሾካሾከለት።

ምንም ፍንጭ እንዳይሰጥ በደካማ ጐኑ ገብተው አፉን እንደሸበቡት ተረዳ። ያስገረመው ሕፃን መሳይ አስተሳሰቡ ነበር። መንፈስ ይመጣብሃል እያሉ ፍርሃት ለቅቀውበታል። ፈገግ ብሎ አሰበ።

"ለመንፈስ ነው ጎራዴውን የሠራኸው?"

"እንደዚያ እያሉ ነው ያሠሩኝ። ከአሁን በፊት የሠራኋቸውን ጌጣጌጦችም ለሱ እንደ ነበር ነግረውኛል።"

"መንፈሱ የት እንደሚገኝ ታውቃለህ?" መርማሪው ከተቀመጠበት በዝግታ ከተነሳ በኋላ ተመልሶ ተቀመጠ።

"አላውቅም። በአዲስ አበባ እንደሆነ ተነግሮኛል።"

"የመንፈሱን ስም ታውቃለህ? የተለየ ስም አለው?" አለ መርማሪው።

"የጠረፉ ንጉስ" ተብሎ እንደሚጠራ ተነግሮኛል። በምሠራቸው እቃዎችም ላይ በአጽሮተ ተጽፎ ይገኛል።" አንጥረኛው የመንፈሱን ስም ሲጠራ ውስጡን የሆነ ነገር ሲረበሽ ታወቀው።

"የጠረፉ ንጉስ አልከኝ?" መርማሪው ቃሉን ደገመለት።

"የጠረፉ ንጉስ።" ሲል አንጥረኛው አረጋገጠለት።

"ፈረንጁም እያገለገለ ያለው እሱኑ ነው እያልከኝ ነው?" በአግራሞት ጠየቀው።

"እንደዚያ ነው። በርግጥ ፈረንጁ ይሄ ብቻ አይደለም። ብዙ የሩቅ ምስራቅ ሰዎችም እየታዘዙ ናቸው እየተባለ ነው የሚወራው።"

"አልገባኝም።" መንፈሱ ሁሉንም እንደሚያዝ አንተም ታውቃለህ ማለት ነው?" ሲል ጠየቀው።

"በተራራው ላይ የሚኖረውን ሽማግሌ የጦር መኮንን የሚያገለግለው ለጠረፉ ንጉስ እንደ ሆነና ለዚህ ግልጋሎቱም በርከት ያለ ክፍያ እየተቸረው እንደሚኖር ነው የነገረኝ። የምሠራውን በእምነትና በፍርሃት መሥራት እንዳለብኝ ነግሮኛል። እንደሚለው ከሆነ መንፈሱ ሁሉንም ነገር ያውቃል።"

መርማሪው ትንሽ ማሰብ ነበረበት። ከሌላ አቅጣጫ የተለየ መስመር እየታየው ነው። ከተራራው ላይ የሚኖረውን የጦር መኮንን በልቡ እየደጋገመ አሰበው።

"ከተራራው ላይ የሚኖረው የጦር መኮንን አሁንም በዚያው ነው? ስለሱ ብዙ ነገር አልጠየቅሁህም።"

"በዚያ ጫካ ከአራዊቶች ጋር ብቻውን ይኖራል።" አለ ገብረክርስቶስ።

"ብቻውን እንደሚኖር በምን አወቅህ?"

"እራሱ ነግሮኛል።" አለውና በረጅሙ ተንፍሶ የነገረውን ለማስታወስ ሞከረ።

"የወርቅ ጕራጼውን በምትሠራበት ወቅት ነው የነገረህ?"

"በዚያን ወቅት ነው የነገረኝ።"

"ስለ ሌላስ ምን የነገረህ ነገር አለ?" ለማስታወስ እየሞከረ።

"ብዙ ነገሮችን ይነግረኝ ነበር።" አለውና ለማሰብ ዓይኖቹን ከደነ።

የሰማውን ካልሰማው እየደባለቀ በጉደለ ራሱ እየሞላ ሲናዘዝበት ዘሩባቤልና ሴቷ በመቅረጸድምጽ እየቀዱት ነበር። አንጥረኛው ውስጡ የነበረውን አሟጥጦ የጨረሰው እኩለ ሌሊት ተገባድዶ መንፈቀ ሌሊት ከአለፈ በኋላ ነበር።





# ምእራፍ አሥር

ከአዲስ አበባ ከተማ በስተሰሜን አቅጣጫ ከተራራው ጫፍ በአንድ አነስተኛ የቆርቆሮ ክዳን ቤት ውስጥ የሚኖረው የጦር መኮንን ብቻውን ነው። ሰፍራው ከእንግሊዝ ቆንስላ ጽሕፈት ቤት አናት የሚገኝ ሲሆን በጥቅጥቅ ደን ተውጦ ይገኛል።

ዳገቱን ወጥቶ ከመጨረሱ በፊት ከመኪናው ሲወርድ በምእራብ በኩል ያለው ቀይ ደመና እየሳሳ ቀኑ መሽቶ ነበር። ከተለያዩ ነፍሳትና ከአውሬዎች ጩኸት በቀር የሚሰማ ድምጽ አልነበረም። በስተምእራብ በኩል በአለው ተራራማ ጫካ ውስጥም የበርካታ ጅቦችና የቀበሮዎች ጩኸት ይሰማል።

ቀበሮዎቹና ጅቦቹ በአንድ ነገር ላይ ጠብ ሳይገጥሙ አልቀሩም ሲል አሰበ ዘሩባቤል። ጸባቸው እየከረረ ጩኸታቸው እየጨመረ መጥቷል። የዝንጀሮና የተኩላዎቹ ጫጫታም እንደዚሁ ጸጥታ የነገሠበትን ጫካ እየበጠበጠው ነው። ተፈጥሮ ከውስጧ ባሉት ፍጥረታት የራሷን ትእይንት ጀምራለች። ለጠባቸው ምክንያት የሆነው የሞተ እንስሳ ሊሆን ይችላል የሚል ግምት ሰጠ ለራሱ።

የጅብና የቀበሮዎች ጠብ የሚፈጠረው በሞተ ነገር ላይ ሲገናኙ የይገባኛል ጥያቄ በሚያነሱበት ወቅት ነው። ተራራውን ጨርሶ ከረባዳው ሰፍራ ደርሷል። የእንቁራሪቶች ጩኸት አካባቢውን የሟርት መንደር አስመስሎታል። በርጥበት በተሸፈነው ጠባብ የእግር መንገድ ወደ ሽማግሌው የጦር መኮንን መኖሪያ ቤት በሚጓዝበት ወቅት በቅርብ ሰዓት ያለፈ የእግር ኮቴ መሄዱን ተረዳ። ተጨማሪ ሰው አለ ማለት ነው። በአጥሩ ተንጠልጥሎ ወደ ውስጥ ከገባ በኃላ ወደ ግድግዳው ተጠግቶ አደመጠ። በትንሹ የተከፈተ የቴሌቪዥን ስርጭት እየተላለፈ ነው። መብራት ግን አይታይም። ምናልባትም መብራቱን አጥፍቶ በቲቪው ብርሃን ብቻ እየተጠቀመ እግሩን አንፈራጥጦ እሳት እየሞቀ ሊሆን ይችላል ሲል አሰበ ዘሩባቤል።

በሩን ሲያንኳኳው ከውስጥ ይሰማ የነበረው የቲቪ ድምጽ ተቋረጠና ሁሉም ነገር ጸጥ አለ። በድጋሚ አንኳኳው። በጸጥታው መካከል የሰው ኮቴ ወደ በሩ ሲመጣ የሰማ መሰለው። ትክክል ነበር። የግዙፍ ሰው ከባድ ርምጃ ወደ በሩ እየቀረበ ነው። ግዙፍ ሰው እበሩ አጠገብ ሲደርስ ኮቴው ጠፋና ሕይወት አልባ ጸጥታ ሆነ። ደገመና አንኳኳ። ጠንከር ያለ ድምጽ አስገመገመ። የተረጋጋ የሚመስል ድምጽ። መርማሪው ልቡ እንደመረበሽ አለበት። ሆኖም አልበረገገም ነበር።

"ማነህ! ምን ትፈልጋለህ?" እርጋታ የተላበሰና ጠንከር ያለውን ድምጽ ሲሰማ መርማሪው ጠቅላላ ሰውነቱን `ኤሌክትሪክ የጨበጠ ያህል ንዝረት ተሰማው።

"እኔ ነኝ። መልእክት አለኝ። ከጠረፉ ንጉሣችን።"
ባጠናው መሠረት መልስ ሰጠውና የሚከተለውን ለመጠበቅ ተዘጋጀ።

በግማሽ በተከፈተው በር ትከሻውን ሰግደድ አድርጎ ብቅ አለ ሽማግሌው የጦር መኮንን። ከውጭ የቆመው ሰው አንድ ብቻውን ያለውን ሰው ተመለከተው። ስለሆነ ብዙ የተጨነቀ አይመስልም። ከአድማስ ጠርዝ ላይ በምትገኘው የጨረቃ ብርሃን ትኩር ብሎ ተመለከተውና ሽጉጥ በጨበጠበት እጁ እንዲገባ ጋበዘው።

ወደ ውስጥ ሲገባ በሙቀት የታመቀ አየር ስለተቀበለው በቅዝቃዜ ለተኮማተረው ሰውነቱ አንዳች አይነት ስሜት ሰጠው። ክፍሉ በደብዛዛው ብርሃን የተዋጠ ነበር። ቲቪው በሚረጨው ብርሃን ሁሉንም ነገር ለይቶ ለማየት አመቺ ባለ መሆኑ የሽማግሌውን መልክ ለማየት አልቻለም። በሩን ዘግቶ በሚመለስበት ሰዓትም እንደ ቆመ ነበር።

በበርሜል ቂጥ ላይ የተገፋፈጠው ጉምድማጅ እንጨት ተንተርክኮ የእሳተ ጎመራ ፍንጣሪ መስኋል። በሌላኛው ጥግ በኩል ከሶፋው ትይዩ በተቀመጠው ቴሌቪዥን የቢቢሲ ዜና በአንዲት ሴትና ወንድ የዕለቱ የዓለም ዜና እየተተነተነ ነው። የጦር መኮንኑ ወደ ሶፋው ከመመለሱ በፊት ከበሩ አጠገብ የነበረውን ማብሪያ ሲጫነው ድባቡ ውጦት የነበረው ሳሎን የብርሃን ኩሬ ለብሶ ሁሉም ነገር በድምቀት መታየት ጀመረ።

ሽማግሌውን የጦር መኮንን በደንብ አድርጎ አስተዋለው። የሰውነቱ ግዝፈት ከመረጋጋቱ ጋር ተደማምሮ የፈጠረው ግርማ ሞገሱ ሳይሆን አይቀርም ልቡን ሲያሸብረውና እጁን ሲያልበው ታወቀው። በአሁኑ ሰዓት እንደዚህ ያለ ስሜት ጥሩ አይደለም። መቁረጥና መጋፈጥ አለብህ መርማሪው ራሱን አስጠነቀቀ። ሽማግሌው ወደ መቀመጫው ከመመለሱ በፊት ከቲቪው አጠገብ ወደ ቆመች አነስተኛ ፍሪጅ እየተራመደ ምን እንደሚፈልግ እንግዳውን ጠየቀው።

"ቢራ ይሁንልኝ።" ሲል መለሰለት።

ቅዝቃዜው ለቢራ መጠጥ ተስማሚ አልነበረም። በምርጫው እራሱን ታዝቦ እስከሚጨርስ የጦር መኮንኑ ምርጫውን እንዲያስተካክል ጠየቀው።

"አልኮል አይሻልህም? ይበርዳል እኮ።" ቢራውን ይዞ ከመመለሱ በፊት አስመረጠው።

"ምን ይገኛል?" አለው ለመረጋጋት እየሞከረ።

"የፈለግኸው አይጠፋም።" ሳቅ ብሎ ተመለከተው። ሽማግሌው።

"ከተገኘ ውስኪ ምርጫዬ ነው።"

ሽማግሌው የጦር መኮንን ከፍሪጁ አጠገብ የነበረች አነስተኛ ሼልፍ ከፈተና ከአንገቱ አካባቢ ውኃው ዝቅ ብሎ የሚታየውን የውስኪ ጠርሙስ ከሁለት ብርጭቆ ጋር ይዞ ተመለሰና እንግዳው አጠገብ ካለው አነስተኛ





ጠረጴዛ ላይ እያስተካከለ "በረዶ ይሻልሃል አምቦ ውኃ" ሲል ፈቃዱን ጠየቀው።

"በረዶ ይሁንልኝ።" መርማሪው ሰውነቱን በመንጠራራት አፍታታው።

በረዶውን ይዞ መጣና በግማሽ ከተቀዳው የውስኪ ውኃ ውስጥ በሚጨምርበት ሰዓት በእጅጌ ጉርድ ሸሚዝ የተጋለጠውን ጠንካራ እጁን በደንብ ለማየት ቻለ መርማሪው።

ሦስተኛውን ብርጭቆ እስከ ጨለጠበት ጊዜ ድረስ ውይይታቸው ፍፁም የተረጋጋና በመግባባት ላይ የተመሰረተ ሆኖ ነበር የቆየው።

"ስም አልተዋወቅንም" አለው የጦር መኮንኑ።"

"ዘሩባቤል እባላለሁ።"

"እኔም አፈወርቅ እባላለሁ። የቀድሞው መንግሥት የጦር መኮንን አባል ነበርሁ።"

"እኔም የአሁኑ መንግሥት የጸጥታ ሠራተኛ ነበርሁ።"

ሁሉም ነገር ተለወጠና ከተቀመጠበት እየተዝናና ተነስቶ አሸቀልቁሎ መርማሪውን ተመለከተው ሽማግሌው የጦር መኮንን።

"ለትንሽ ጊዜ ተለይቼህ ወደ ውስጥ ልገባ ነው። የማስተካክላቸው ትንሽ ሥራዎች ስላሉኝ እባክህ ለተወሰኑ ደቂቃዎች ከመጠጡ እየተጎነጨህ ጠብቀኝ።" መልስ ሳይጠብቅ ወደ ፊት ተራመደ ሽማግሌው።

ጨዋታው መጀመር ያለበት አሁን መሆን አለበት። ለሁሉም ጊዜ አለው ለመጫወት ጭዋታውን የመጀመርያ ጊዜ አለው። እናም ጊዜው አሁን ነው። እጁን ወደ ጃኬቱ ስር አሳልፎ ከቀበቶው ላይ የነበረውን አውቶማቲክ ሽጉጥ በተቀላጠፈ ፍጥነት አውጥቶ ከማጅራቱ ላይ ሲደግንበት እርምጃውን አቁሞ በመገረም አሰበ ሽማግሌው የጦር መኮንን።

"ምን እያደረግህ ነው? እየስከርክ መሆኑ መሰለኝ።" ድምጹ ብቻ ሳይሆን ጠቅላላ እንቅስቃሴው ሁሉ ፍጹም የተረጋጋ ነበር።

"አልሰከርኩም። እንደዚያ የምታስብ ከሆነ ስህተት ነው። ምንም ዓይነት እንቅስቃሴ ብታደርግ እንደምገድልህ ይግባህ። የምትንቀሳቀስ ከሆነ ምላጩን እስበዋለሁ።" መርማሪው ክፉኛ አስጠነቀቀው።

ሽማግሌው የጦር መኮንን ትንሽ ያመነታ መሰለ። ከአንገቱ ላይ ያረፈው የሽጉጥ አፈሙዝ እንቅስቃሴ ቢያደርግ ደንደሱን ቀንጥሶ ሊጥልለት እንደሚችል ያምናል። ይህንን ወፈፌ በእልህ መጋፈጥ የለበትም። ከወፈፌዎች ጋር የሚደረግ ድርድር ጥንቃቄን የሚጠይቅ ነው። ትንሽ ስህተት ሕይወትን ሙሉ ያሳጣል። ያለምንም ጥርጥር ስህተት ተፈጥሯል።

"ፊቴን እንድመልስ ፍቀድልኝ።" አላስጨረሰውም።

"ማንኛውም ነገር የሚከናወነው በአንተ ጥያቄ ሳይሆን በእኔ ትእዛዝ ብቻ ነው። ጥያቄ አልቀበልም። እጅህን ከፍ አድርግና ወለሉ ላይ ተንበርከክ" ሽማግሌው የተባለውን አደረገ።

"ምን እየሠራህ እንደ ሆነ በትክክል..." በድጋሚ አቋረጠው፡፡

"ኧ. . . ኧ. . .ሽ ገና አልተፈቀደልህም፡፡ እኔ የምጠይቅህን ከመመለስ በቀር ምንም ዓይነት ጥያቄም ሆነ ማብራሪያ መስጠት የተከለከለ ነው፡፡ እጅህን በደንብ ከፍ አድርግ፡፡"

የጦር መኮንኑ የተባለውን እና የሚካሄደውን ሁሉ መቃወም አልፈለገም "የሚያስደስትህ ከሆነ አደርጋለሁ" እጁን ሽቅብ ሰቀለለት፡፡

"ሽጉጥክን መውሰድ አለብኝ፡፡"

ያለ ተቃውሞ ፈቀደለት፡፡ የዚህ ዓይነት መግባባት እንደሚፈጠር ይጠብቅ ስለ ነበር አልተገረመም፡፡ የሰለጠኑ ወታደሮች መሸነፋቸውን ከተረዱ በመንገታገት የሚገኝ አሸናፊነት አለ ብለው አያምኑም፡፡

"እጅህን በካቴና እንዳስገባው ወደ ኂላህ መልስ" የተባለውን አደረገ፡፡

"ከአንተ ዕድሜ በእጥፍ ለሚበልጥ ሽማግሌ ካቴና ማጥለቁ ለምን ያስፈልጋል..."አላስጨረሰውም፡፡

"የመናገር መአቀቡን አላነሳሁም፡፡"

ድርጊቱ ቢያበሳጨውም አልተቃወመም፡፡ ተሸናፊነቱን አውቆ እጁን ለምርኮ መዘርጋት ከሰለጠኑ ወታደሮች የሚጠበቅ ስለሆነ የሽማግሌው ትህትና ለደኅንነቱ ብዙም ያስገረመው አልነበረም፡፡ በወጥመድ እንደተያዘች ወፍ አድፍጠው ጥበብ በተመላበት ሁኔታ የማምለጫ ቀዳዳ እንደሚፈልጉም ያምናል፡፡

በአልሸነፍም ባይነት እየተንገታገቱ የሕይወታቸውን ክር ለመበጠስ አይጣደፉም፡፡ በሰኮንዶች ልዩነት የተሳበ የመሣሪያ ምላጭ ረጅሙን ሕይወት ያሳጥራል፡፡ በደቂቃዎችም እንዲሁ ብዙ ነገር ይለወጣል፡፡ የሰኮንዶች ሽርፍራፊ ለመኖርም ሆነ ላለመኖር ወሳኝነት እንዳላቸው ያለፈበት ሙያው ብዙ አስተምሮታል፡፡ ያለ መንገታገት የተባለውን ሁሉ መፈጸም መቻሉ አላስደነቀውም፡፡

ካቴናውን አጥልቆለት ከወንበሩ ላይ እንዲቀመጥ ፈቀደለት፡፡

"ያለ መነፅር ማንበብ ትችላለህ?" የጸጥታ ሠራተኛው ትህትና በሚመስል የድምጽ ቅላፄ እየጠየቀው በግራ እጁ ብርጭቆውን አንስቶ ከውስኪው ተጐነጨለት፡፡ ፡፡

በአወንታ እራሱን ከፍ ዝቅ አደረገና "እነባለሁ" ሲል መለሰለት፡፡ "የደህንነት ሠራተኛ ነህ" እንደ ተረጋጋ ሲመልስለት መርማሪው ተደነቀ፡፡

ጎልማሳው እራሱን አወዛወዘ "ትክክል ነህ የሕዝብ ደኅንነት ሠራተኛ ነኝ፡፡"

"ጥፋተኛ አይደለሁም ብዬ ልነግርህ አልችልም፡፡ ነገር ግን ለጥፋቴ ምክንያት ነበረኝ፡፡"

"ከምጠይቅህ ውጭ እንዳትናገር አስጠንቅቄህ ነበር፡፡ ይህንን





እያስታወስህ የምትጠየቀውን ብቻ መልስ" ድምጹ ብዙም በቁጣ የታጀበ አልነበረም፡፡

"እታዘዛለሁ ክቡር ደኅንነት፡፡"

በማፌዙ አልተከፋም፡፡ በድንገት ስሜቱ ሲቀዘቅዝ ሲመለከት ተስፋ እየቆረጠ መሆኑ ተሰማው፡፡

"ከማድረግ በቀር ሌላ አማራጭ የለህም፡፡ በሕይወት ለመቀጠል እያንዳንዷ ደቂቃ የምትወሰነው አንተ በምታደርገው እንቅስቃሴ ብቻ ነው፡፡"

"እያስፈራራህ ልታሽቆጠቁጠኝ አትድፈር፡፡ ከፈለግህም ተኩሰህ መግደል ትችላለህ" በተቀመጠበት እየተወራጨ ሽቅብ አስተዋለው፡፡

"ኧ-ኧኧ..." ሽጉጡን ከፍ አደረገ፡፡ "እንደዚያ ማድረግ የለብህም፡፡ በፍጹም እንደሱ አታስብ፡፡ "በቢላዋ ቀልድ ይቅር አለች ዶሮ" አሉ ጋሼ እንትና፡፡ ሽጉጤ የተቀባበለ ነው፡፡"

"ስሜቴን እየተጫንከኝ የምታስቸግረኝ ከሆነ ያለኝ ምርጫ መናገር መሆኑን እወቅልኝ፡፡" በሚችለው ሊያስጠነቅቀው ሞከረ፡፡

"ነገሮችን የማታወሳስብ ከሆነ ፡፡"

"ማወሳሰብ ምንድነው?" ከበረዶ በቀዘቀዘ ስሜት ጠየቀው፡፡

መርማሪው አሰበ፡፡ እንዳለውም ሽማግሌው ተስፋ እየቆረጠ ከሆነ የነገሩ ውል መልሶ መጥፋቱ የማይቀር ነው፡፡ ያ ከመሆኑ በፊት በትዕግሥት ማነጋገር አለበት፡፡

"የሚያውቁትን በትክክል ባለመመለስ ማደናገር ማወሳሰብ ይባላል፡፡"

"የምንግባባ አይመስለኝም፡፡"

መርማሪው ዓይኑን ወደ ጓዳ ከሚያስገባው በር ላይ ለሴኮንድ ወርወር አደረገና "ሁሉም ነገር ላይ ከፍተኛ ስህተት የሠራህ ሰው ነህ" አለው፡፡

"ምንድነው ስህተቱ ገንዘብ ለማግኘት መጣሬ? ዕድሜዬን ሙሉ ተንከራትቼ አገሬ ለኔ የሠራችው ምንም መልካም ነገር እንደሌለ ተረድቻለሁ፡፡ ስለአደረገችልኝ ውለታዋ ምንም የማውቀው አለዚያም የማስታውሰው መልካም ነገር የለም" ይህንን ሲናገር ፊቱ እየጨፈገገ ነበር፡፡

"አንተስ ለአገርህ ምን ሠራህላትና ነው የምታማርራት? መቀባጠርክን ተውና ስለ አደገኛው የዘራፊ ቡድናችሁ አጠቃላይ ሁኔታ ንገረኝ፡፡" ዘሩባቤል ደሙ መፍላት ጀመረ፡፡

እራሱን በኃይል ነቀነቀ አዛውንቱ የጦር መኮንን "ስለ የትኛው ዘራፊ?"

"ስለ ዘራፊው ቡድናችሁ አጠቃላይ እንቅስቃሴ ነው የምጠይቅህ፡፡"

በዝምታ ተዋጠና ከፊት ለፊት የተቀመጠውን የመረጃ ሰው ተመለከተው፡፡ በመካከላቸው ያለውን አለመግባባት እያጠናከረው ለመሄድ የቆረጠ ይመስላል በተቀመጠበት እንደ መቁነጥነጥ እየከጀለው ነበር፡፡

"ትሰማኛለህ?" ሲል ጀመረ፡፡ የጦር መኮንኑ "ስለዚህ ቡድን ለማወቅ

የምትፈልገው እውን ለሀገርህ ተቆርቁረህ ነው? በፍጹም እንደዚያ አይመስለኝም። ጥቅማቸውን ከሚያሳድዱ አስመሳዮች አንዱ ልትሆን እንደምትችል እገምታለሁ። ሕግን እንደ መሣሪያ በመጠቀም እያስገደዱ የሚዘርፉ አስመሳዮች ተበራክተዋል። የምትሠሩት የበቀል ሥራ ነው። ወንጀለኞች ሆናችሁ ሌላውን ወንጀለኛ ትላላችሁ። እየዘረፋችሁ ሌላውን ዘራፊ ትላላችሁ። እንድትገድሉ እና እንድትዘርፉ የፈቀዳላችሁ ማን ነው። እራሳችሁ ለራሳችሁ ሁሉንም የማድረግ መብት የሰጣችሁ ወንጀለኛ ስለሆናችሁ ለጥፋታችሁ ጠያቂ የሌላችሁ ሕጋዊ ወንጀለኞች መሆናችሁን እነግርሃለሁ። ይህንን አንተም እኔም እናውቃለን ጠያቂ ስለሌላችሁም ለእናንተ ያልተመቻችሁን እያሳደዳችሁ ትፈጃላችሁ። ከተስማማችሁ ጋር ትዘርፋላችሁ። በሁለትና በሦስት ተከፋፍላችሁ ይህችን አገር እንደ ጭራቅ ስትበጫጭቋት ዝም ብዬ ከምመለከት የድርሻዬን ልወስድ ብዬ ነው ወደዚህ ተግባር የገባሁት። አንተም ከአንደኛው ቡድን ተገንጥለህ የወጣህ በመሆንህ የቋመጥክበትን ሀብት ለመዝረፍ እኔን አታልለህ ያዝህ።

የሕግ አካል ነኝ እያልክ ስትመጻደቅ ምን ያህል እንደምበሽቅ ታውቃለህ? በጫካ ለመኖር የፈቀድኩት የናንተን የማታለልና የውሸት ክርፋት ሽሽት ነበር። ይህች ሀገር የሚሠራላትን ስለማትወድ እናንተን በእቅፏ ይዛ ንጹኅ ዜጎቿን እያስቃየች ናት። ይህ ሕዝብ ምን ያህል እንደሚጠላችሁ ታውቃለህ? የጭራቅ ያህል ነው የሚጠላችሁና የሚፈራችሁም። እንደ ሾተላይ ነፍሱን ጭምር ለመንጠቅ በዛቻና በማስፈራራት የቀረች ሕይወቱን የስጋትና የጥርጣሬ ታደርጉበታላችሁ። የሀገሪቷንም ሀብትና ጥቅም የምታውሉት የህዝቡን ኑሮ ለመደጎም ሳይሆን እብድ አላማችሁን ለማሳካት ለሚረዳችሁ አካል እጅ መንሻ በመስጠት ነው።"

ከፊቱ ላይ ተፋበትና በእልህ ሲያንኮራፋ ስድቡንም ሆነ ምራቁን በትዕግሥት ተቀብሎ የተፋበትን ምራቅ በሶፍት እየጠራረገ ትኩር ብሎ ተመለከተው። በርግጥም እስከ ወድያኛው ተስፋ ቆርጦ ነበር።

የማይረባ አሳዛኝ ፍጥረት ሆኖም ተሰማው። ለሠራው ጥፋት በእልህ መንገድ መሄዱ ብዙ ርቀት አይወስድም። በመግባባት ነው መቀጠል ያለበት። ከፊቱ ላይ ጠራርጎ ምራቁን ከአጸዳ በኋላም ለብዙ ደቂቃ አሰበ። ከማሳመን ውጭ በኃይል የሚደረግ ማንኛውም ሙከራ ከአንድ የመረጃ ሠራተኛ የሚጠበቅ አይደለም። ያውም ተስፋውን ካሟጠጠ ሽማግሌ ጋር።

"ጭርት እንዳይዘኝ ከመስጋቴ በቀር ምንም ቅሬታ የለኝም። የሠራኸው የማይገባ የወረደ ተግባር በመሆኑ ከአንተ አልጠበቅሁም። ንግግርክም ቢሆን ሥነ-ምግባር ጎድሎታል። የምትላቸው ዓይነት ሰዎችን አይደለሁም። የራሳቸውን ጥቅም ከአገርና ከሕዝብ ያስቀደሙ እንዳሉ ስለማውቅ ለሰነዘርከው አሳብ ቅር አይለኝም። ይህ እውነት ነው።"





"በምን እርግጠኛ መሆን ይቻላል?" ሽማግሌው የጦር መኮንን ብርጭቆውንና መርማሪውን ተራ በተራ እየተመለከተ ጠየቀው።

"አንተ በምትገምታቸው አካላት ውስጥ እንደሌለሁበት ግን እነግርሃለሁ።"

"እነሱነታቸውን ነዋይ ከሰወረባቸው ወፈፌዎች መካከል ላትኖርበት ከቻልክ እግዚአብሔር በታምሩ የመረጠህ ዕድለኛ ሰው መሆን አለብህ።"

"ግንዛቤህ የተሳሰተ ስለሆነ ሰርዘው። እያደንሁ ያለሁት እውነተኛዎቹን ወንጀለኞች ብቻ ሳይሆን አንተ የምትላቸውን አስመሳይ ጭራቆችንም ጭምር ነው። አንድ ቀን ለፍርድ እንደማቀርባቸው አምናለሁ። በርግጥ የውስጥ ጦርነት የተወሳሰበ ስለሆነ ንጹትን ከመጥፎ ለይቶ ለመምታት ይከብዳል። ሆኖም አንድ ቀን ተለይተው ይመታሉ።"

ከብርጭቆው የቀረችውን ጭላጭ ተመለከታት። የምታረካው አልነበረችም።

ፊቱን በጥንቃቄ ሲመለከተው ቆይቶ "ጥሩ ሕልመኛ ትመስላለህ። ሆኖም ሕልምህ ከሕልምነት የዘለለ አይደለም። በርግጥም የምትመኘው ሁሉ እውነትክን ከሆነ ከማትወጣበት አረንቋ ውስጥ እግርህን እየመሰግህ ስለሆነ ወፈፌዎቹ እነሱ ሳይሆኑ አንተ እራስህ መሆን አለብህ።" ሲል መለሰለት።

"እንዳልከው እብዶች መካከል ጤነኛ ሰው ቢገኝ እብዱ እሱ መሆን እንዳለበት አምናለሁ።" የጸጥታ ሠራተኛው ያለውን ያለተቃውሞ መቀበሉን አረጋገጠለት።

"ለብቻህ ማበዱን የመረጥከው ለምን ይሆን? ይህ ሁኔታ አስገራሚና አስቸጋሪው የታሪክህ ክስተት ሆኖ ማለፉን መገመት ነበረብህ። ለምንድነው የማታገላብጠውን ቋጥኝ ለመፈንቀል የምትታገለው? ለምታደርገውስ ጥረት ውለታህን ሊሰጥህ የሚችለው ማነው?"

"የራሴ ኃላፊነት አለብኝ።"

"እውነተኛ ብትሆንና ላምንህ ብችል አብሬህ በሠራሁ በተደሰትሁም ነበር። አንተ የምትለውን ዓይነት ሰው በዕድሜዬ የመጨረሻ ምእራፍ ላይ ባገኝም ለኔ እንደ ተአምር ነው የምወስደው።"

"ብትጠረጥረኝ አልፈርድብህም።" አለው ዘሩባቤል።

"የኔን በዚህ መኖር የነገረህ ማነው?" ሲል ጠየቀው።

"ጎራዴ የሠራው አንጥረኛ ነው።"

"ይዘኸዋል ማለት ነው?" ቀና ብሎ ፊቱን ተመለከተው።

"ትናንትና ምሽት ላይ ይዤዋለሁ።"

"አሁን የት ነው ያለው?" ሲል በጥርጥር አስተዋለው።

"ምርመራ እየተደረገለት ነው።"

"ወደ ገሃነሙ ድርጅት የሚያስገባውን መንገድ አልጠቆመህም።"

"ምንም የነገረኝ የተጨበጠ ነገር የለም።"

"እኔ ብነግርህ ደፍረህ የምትሞክረው ይመስልሃል?።"

"እኔም የምፈልገው እሱን እንድትነግረኝ ነው።"

"ልነግርህ የምችል ይመስለኛል። ያም ሆኖ አላምንብህም።" አለውና ራሱን ነቀነቀ።

"ለምንድን ነው የማታምነብኝ?" በጥንቃቄ አስተዋለው ዘሩባቤል።

"እምነት የምጥልብህ አይመስለኝም።" ሲል መለሰለት።

"የገሃነሙን በር ማግኘት እንድችል ብትተባበረኝ ነፃ እለቅሃለሁ።"

"ገሃነም እኮ ያስፈራል። ስለ ገሃነሙ ውስጠ ምሥጢር አንጥረኛው ነግሮህ ነበር እንዴ?" የምጸት ፈገግታ ጋበዘው።

"ነግሮኛል። እነኛን የሳጥናኤል ደቀመዝሙሮች በአካል ለማየት ጓጉቻለሁ። ሁሉንም ሰይጣኖች እንዳያቸው ወደነሱ የሚያደርሰኝን መንገድ ልትጠቁመኝ ይገባሃል። አንጥረኛው ሲነግረኝ በጣም ነው የተበሳጨሁት።" ጠጋ ብሎ የሸማግሌውን ትከሻ ያዝ አደረገው።

"ብታምነኝ ደስ ባለኝ ነበር። የምትለው ሁሉ በአስገዳጅነት ሳይሆን በመግባባት የሚሠራ ነው። እመነኝና የታሰርኩበትን ካቴና አውልቅልኝ አንተን መቋቋም የማልችል ሽማግሌ መሆኔን ተረድተህ እጄን ነጻ አድርገህ መነጋገር ይኖርብናል።"

"የምትለኝን መቀበል ከባድ ፈተና ነው። የአንተን እጅ ከሰንሰለቱ ነጻ ማድረግ ሌላ ፈተናና እብደት ነው።"

"በአንተ ቦታ ብሆን የሚሰማኝ ተመሳሳይ ነው። ያም ሆኖ በዕድሜ የገፋሁ በመሆኔ አንተን ለመቋቋም ይከብደኛል። እጄ ላይ ያጠለቅኸውን ካቴና አውጣልኝና ሕልውናዬ ነጻ ወጥቶ እናውራ።"

ይህ ጥያቄ በፍጹም ሊሞከር የማይቻል ነበር። መርማሪውን እየተፈታተነው ነው ያለው። ቢሸመግልም ወታደር ነው። ይህ የሞኞች ጨዋታ የሚመስል ቀልድ ነው። እራሱን አወዛወዘ።

"በዚሁ ሁኔታ ትቆያለህ።"

"አንተም መረጃ እንድሰጥህ አትጠይቀኝ።"

"የምታቀርበውን መደራደርያ አልስማማበትም። በምትለው ወዳጅነት ለመቀጠል የምፈልገው መረጃ መቅደሙ አስፈላጊ ነው።"

የመረጃ መኮንኑ ከውጭ በኩል የሰው ኮቴ የሰማ መሰለውና አደመጠ።

"የሚመጣ ሰው ነበር እንዴ?" ወደ ጆሮው ተጠግቶ ጠየቀው።

"አልፎ አልፎ እየመጡ ይጎበኙኛል።"

"ለምን አልነገርከኝም ነበር?" ኮስተር ብሎ ጠየቀው። ዘሩባቤል።

"የማውቀው ነገር አልነበረም። ሰዎቹ በፈለጉበት ሰዓት ነው የሚመጡት።"

"የዛሬው አመጣጣቸው የተለመደ ነው? ማለቴ ሁሌም በድንገት እየመጡ የሚጉበኙህ በምሽት ነው?"





"አልፎ አልፎ እንደዚያ ያደርጋሉ።"

"ለምን አልነገርከኝም ታዲያ?" በጥርሶቹ መካከል በድጋሚ ጠየቀውና ጩኸት እንዳያሰማ በእጁ ምልክት አስጠነቀቀው።

"እኔን የሚያሳስብ ነበር እንዴ?"

አዛውንቱ የጦር መኮንን የሰጠው መልስ ትክክል መሆኑን አምኗል።

"በሞኛ ሞኝ ጥያቄዬ ሳትደነቅ ብትቀር ነበር መገረም የነበረብኝ። በጓሮ በኩል በር አለ ወይስ የለም?" ሽጉጡን ወዳፉ እያቀረበ ጠየቀው።

"ምን አልከኝ?" አንገቱን ወደ ጉን ዘንበል አደረገ ሽማግሌው።

"የአደጋ ጊዜ መውጭያ የለም ወይ?" አፈጠጠበት።

"መውጣት ፈለግህ እንዴ?" ትኩር ብሎ እየተመለከተ ጠየቀው።

"ብቻዬን አይደለም የምወጣው። ቅደምና ምራኝ።" ሸሚዙን ይዞ ሸቅብ ሳበውና ከቅምጡ አነሳው።

"እጁን ፍታኝ ..." አላስጨረሰውም።

"እገድልሃለሁ" ሽጉጡን ወደ አፉ የበለጠ አቀረበው።

"አስፈላጊ ነው እንዴ?" ትከሻውን ነቅነቅ አደረገው ሽማግሌው።

"አታሹፍ አንተ ጩርሟሳ።" ሽጉጡን ወደ ግንባሩ ከፍ አደረገበት።

"እኔን ማጣታቸው ለመረጃ ሥራህ ጥሩ አይደለም። ትተኸኝ ውጣ።"

"ሊያሳስብህ አይገባም።" ወደ ጓዳው አቅጣጫ ገፋው።

የኊሊት ተጠፍሮ እንደ ታሰረ ወደ ውስጠኛው በር እየመራ ወሰደው። የአደጋ መውጫው በር የተዘጋው በትልቅ ግንድ ተደግፎ ነበር።

በተጠቀጠቀው ጫካ ውስጥ ለብዙ ደቂቃዎች ከተጓዙ በኋላ ወደ መንገዷ አቅጣጫ ተመለሱ። ሽማግሌው በጫካው ሲሹለከለክ እንደ ለማዳ ውሻ ነበር።

መኪናውን ያቆማት ከመንገዱ ገባ ብሎ ከደኖች መካከል ቢሆንም በጨረቃዋ ብርሃን እየተመሩ ከቆመችበት ስፍራ ያለ ችግር ደረሱ። የመገፍተር ያህል ከመኪናዋ ውስጥ አስገብቶት ሞተሩን አስነሳና ወደ ቀጭኗ ጎዳና ወጡ። በውኃ የተበላው መንገድ ለመኪናዋ ተስማሚ አልነበረም። የመኪናዋ ፍጥነት ከሚገባው በላይ ስለ ነበር እየሸሸ ገደል ገብቶ መሞትን እንደ ምርጫ ወስዶታል ማለት ነው" ሲል አሰበ ሽማግሌው።

እየተነሳች ስትነጥር ዓይኑን ጨፍኖ በስሜት አደመጠ። ቁልቁል እየተንከባለለች ያለችም መሰለው። ከመጠን በላይ እየፈጠነች ነው። ይህ እብድ ምን እየሠራ ነው ያለው? ወደ ገሃነብ ያውርድህ አንተ የማትረባ ከንቱ" በውስጡ አጉተመተመ ሽማግሌው የጦር መኮንን።

# ምእራፍ አሥራ አንድ

“ብዙ አላስቸግርህም ለጓደኛዬ የነገርከውን ያህል ትነግረኛለህ። ስለኔ የተሳሳተ ግምት እንዳይኖርህ። ቀልድና ውሸትን የማልወድ ትሁት ሴት ነኝ” ጨዋታው መጀመሩን ያበሰረችለት የመጀመሪያዋ ወፈፌ ሴት መርማሪ መሆኗ ነው።

“ለእያንዳንዳችሁ ቃል መስጠት አስፈላጊ ነው እንዴ?”

“በጣም አስፈላጊ ነው። ጓደኛዬን ከምጠይቅ ካንተ ብረዳ ጥሩ ግንዛቤን ይፈጥርልኛል። እንዴት ያለሁ ጨዋታ ወዳድ ሴት መሰልኩህ።”

“ስለ የትኛው ነው መገንዘብ የምትፈልጊው?” ቀና ብሎ ፊቷን ተመለከተ።

“ከራስህ አንደበት ሁሉንም ነገር መስማት እፈልጋለሁ።”

እንደ እስክስታ እያደረጋት ከአንገቷ በመጠኑ ተጠጋችው።

“ስለ ራሴ ብትጠይቂኝ ብዙ እነግርሽ ነበር።” መኮንኑ በአጭሩ መመለስ እንዳለበት ተረዳ።

“እሺ. ስለ ራስህ አጫውተኝ። በተራራው ላይ መኖር ከጀመርህ ምን ያህል ዓመታትን አሳልፈሃል?” እንደ ተዋናይ ተውረገረገችበት።

“አሥር ዓመት አልፎኛል።”

“ለምንድነው ከአራዊት ጋር መኖር የመረጥከው? የደረሰብህ ተጽዕኖ አለ እንዴ?”

“የአውሬዎች ጩኸት መስማት ስለሚያስደስተኝ እንጂ ምንም ተጽእኖ አልደረሰብኝም።”

“ከማፍያው ቡድን ጋር የነበረህ ግንኙነት ምን አይነት ነው።”

“የአሽከርና የጌታ ዓይነት ግንኙነት” ትከሻውን እንድማንጠር አድርጐ መለሰላት።

“የቡድኑ መሪ አረብ ነው ብለህ ለጓደኛዬ እንዳጫወትከው ነግሮኝ ነበር።”

“ትክክል ነው የነገረሽ። እንደሱ ብዬዋለሁ።”

“አረቡን በግንባር ቀርበህ አነጋግረኸው በወቅቱ የሰጠህ መመሪያ ካለ እስቲ ንገረኝ?”

በስሜት ስትቅበጠበጥ ሴት አናብስት መሰለችው።

“የተጣለብኝን የሥራ ድርሻ በትጋት መሥራት እንዳለብኝ መመሪያ እንደ ሰጠኝ አስታውሳለሁ።”

“ምን ነበር የሥራ ድርሻህ?” ረጋ ብላ ጠየቀችው።

“በየጊዜው ይለዋወጣል ይህ ነው የሚባል አይደለም።”

“የተሰጠህን ትእዛዝ እንደምትወጣው አምነህ ተቀበልከውና ሥራህን ጀመርክ?”





በአዎንታ እራሱን ነቀነቀ። “የገንዘብ ችግር ስለነበረብኝ አምኜውም ባይሆን ትእዛዙን መቀበል ነበረብኝ።”

“አረቡ ምን ዓይነት ሰው እንደ ሆነ ስእላዊ መረጃ ልትሰጠኝ ትችላለህ?”

የሰውየውን ቅርጽ በዓይነኅሊናው ሲቃኝ ቆይቶ “ተክለ ሰውነቱን ነው የምትጠይቂኝ?” ሲል ጠየቃት።

“ስለ ሁሉም ነገሩ ማወቅ እፈልጋለሁ።”

“ወፍራም ነው ብሎ መናገር የሰውነቱን ቅርጽ ስለማይገልጸው ድቡልቡል ብለው ይሻላል።”

“የወሲብ ጥማተኛ ነው የሚባለውስ?” አለችው።

“ከሁለት ዓመት በፊት እንደ ጐበኘሁት አስጠልቶኝ ነበር።”

“ወደዚህ ቡድን ከተቀላቀልህ ገና ሁለት ዓመትህ ነው?”

“ሁለት ዓመቴ ነው።” ሲል ቃሉን ደገመላት።

“የዚህን ዓይነት ድራማ ስትመለከት ስለ ተሰማህ ስሜት አልጠይቅህም። በአንተም ውስጥ ያለው ወንድነት ተመሳሳይ ነው። ሰውየው ሴቶቹን ከየት ነው የሚያመጣቸው?”

“በየሦስት ቀኑ ሴቶችን ይዘው የመጡት ደላሎች አሉት።”

“የመጀመሪያዎቹ የት ይሄዳሉ?” ትኩር ብላ እየተመለከተች ጠየቀችው።

“የማውቀው ነገር የለም።”

“ከጐበኘትህ በኋላ የተሰጠህ መመሪያ ምን ነበር?”

“ወደ ተሰጠኝ የሥራ ድርሻዬ እንድሄድ ነበር።”

“የተሰጠህ የሥራ ድርሻህ በተራራው ላይ ያለውን ቤት መጠበቅ ነበር?”

“በተራራው ላይ ያለው ቤት የራሴ ነው።”

“የጠረፉ ንጉሥ ከማፍያዎች ጋር ነው የሚሠራው?” አለችው።

“እራሱም ማፍያ ነውኮ።”

“ይኼም ሌላው እብደታችሁ ነው።” አለች።

“እብደት?” አለ ሽማግሌው የጦር መኮንን።

“በቅዠት ውስጥ ያለ እብደት። የሌሎችን ትኩረት ለመሳብ የሚያደርገው ትእይንትም እራሱን የቻለ አንድ እብደት፤ ሌሎችን እንደ እብድ እንዲያስቡ ሳይኮሎጂካላዊ አካሄድ መጠቀም ሌላኛው እብደት ነው። በሁሉም ነገር ላይ የምትጠቀሙት ሳይኮሎጂ እብደትን ነው። እንደምትነግረኝ በብዙ መንገድ አእምሮአችሁን እየነጠቀ ወስዶ በቦታው የእሱን እብድ አስተሳሰብ በመተካት የሱን እብደት እያደነቃችሁና በፍርሃት እሱን እያመለካችሁ እንድትታዘዙት ቀይሯችኋል። ምድራዊ የሳጥናኤል ደቀመዝሙር ብለን ብንጠራው የሚጋነን አይመስለኝም። “የጠረፉ ንጉሥ ነኝ” ሲል እራሱን ሰይሟል፤ ሁለተኛው ምድራዊ የጠረፉ

ሳጥናኤል" በምጸት ፈገግ ብላ የሽማግሌውን ፊት ተመለከተች።

"ከእሱ ጋር የሚሠራ ሰው ስም ልንገርሽ እንዴ?" አላት ሁሉንም ነገር ወደ ጐን ትቶ።

"ከሱ ጋር ሥለ ሚሠራ ሰው?" የጥርጣሬ በሚመስል አኳኋን አስተዋለችው።

"ለምርመራ ስራሽ ሳይጠቅምሽ አይቀርም።"

"እሱም መንፈስ ነኝ የሚል ነው?" ስትል ጠየቀችው።

"አብዛኛዎቹ ከጠረፉ ንጉሥ ጋር የሚገናኙት በእሱ በኩል የሚመጡ ናቸው።"

"አልገባኝም። እንደ ገና ብታብራራልኝ?"

"የነገራት ብዙ የተጨበጠ ስላልነበር በቅሬታ አቋረጠችው።

"በተቻለኝ መጠን ስሜትክን ላለመጉዳት እጠነቀቃለሁ። ግን ውሸት ነው።"

"ስሜቴ ተጎዳ የሚል ቃል አልወጣኝም ብትቀበይም ባትቀበይም . . . " አንጠልጥሎ ተወው።

"ብትልም ምንም አይደለም። ሰው የተሰማውን መግለጽ ወንጀል አይደለም..."። የምጸት ሳቅ ጋበዘችው።

"ወዳጅነታችንን ሊያሻክር የሚችል ቃል አልተናገርሽም።" እሱም በምጸት መለሰላት።

"ብቻህን ለመኖር የወሰንክበትን ምክንያት አልገለጽክልኝም። ከሰው ተነጥለህ መኖር የፈለግኸው ለምንድን ነው?"

"ከወጣትነት ዘመኔ ጀምሬ በበረሃ ስለኖርሁ ይመስለኛል። ከከተማው ሙዚቃና ግርግር የጫካው ጸጥታ ያስደስተኛል።"

"በተራራው ላይ እንድትኖር ያደረገህ ምክንያትህ ይሄ ብቻ ነው?"

"ይሄው ነው።" እሩቅ በሚመስል ድምጽ መለሰላት።

"ከነዚህ ሰዎች በመጀመሪያ ልትገናኝ የቻልከው እንዴት ነበር?"

"በመጀመሪያ የተገናኘሁት ከሳምሶንና ከስምኦን ጋር ነበር።"

"እነሱ ናቸው የመለመሉህ?"

"እንደዚያ ነበር።"

በረጅሙ ተነፈሰችና ከተቀመጠችበት ስትነሳ እሱም በረጅሙ ተነፈሰ።

ኮሎኔል አፈወርቅ የተሰላቸበት ቀንና ሰዓታት ቢኖር ያቀን ብቻ ነበር። ሁሉም ነገር እየከበደው ነው።





# ምእራፍ አሥራ ሁለት

በሀያ ሺህ ካሬ እስኩዌር ሜትር ስፋት ላይ የተገነባው ታላቁ የቦሌ መድሃኒዓለም ቤተ መቅደስ ከዓለም የሦስተኝነት ከአፍሪካ የአንደኛነት ደረጃ ይዟል ተብሎ ተመዝግቧል። የቤተ መቅደሱ ጉልላቶች በከተማዋ በየትኛውም አቅጣጫ ሆኖ ለማየት በሚያስችል ስፍራ ላይ ነው የተገነባው። ቤተ-መቅደሱ ያረፈበት ስፍራ በስተምስራቅ አቅጣጫ ከዓለም አቀፍ አውሮፕላን ጣቢያው በቅርብ ርቀት ላይ የሚገኝ ሲሆን በስተሰሜንና በስተደቡብ የቤተ-መቅደሱን አጥር እያጠበቡ የሚያገናኙ ጐዳናዎች ናቸው። አሥራ አምስት ሚሊዮን ወጥቶበታል የሚባለው የሊቀ ጳጳሱ ኃውልት የሚገኘውም በዚሁ ስፍራ ካለው አደባባይ ሲሆን ቤተ ክርስቲያኖች በመቀደሻ እጣንና ጧፍ እጦት እየተዘጉና ሰው በረሃብ በሚሞትባት እንደ ኢትዮጵያ ባለች ደሀ ሀገር በሕይወት ያለን ሰው ኃውልት ማሠራት ከመንፈሳዊ ሕይወት ውጭ ስለሆነ ይፍረስ ተብሎ ተጠይቆም ነበር።

ይህ ስፍራ የምእመናን መግቢያ ዋናው በር ሆኖ ከመግቢያው በግራ በኩል የቤተ መቅደሱ መገልገያዎች ሁለት መለስተኛ ሕንፃዎች አሉ። ከሁለቱ ሕንፃዎች አንደኛው የመጥምቁ ዮሐንስ የጸበል ቤት ሲሆን የጸበል ቤቱ በሁለት የተከፈለ ሆኖ በስተሰሜን የሴቶች በስተደቡብ ደግሞ የወንዶች መጠመቂያ ስፍራ ነው። አሥራ አምስት ሚሊዮን ዶላር ብዙ ተቋማት ተገንብተው ረዳት ለሌላቸው ወገኖች ቢደረግ የጳጳሱን ክብር ከኃውልቱ በተሻለ ያጉላው ነበር ተብሎ ይታመናል።

ከአራት ሰዓት በኋላ ጸበል ቤቱ ስለሚዘጋ አርፍዶ የመጣ ቢኖር ወደ መጠመቅያው መግባት አይችልም። ከፀበል ቤቱ እስከ ቤተ-መቅደሱ ያለው ረጅምና ሰፊ ቦታ ለመንገድ ተከፍሎ በሸክላ ከተነጠፈው ሰፋፊ የእግረኛ ጎዳና በቀር አብዛኛው ስፍራ በተለያዩ አበባዎችና በሣር የተሸፈነ ነው።

ወደ ቤተ መቅደሱ ሲገባ በምእራብ በኩል ያለውን በር ለመጠቀም ከሰሜን የወንዶች በደቡብ የሴቶች ሆኖ ከቤተ መቅደሱ ዋና በር ፊት ለፊት የሚታየው የቅዱስ ቅዱሳኑ መንበር በመጋረጃ ተከፍሎ የባሻገርን ያህል ይርቃል። የመቅደሱን በር ስፋት እንደ ጠበቀ ወደ መቅደሱ የሚዘልቀው የምእመናኖች መተላለፊያ በርካታ ሰዎችን እንደ ልብ ማስተላለፍ የሚችል ሆኖ የወንድና የሴቶቹን መቆሚያ የከፈለ ነው።

እንደ ሌሎች ቤተ-መቅደሶች የሴትና የወንድ መቆሚያ በመጋረጃ የተከፈለ ስላልሆነ እርስ በርስ ይተያያሉ። ይህ ሥርዓት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ እምነት ዘንድ ያልተለመደ በመሆኑ በመጋረጃ መከፈል ነበረበት የሚል አስተያየት ከመስጠቱ ውጭ ለዚህ ውብ ቤተ-መቅደስ ሌላ ምንም እንከን የሚወጣለት አይደለም ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የእምነት ሥርዓት ከሙሴ ሕግ የተወሰደ በመሆኑ ሴቶች የወር አበባ አይተው ሰባት ቀን ካላለፋቸውና ባልና ሚስትም የግብረ ሥጋ ግንኙነት ፈጽመው ቢያንስ ከሦስት ቀን በፊት ወደ ቤተ-መቅደስ መግባትን ትከለክላለች። እህልና ውኃ ቀምሶ ወደ ቤተ-መቅደስ የመጣ ንጹሕ ቢኖር ከቤተ-መቅደሱ አርባ ሜትር እርቆ ጸሎቱን አድርሶ ወደ መጣበት እንዲመለስ ቤተ ክርስቲያኗ ትምህርት ትሰጣለች።

ፀሐይ ጠልቃ መሬት መደነጋገዝ ጀምሯል። በአንድ ሰባኪ የዕለቱ መንፈሳዊ ትምህርት እየተሰጠ ነው። መኪናው ያለማቋረጥ ወደ ውስጥ ቢገባም የእሱ ሰዎች የሉም። በጠቆረ የክረምት ጨለማ እንደ አልማዝ ስብርባሪ የሚያብለጨልጩትን ከዋክብቶች ሲመለከት ልቡን አንዳች ነገር ሲረብሸው ተሰማው።

አንድ ያለፈ ትዝታ እየቀሰቀሰበት ውስጡ ክፉኛ ታወከበት። በተደበላለቀ ስሜት ፍቅረኛውን ሲያስታውሳት ሰውነቱን የማንቀጥቀጥ ስሜት ተሰማው። ይወዳታል ትወደዋለች። ያፈቅራታል ታፈቅረዋለች። እሷ ለሱ የሁሉም ነገር ንግሥት ናት። ፍቅርን ሰጥታ መቀበል ታውቅበታለች። አልቅሳ ተንሰቅስቃ ከአንጀቱ ትገባለች። ውስጡን እንደ አልቂት እየመገመገች እንደ ምስጥ ትበረብረዋለች። እንደ ሽክላ ታኝከዋለች::: እንደ ዋገምት በሠራ አካላቱ ገብታ ደሙን ትመጥጠዋለች። ምትሃት ሆናበት ባሰባት ባስታወሳት ትዝ ባለችው ቁጥር አብረው እያሉ በሠራ አካላቱ ተሰራጭታ ትርቀዋለች።

ሁኔታዋ ሁሉ አልገባ ይለውና የሚላትን የሚያደርጋትን ሲጠፋው "ምትሃተኛ" ይላታል በልቡ። ፍቅሯ እንደ ውቃቢ ከጭንቅላቱ ላይ ወጥቶ እረፍት ነስቶት ግማሽ ወፈፌ አድርጎት የሚካድምለት አጋፋሪ እንዳጣ ባለ አውሰያ እያንቀዠቀዠው የመረጋጋት ነገር የማይታሰም ጉዳይ ይሆንበትና በድንገት የያዘውን ያሰበውን ጥሎ እሷን ፍለጋ ይበራል።

ረስቶት ይሁን ወይም ራሷ ትምጣ በሚለው አጉል ጀብደኝነቱ ሳይደውልላት አንድ ሳምንት አለፈ። የውኃ ሽታ መሆኑን ስትረዳ እራሷ ደወለችለት። ሳትገረም አልቀረችም።

የሴትነት ክብሯን ተዳፍራ በመደወሏ ብቻ ሳይሆን ስትደውልለት እንደ ዘነጋት ሲነግራት "ጭራሽ ተረስቻለሁ ማለት ነው?" አለችው እየሳቀች። መርሳቱን እንደ ንቀት ነው የቆጠረችው።

"ይቅርታ...ሥራ ስለተደራረበብኝ" በሀፍረት እየተደነጋገረ መለሰላት።

"ልክ ነህ ሥራ እንደሚበዛብህ አይቻለሁ" በልቧ ቆይ አንተ ደደብ ባልሠራልህ እያለች። ነገሩን ቀለል ለማድረግ ሞከረች።

"ከመቀመጫዬ ተነስቼ ይቅርታ እጠይቃለሁ" ይቅርታውን የተቀበለች መሆኗን ብትገልጽለትም በልቧ ግን እየደጋገመች እየዛተችበት ነበር የቆየችው።

"ቆይ ባልሠራልህ!" ብቻዋን ፎከረች።





"ምንም አይደለም። ተቀመጥ ይቅር ብዬሃለሁ" ደስ የሚል ሳቅ ለገሰችው።

እሱ ሳይሆን እሷ እንዲገናኙ ጠየቀችውና ቀጠሮ ሰጠችው። በቀጠሮአቸው ቀን ስትመጣ እጅግ የተለየች የውበት ምትሃት መስላ ደረሰች። አለባበስና እንቅስቃሴዎቿን ሲመለከት እሱን በሷ ውስጥ አድርጎ ለመመዘን ሞከረ። በጭራሽ የሷን ሚዛን የሚደፋ ሆኖ አላገኘውም። የለበሰችው ስስ ቢጫ ፓሪ ቀሚስ ወገቧን ሰርስሮት ስለ ገባ ገልባጣ መቀመጫዋን አጉልቶ አውጥቶታል። በጥቁር ስስ የጡት ማስያዣ የተያዙት ጡቶቿ እንደ ሚሳዬል አፍንጫ ወደ ፊት አፍጥጠዋል። ቀይ ሰውነቷ በሮዝ ከለር ደምቆ ይታያል። ከአንገቷ ላይ ትንሽዬ እስከርቭ ጣል ያደረገች ሲሆን የጎይኗን ቅንድቦች በጥቁር ኩል ተኩላዋለች። በደብዛዛው የክበቡ መብራቶች ደምቀው ወደ ዳር የወጡ የሚመስሉት ትላልቅ ዓይኖቿ እጅግ ደምቀዋል። እራሱን ገመተ። እጅግ በዝታበታለች። ለውበቷ አቻ የሚገኝለት አልመሰለህ አለው።

ከተቀመጠበት ተነስቶ ሰላም ሲላት የተቀባችው ሽቶ በአፍንጫው ሳይሆን በሁለመናው ተሰራጭቶ ውስጡ ሁሉ እሷን እሷን የሸተተ መሰለው። ሆን ብላ ወደ ደረቷ ስባ ለጠፈችው። አልተቃወመም። በመካከላቸው ለአየር ክፍተት ሳይተው ለሰከንድ ተቃቀፉ። ማሽነፍዋን ስላረጋገጠች ካሁን በኋላ መኮፈሱ ያበቃል።" አለች በልቧ።

እንደ ጣኦት ካህን ልቡን አውጥታ እንደምትወስደው እርግጠኛ ነበረች። ልቡን አውልቃ ባዶ ቀፎውን ታስቀረውና በሴት ላይ የሚደረገው መንቀባረርና መኮፈስ ያበቃል። እጢውን እንደ ጣለ ሰይጣን በየደረሰችበት ጥላዋን እየተከተለ ይንከራተታል። ይህንን ታደርጋለች።

"ስምክን ብትነግረኝ ቅር ይልሃል?" አለችው ::

"ዘሩባቤል ዓለምሰገድ" አላት።

"በጣም ደስ የሚል ስም ነው" ደርዝ ያለው ሳቅ ሳቀች።

"እኔም የወይን እሸት ዓለሙ እባላለሁ።"

ከተዋወቃት ከትንሽ ቀናት በኋላ እየደጋገመ መደወል ሲያዘወትር እያፈቀራት መሆኑን እያመነ መምጣት ጀመረ። ልቡ ክፉኛ ሳስቶበት በትንሽ በትልቁ መጠራጠርና መቅናት አዘውትሮ ነበር። ወደ መታጠቢያ ክፍል ለመግባት ስትነሳ ሳይቀር የት ልትሄድ እንደ ፈለገች ይጠይቃታል። ከአንጀቷ ከት ከት ብላ እየሳቀችበት ወደ ገላ መታጠቢያው ክፍል ትገባና በሩን ከቆለፈችበት በኋላ ትጠራዋለች። ተነስቶ በሩን ለመክፈት ሲሞክር ስትሰማ ቀጭን ሳቅ ትስቀበታለች። ይበሳጫል። ምን አስነካችኝ ይሆን? እራሱን ይጠይቃል። የራሱን ከንቱነት እየተራገመ ይመለሳል።

የመጀመሪያው አይደለችም። ይህንን በሚገባ ጠንቅቆ ያውቃል። ግን ልዩ ናት። ፈጽሞ ከማንኛቸውም ጋር ሊያወዳድራት አልቻለም። ከዚያ

በፊት ከብዙ ሴቶች ጋር አብሮ ቀብሟል። ያም ሆኖ ካንዳቸውም ጋር እንደዚህ ካለ የፍቅር ወጥመድ ውስጥ ገብቶ አያውቅም።

እራሱን እየታዘበ "ቆይ ጠብቂኝ አንቺ ሞልቃቃ" እየተራገመ ወደ ሳሎን ተመልሶ ከሶፋው ላይ እጆቹን ዘረጋግቶ በመቀመጥ ዓይኖቹን ኮርኒሱ ላይ ተክሎ ማሰብ ሲጀምር በድንገት ደርሳ በርግብ ሰውነቷ ስትጨፍርበት ሁሉንም ይረሳል። ካልተለማመጣት አትለቀውም። በእርጥብ ሰውነቷ ከላዩ ላይ ወጥታ እንደ ሕፃን ትታገለዋች። ቁጣው በርዶለት መሸነፉን ለማሳወቅ ያህል እንደማኩረፍ ይነጫነጫል። ቂም አይዝም። ውሸቱን ነው ቅብጠቷን ይወደዋል።

በፍቅር ጉዳይ ላይ ከሴት ጋር በተሸናፊነት እጅ እሰጣለሁ ብሎ ገምቶት አያውቅም። ሥራው ከብዙ ሴቶች ጋር ያገናኘው ስለ ነበር ብዙዎች ቀርበውታል። አብዛኛዎቹን ያነጋገራቸው የነበረው በሥራ ጉዳይ ላይ ብቻ ነው። በተለይም አንዳንድ ሴቶች ሲያጠምዱት ሲርቅ ሲጠጉት ሲሸሻቸው ነበር የኖረው።

አንዳንድ ጊዜ ትኩር ብለው ይመለከቱትና ያታዬ ሴት መሆኑንም እረሳው እንዴ? በማለት የመጡበትን ጉዳይ ረስተው የሚመለሱም ነበሩ። አንዳንዶቹም በሆነ ባልሆነ በብስጭት ሲነጫነጩ ሲመለከት ይገርመዋል።

ቢሮው የገቡ ሴቶች ጉዳያቸውን ጨርሰው በሚወጡበት ሰዓት እፎይታ ይሰማዋል። ሴቶችን ለምን እንደ ጦር እንደሚፈራ ለራሱም አይገባውም። ሁል ጊዜ ይፈራቸዋል። ያም ሆኖ ጉዳይ ያላቸው ሴቶች ከመጡ በሥርዓት ያስተናግዳቸዋል። ከሴቶች ጋር ያለው ግንኙነት በሥራ ብቻ ቢሆን ደስታው ነው።

ስለ ትህትናው በማንሳት ሲያደንቁት ብዙም አስተያየት ላለመስጠት ባጭሩ "አመሰግናለሁ" ይልና አንገቱን በመነቅነቅ መልስ ስለሚሰጣቸው የበለጠ ይበሳጫሉ። አመለካከቱ ሁሉ እንደ ሴቶቹ ሁኔታ ይለያያል። ሴትን በተለየ መልኩ መመልከት እንዳለበትና የሴት ልጅን ውበትም ማድነቅ የሚገባና ፍቅር የሚይዛት መሆኑን የተረዳው ዘግይቶ ነበር። ስለ ሴት ልጅ ውበት ለማድነቅ ዓይኑ ተከፈተለት። አጋጣሚው ጥሩ ነው። ልቡ በትክክል እንዲያስብ ረድቶታል። የተስተካከለ ሰውነት ከመልካም ውበትና የሚስብ ትህትና ጋር ፈጣሪው ባልጠበቀው ሰዓት ችሮታል። ይህቺ ልጅ ቢሮውን በእንግድነት ከመርገጧ በፊት በሴቶች ላይ ስለነበረው ትምክህት ብዙ ትሰማ እንደ ነበር ነግራዋለች። ከቢሮው ስትገባ የጠበቃት የተለየ መሆኑን ተረድታለች። የነበረው ባህርይ በሴት ላይ መንቀባረር ሳይሆን ሁሉንም በስፍራው ይደረግ ከሚል አስተሳሰብ ነው። ባህሪውን የበለጠ ወደደችለት። እሱ ስለሷ ባይረዳም እሷ ስለሱ በሁሉም ነገር ተዘጋጅታበታለች።

ለምን እንደ መጣች ሲጠይቃት በተለመደው ርጋታዋ ስለመጣችበት ጉዳይ ነገረችው። በተዘዋዋሪ መንገድ ካልሆነ በቀር የመጣችበት





ጉዳይ እሱን በቀጥታ የሚመለከት አልነበረም። እሷን ለመርዳት ጉዳዩን ወደሚመለከተው ሰው ወስዷት ወደ ራሱ ቢሮ ተመለሰ። እንደ ጨረሰች በምስጋና ሰበብ ከቢሮው ገባችና "እግዜር ይስጥልኝ የመጣሁበትን ጉዳይ ጨርሼአለሁ" አለችው።

ቀና ብሎ ተመለከታት። የቅድሟ ልጅ ነበረች።

"ዕድሜ ለአንተ" ጎንበስ አለች ከጭንቅላቷ "አለቃው ሳትሆን አልቀረህም። ጉዳዩን በተቀላጠፈ ሁኔታ ነው የጨረሰልኝ። የሌሎችን ጫናና የተለየ ጥቅም ስንጠብቅ ኃላፊነታችንን መወጣት ተስኖናል።" ሳቅ ስትል ነጫጭ ጥርሶቿን በትህትና ለገሰችውና ዓይኖቿን አስለመለመች።

"እዚህ መሥሪያ ቤት አለቃና ምንዝር ብሎ ነገር የለም!! ያለ ምንም ቅሬታ ባለ ጉዳይን እናስተናግዳለን።" ሲል መለሰላት።

"የአንተ ትህትና የተለየ ይመስለኛል።" ትኩር ብላ እየተመለከተች መለሰችለት። "ስለ አንተ ለመመስከር በዚህች ደቂቃ ያሳየኸኝ የሚበቃኝ ይመስለኛል።" ኮስተር ያለች መሰለች።

"በተሰለፍንበት ቦታ ኃላፊነታችንን በትክክል የምንወጣ ሠራተኞች ብንሆን እያልኩ እመኛለሁ። በነገራችን ላይ ሥራ ሥለሚበዛብኝ ተቀመጭ አላልኩሽም።" ነገሩ ገባትና እንደ ማፈር አለች። ውጭልኝ ብሎ እያሰናበታት ነው።

"እሄዳለሁ። ሌላ ጊዜ እንደምንገናኝ ተስፋ አደርጋለሁ" ማፈሯ እየጨመረ ተናገረች።

"ለተመሳሳይ ጉዳይ ከመጣሽ መገናኘታችን አይቀርም።" በድጋሚ ወደ በሩ እየተመለከተ መለሰላት።

"ፈቃድህ ከሆነ ስልክህን ብትሰጠኝ? ጉዳይ ገጥሞህ ወደ መሥሪያ ቤቴ ብቅ ብትል ደስ ብሎኝ አስተናግድሃለሁ።"

ተጣድፎ ከቢሮው ሊያስወጣት መፈለጉን ስትረዳ ከመናደድ ይልቅ ተደንቃለች።

"የቢሮ ስልኩን በወረቀት ላይ ጽፎ ሲያቀብላት ቁጥሮቹን ተመልክታ እንደ መሳቅ አለች።

"ተንቀሳቃሽ ስልክ የለህም እንዴ?" ጥያቄዋ የመገረም ነበር።

"ለጊዜው ያለኝ ስልክ ይሄው ነው። በዚሁ መገናኘት እንችላለን ዘወትር ቢሮዬ እገኛለሁ።"

"ለረከሰ ስልክ" ልትለው ፈለገችና ተወችው።

የዚህ ዓይነት አነጋገር ከግብረገብነት የዘለለ በመሆኑ ያሰበችውን ሳትናገር ጸጥ አለች።

"ይቅርታ ተንቀሳቃሽ ስልክ አላወጣሁም።" አላት።

"አንተ ስላላወጣህ ኔትወርኩ ከመጨናነቅ ይድናል ብለህ አስብክ እንዴ?"

"እንዳልሽው ላይቃለል ይችላል፡፡ ቢሆንም የራሴን ኃላፊነት እየተወጣሁ ነኝ ብዬ እገምታለሁ፡፡" ለስላሳ ሳቅ ጋበዛት፡፡

"ከመረጃ መራቅ ጥሩ አይደለም፡፡" ከልቧ ሳቀችበት፡፡ "ሥራህ የተለያዩ መረጃዎችን የሚጠይቅ ይመስለኛል፡፡"

"ለመረጃ ማጠናቀሪያ እነዚህ አይበቁንም?" ከፊት ለፊቱ ያለውን ኮምፒውተር አመለከታት፡፡

ቀልዱ ወደ መራር ቁም ነገር በደቂቃዎች መለወጡ አስገረማት፡፡ የጀመረችው እንደማያዋጣት ስታውቀው ተሰናብታው ወጥታ ሄደች፡፡ የመጣችበት ጉዳይ የተሳካ ባይሆንም እሱን በማየቷ ተደስታለች፡፡ እግር ጥሩ ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜ ካላሰቡት ይወስድና ያላዩትን ያሳያል፡፡ የመጣችው አንድ በውጭ የምትኖር የአክስቷ ልጅ ፓስፖርቷ ጊዜው ስላለፈበት መታደስ የሚችልበትን መንገድ እንድታስተካክልላት ነበር፡፡ እሱም እንደዚሁ ተገላገልኩሽ በማለት ይመስላል በረጅሙ ተነፈሰ፡፡ ያም ሆኖ ግልጽ ባልሆነ ስሜት አእምሮው ስለተወጠረበት ልቡ ክፉኛ ሲታወክበት እየተሰማው ነበር፡፡ እስከ ወጣችበት ድረስ ምንም የተሰማው ነገር አልነበረም፡፡ ተሰናብታው ከወጣች በኋላ ግን ያልተለመደ አዲስ የሆነ ስሜት ተፈጠረበትና ልቡ ስትሸበር ግራ ተጋብቶ መንቆራጠጥና መቅበጥበጥ ጀመረ፡፡ እረፍት የለሽ የመረበሽ ስሜት ሲያንቆራጥጠው ቆይቶ ወደ መስኮቱ ሄደና ውጭው ላይ አፈጠጠ፡፡ ምን ነካኝ ይሆን? ከየት የመጣ የስሜት መወጣጠር ነው?፡፡ ሕመም ተሰማኝ እንዳልል የሕመም ስሜት የለም፡፡ በራሱ ሁኔታ ተገርሞ እንደ መሳቅ እየከጀለው ወደ መቀመጫው ተመልሶ ከወንበሩ ላይ አረፈ፡፡

የልጅቷ ምስልና የድምጽ ቃና እየተመላለሰ ይረብሸዋል፡፡ ክንፍ አውጥቶ በሃሳብ መብረር የለየለት ወፈፌነት ስለሆነ አደብ መግዛት እንዳለበት አሰበ፡፡ በትክክል ማናገር ሲገባው ያንን አላደረገም፡፡ በራሱ ተበሳጨ፡፡ ስልኬን ጠይቃኝ ነበር፡፡ እኔ ነኝ አይሆንም ብዬ ለራሴ ምቀኛ የሆንኩት፡፡ ተንቀሳቃሽ ስልኬን ልሰጣት በተገባም ነበር፡፡ ይህ የለየለት ጅልነት ካልሆነ ሌላ ምን ሊባል ነው፡፡ እንደዚህ ሊሆን ይችላል፡፡ እሷን ለመርዳት ብዬ በራሴ ያመጣሁት ጣጣ፡፡ በርግጥ ከአሁን በፊትም ማንኛውም እንግዳ በተመሳሳይ እረዳለሁ፡፡ ለዚህች ልጅ ከሚገባኝ በላይ ሆኛለሁ ማለት ነው፡፡ እሷም ብትሆን አፍ አውጥታ ስልኬን መጠየቋ የኔን እንደ እንዝርት መሾር አይታ እንደፈለግኂት በማሰቧ ሊሆን ይችላል፡፡ የተለየ ውበት ኖሮኝ አለዚያም ለዋልኩላት ውለታ ወሮታዬን ለመክፈል አስባ አይመስለኝም፡፡ የከሰዓት በኋላው ውሎውን በተመሳሳይ ስሜት ነበር ያሳለፈው፡፡

ምክንያት ፈጥሮ ለፀሐፊው ነገራትና ለምሳ በወጣበት ቀረ፡፡ ማታም ወደ ቤቱ የገባው ያለ ወትሮው አምሽቶ ነበር፡፡





ከትንሽ ቀናት በኋላ ስትደውልለት በፍጹም አላመነም፡፡ ስለ ሥራና ስለ ጤና ከተጠያየቁ በኋላ ስልኬን ልስጣት ወይስ በዚሁ ይቀጥል? እያለ ሲያመነታ ለጥቂት ጊዜ ጸጥታ በመስፈኑ ጥያቄ አቀረበችለት፡፡

"ምነው ሰላም አይደለም እንዴ?" የድምጿ ልዩ ኪናዊ ውበት የበለጠ የደመቀ መሰለው፡፡

"ምኑ?" ግራ የተጋባ በሚመስል ድምጽ ጠየቃት ዘሩባቤል፡፡

"ጸጥ ስትለኝ ጊዜ..." ለመጨረስ አመነታች፡፡ የወይንሸት፡፡

"አንቺ እንድታወሪኝ ተራ ለመስጠት አስቤ ነበር፡፡" ንግግሩን በሳቅ ለማጀብ ሞከረ፡፡

"እ... እንደዚያ ነው" አለችው እየሳቀች፡፡ ሳቋ የተለየ ምትሃት ያለው መሰለው፡፡

"ከዚህ ውጭ ምን ይፈጠራል ብለሽ ስጋሽ?" የድምጹ መደነቃቀፍ አበሳጨው፡፡ አንዳች ነገር ከጉሮሮው እንደ ተወተፈ ሁሉ ቃላቱን ባወጣ ቁጥር እየተሰነጣጠረ አስቸገረው፡፡

"እንጃ ምን አውቃለሁ" እያወራህ በድንገት ጸጥ ስትል እኮ..." ልትል የፈለገችውን አንጠልጥላ ተወችው፡፡

ይህ ልዩ ስልቷ መሆን አለበት ሲል አሰበ፡፡ ስሙን እያቆላመጠች ነበር የጠራችው፡፡

"የሆነ ነገር አስቤ ነው፡፡" በረጅሙ ተነፈሰ፡፡ ግን ምንም እያሰበ እንዳልነበር ያውቃል፡፡

"ምን አሰብህ?" የሚለውን ለመስማት የስልኩን እጀታ በሁለት እጇ እንደ ያዘች ተጠባበቀች፡፡

"የተንቀሳቃሽ ስልኬን ቁጥር እንድሰጥሽ ጠይቀሽኝ ነበር"አለ ዘሩባቤል፡፡

"አዎን" ጠይቄህ ነበር፡፡ እንደሌለህ ነግረኸኛል፡፡"

"ምን ተሰማሽ?" በሳቅ አጀባት፡፡

"ምን ይሰማኛል፡፡ ያው መስጠት እንዳልፈለግህ ስለ ገባኝ ተውኩት፡፡" እሷም ሳቀች

"የለኝም ማለቴን አላመንሽበትም ማለት ነው?" ትንፋሹ ተርገበገበ፡፡

"እንዴት አምንሃለሁ፡፡ ሕፃን ልጆች እንደመጫወቻ ለያዙት ስልክ የለኝም ብትለኝ የማምንህ ይመስልሃል እንዴ?" እየተገረመች ለመሆኗ የድምጿ ቃና ነገረው፡፡

"እንደዚያ ከሆነ ቅር አሰኝቼሻለሁ ማለት ነው፡፡"

"በፍጹም ቅር አላለኝም፡፡ ምናልባትም ባለ ትዳር ስለሆንህ ይሆናል ልትሰጠኝ ያልፈቀድከው" እግረ መንገዷን የምትፈልገውን ጥያቄ አነሳች፡፡

"አይደለም፡፡" አላት እየሳቀ፡፡ የሰማችው ሳቅ ለጆሮ የለሰለሰና ደስ የሚል ቃና ያለው ነበር፡፡ ሳቁ ብቻ ሳይሆን ድምጹም ለጆሮ ይጥማል፡፡" ስትል አሰበች፡፡ ዘሩባቤል ቆይ ይዋጣልናል ሳይታወቃት ጥርሷን ነከሰችበት፡፡

"አስተያየት ብሰጥህ ትቀበለኛለህ?" አለች የወይንሸት።

"ይቻላል።" የምትለውን ለመስማት እየጓጓ ፈቃድ ሰጣት። ምናልባትም በቢሮ ውስጥ ስለ አደረገላት ትህትና ልታመሰግነው መስሎት ነበር።

"ድምጽህ ደስ ይላል..." ቃላቶቿ የወጡት እየተቆራረጡ ነበር።

"አመሰግናለሁ።" አለ ዘሩባቤል።

ሴቶች ብቻ ሳይሆኑ ወንዶችም ድምጹ ደስ እንደሚል አስተያየት ይሰጡታል።

"ታድያ..." ያሰበችውን አቋርጣ ነዳጁን እንደ ጨረሰ ሞተር በድንገት ጸጥ አለችበት።

"ታዲያ ምን?" አለ ዘሩባቤል።

"እናማ ድምጽህ ስለሚያምር የድምጽ ቡዳ ልትሆን ትችላለች ብለህ ነው ስልክህን የከለከልከኝ።"

"እንደዚያ አስቤ አላውቅም ስለ ውበቱም ቢሆን አንች ስትነግሪኝ የመጀመሪያዬ ነሽ..." አላመነችውም።

ብዙ ደርዘን ሴቶች አስተያየት ሊሰጡት ይችላሉ ስትል አሰበች። ቢሆንም የእሷ ጉዳይ አይደለም።

"አትዋሸኝ። እስከ አሁን ከሴት ጋር አልተነጋገርኩም እያልከኝ እንዳይሆን።" የቀልድ ቁጣ ተቆጣች።

"ብነጋገርም ስለ ድምጼ ውበት የነገሩኝ የሉም።" አለ ዘሩባቤል።

"እየዋሸኸኝ ነው። ይህንን ድምጽ የሰማች ማንኛዋም ሴት ሳታደንቅህ ታልፋለች ብዬ አላምንም። እንዲያውም ብዙ ሴቶች በድምጽህ ሊያፈቅሩህ እንደሚችሉ እገምታለሁ።" ጠንከር ባለ ቃል መለሰችለት።

"ከሴት ጋር ተነጋግሬ አላውቅም።" አለ ዘሩባቤል።

አባባሉ ከመጠን በላይ አሳቃትና በሃፍረት እንደ መሸማቀቅ ሲያደርጋት የስልኩን እጀታ በሁለት እጇ ጨብጣ በኃይል ተነፈሰች።

"ከሴት ጋር ተነጋግረህ አታውቅም እንዴ? በጣም ሲበዛ ቀልድ ትችላለህ።"

"አንችም ሳቅሽ ደስ ይላል። በሳቅሽ የወደደሽ..." አንጠልጥሎ ተወውና የምትለውን ለመስማት ጆሮውን አቀና።

"እንደ ብራቅ ጮሁኩብህ አይደል? በጣም ይቅርታ" አንዳንድ ጊዜ ስስቅ እራሴን መቆጣጠር ያቅተኛል።" ያፈረች መሰለች የወይንሸት አለሙ።

"በፍጹም እንደሱ አላሰብኩም። ከምሬ ነው የተናገርኩት። ውበቱን እንጂ ጩኸቱ አልተሰማኝም።"

"እንዳልከው ይሁንልህ። ሴት ልጅ ውዳሴን ትወዳለች የሚለውን አባባል በተግባር እየተረጎምህ ይመስለኛል። ይልቅስ ሁል ጊዜ እንድደውልልህ ለምን ስልክህን አትሰጠኝም ለሚስትህም ቢሆን ድምጼን ስለወደደችው ነው የምትደውልልኝ ሌላ ጉዳይ የላትም ብለህ ንገራት። ሴት ሆና በሴት





ትጨክናለች የሚል ግምት የለኝም። ከጨከነችም አጠገብህ በማትኖርበት ሰዓት ምልክት አድርግልኝና እራሴ እየደውልሁ አነጋግርሃለሁ።"

"እኔ እራሴ ሲመቸኝ እየደወልሁ እናወራለን።" አለ ዘሩባቤል ለመከላከል እየሞከረ።

"ሮጠህ የትም ላትደርስ በከንቱ አደከምከኝ ምን ዓይነት ሞኝ እንስሳ ነው እባካችሁ?" በውስጧ አልጎመጎመች የወይንሸት።

ቁጥሮቹን እየነገራት ከማስታወሻዋ ላይ ከመዘገበች በኋላ "በጣም ደስ ስለ አለኝ ቅሬታዬን እንስቻለሁ።" አለችው እየሳቀች።

ከፍቅረኛው ጋር የመጀመሪያው ትውውቃቸው በዚሁ መልኩ በተደረገ ሂደት ነበር የተጀመረው። ከመድሃኒዓለም ቤተ-መቅደስ ግቢ ከመኪናው ውስጥ እንደ ተቀመጠ በምልሰት ሲያስባት ቆየና አንዳች ኃይል ከውስጡ ሲገፋፋው ስለ ተሰማው ተንቀሳቃሽ ስልኩን አውጥቶ መስመሩን ተጫነው። ጥሪ ማስተናገድ አይችልም። እየተበሳጨ ከፊት ለፊቱ መኪናዋ ኪስ ውስጥ ወርወር አድርጎት ዙሪያውን ተመለከተ። አካባቢው ጨለማ ቢውጠውም ምድረ ግቢው በሰው ሠራሽ መብራቶች በመጥለቅለቁ ማንኛውም እንቅስቃሴ ይታይ ነበር። በስተደቡብ ምስራቅ በሚገኘው አየር ጣቢያ የሚነሱና የሚያርፉ አየሮች ድምፃቸው ያስተጋባል።

የምእመናኑ መንፈሳዊ ስብከት አብቅቶ ትምህርቱን ሲከታተል የነበረው ሕዝብ ወደ መኖሪያው ለመመለስ ከግቢው በመውጣት ላይ መሆኑን ተመለከተ። ግቢው ውስጥ የነበሩት መኪናዎችም በደቡብና በሰሜን ባሉት ሁለት በሮች እየወጡ ናቸው። ሰዓቱን ተመለከተ። ከምሽቱ ሁለት ተኩል ይላል። እስከ ሦስት ከጠበቀ በኋላ ከቤተ-መቅደሱ ግቢ መውጣት ይኖርበታል። ከሦስት ሰዓት በኋላ በሩ ሊዘጋ ይችላል። የተፈጠረው ነገር ባይገባውም ውስጡን አንዳች ነገር እየረበሸው መንፈሱ ተወጥሯል።

"አሳባቸውን ለውጠው? ወይስ ችግር ገጥሟቸው?" እራሱን እየደጋገመ ጠየቀ ምንም ይሁን ምን አንድ ነገር ይታየዋል። በውል ያልታወቀ አንድ ችግር አለ። አሳቡን ወደ ወይንሸት መለሰ።

በዚህ ሁኔታ የተጀመረው የፍቅራቸው መስመር እየረዘመ እስከ ጋብቻ ጥያቄ ለመድረስ ችሎ ነበር። ያም ሆኖ ገና አልተጋቡም። እሷ የሱን የሥራ ድርሻ ትወቅ እንጂ በሷ በኩል ያለውን ትክክለኛ የሥራ ድርሻዋን አያውቅም። ራሷ አውቃ እንድትነግረው ስለሚፈልግም ወጥሮ በመያዝ ሊጠይቃት አልፈለገም። ጠቅላይ ሚኒስቴር ቢሮ ውስጥ በረዳት ጸሐፊነት እንደምትሠራ ከተዋወቁ ከብዙ ጊዜ በኋላ ከሰዎች ሰምቷል። እሱ በፍጹም ሊጠይቃት አይፈልግም።

በአሜሪካንና በእንግሊዝ የስለላ ባለ ሙያዎች በተዋቀረው ዓለም አቀፍ የመረጃ ሥራ ውስጥ መሥራቷን አያውቅም።

የሚፈልገው እሷነቷን በመሆኑ ስለ ሥራዋ ጸባይ ብዙ ማወቅ ትርጉም የሚሰጠው እንዳልሆነ ይገልጽላታል። በነፃነት የምትሠሪበት ቦታ እስከ ሆነ ድረስ "በርቺ" ከማለት ውጭ የማወቅ ጉጉት አልነበረውም። በተጣላለፈ የደኅንነት የመረጃ መረብ ውስጥ የምትሠራ መሆኗን ቢያውቅ ኖሮ ችግሮችን ያስከትላል የሚል ግምት ያድርበት እንደ ነበር መገመቷ አልቀረም።

የመረጃ ሥራ አንደኛው ሌላውን በዓይነቁራኛ እየተጠባበቀ ጠልፎ ለመጣል የሚሽቀዳደምበት የተንኮል መንገድ በመሆኑ አንድ ቀን ከአደጋ ላይ ልትወድቅ እንደምትችል እራሷም ትረዳለች። ለቃ መውጣቷም የበለጠ አደጋን ያስከትላል ብላ ስለጠረጠረች ልትነግረው አልፈለገችም። አምሽታ ስትገባም ቢሆን የምታመሽበትን ለማወቅ ለምን እንደ ሌሎቹ የመንግሥት መስሪያ ቤት ሠራተኞች ሰዓትሽን ጠብቀሽ አትወጭም? የሚል ጥያቄ እያነሳ መነዛነዝ አይፈልግም።

አንዳንድ ጊዜ እንዲያውም እስከ እኩለ ሌሊት ታመሽና በልዩ ጥበቃ አባላት እስከ ቤቷ ድረስ ያመጧታል። ጠዋትም በተመሳሳይ ሁኔታ ይወስዷታል። ሁል ጊዜ የምትመላለስበት መኪናም የተለያየ ነው። በአሳለፉት የሁለት ዓመት ቆይታቸው ጥሩ ፍቅር አሳልፈዋል። ታምነዋለች እሱም ያለ መጠራጠር ያምናታል። ስለ ማንነቷ አይጠይቅም። እሷም እንደዚሁ እንዲህ ያለ ጥያቄ አንስታ አታውቅም።

ስልኩን እንደ ገና ሞከረው። እንደ ተዘጋ ነው። ደጋግሞ ሞከረው ጥሪ አያስተናግድም እንደ ስልክ መዘጋት የሚያበሳጨው ነገር ያለ አይመስለውም። ከመድሃኒዓለም ቤተ-መቅደስ ግቢ ለመውጣት መኪናውን በሚያንቀሳቅስበት ወቅት ከምሽቱ አራት ሰዓት ሆኖ ነበር። የምሽት ፕሮግራሙ ከተጠናቀቀ ዘግይቶ ስለ ነበር ምእመናኑ ግቢውን ለቅቆ በመውጣቱ ቤተ መቅደሱ ጭር ማለት ጀምሯል። ከቤተ መቅደሱ ግቢ ብዙ ትርምስ አይታይም። አብዛኛው ሕዝብ ቀደም ሲል ሄዷል። መኪናውን እያሽከረከረ ከግቢ ወጥቶ የሰሜንን አቅጣጫ ያዘ። የትራፊክ መጨናነቁን ለማለፍ በጥንቃቄ እያሽከረከረ እያለ የተንቀሳቃሽ ስልኩ ስለ ጮኸ ተንጠራርቶ አነሳው።

ሰዎቹ ነበሩ የደወሉት እየቀለዱበት እንደሆነ ገባው። ኢምፔሪያል ሆቴል አጠገብ ሲደርስ ወደ ቀኝ ታጠፈ ኮርያ ሆስፒታል ከመድረሱ በፊት ዋናውን መንገድ ለቅቆ ግራውን ያዘ። እየሄደ የነበረው ወደ ቤቱ አቅጣጫ ነበር። መመለስ እንዳለበት አመነ ቢሸሽም እንደማይርቃቸው ያምናል። ማድረግ ያለበት ፊት ለፊት መጋፈጥ ብቻ ነው። ከአንድ ቦታ ሆነው ሲመለከቱት ቆይተው ሲንቀሳቀስ አይተው ለመረበሽ ደውለውለታል። አድራጐታቸው ለማንም ግልጽ ነበር።





ወደ ቤቱ ከመግባቱ በፊት የመኪናውን አፍንጫ ወደ መጣበት አቅጣጫ አዞረ። ማድረግ ያለበት ይህንን ብቻ ነው። ሳምሶንና ስምኦን አሻንጉሊት ሊያደርጉት እየሞከሩ ናቸው። በነሱ ግምት አዲስ ምልምላቸው መሆኑ ነው። ራሱን በራሱ "ጀግና ነህ" ቢለውም መልሶ "ፈሪ ነህ" እያለው ነው። ነገሩ ሁሉ አደገኛ ነው ማፍያዎቹ መልምለውታል። ከነሱ መሸሽ የበለጠ አደጋን ያመጣል።

# ምእራፍ አሥራ ሶስት

በልዩ ጥበብ የተሠራው ባለ ሰባት ፎቅ በደብዛዛው የምሽት ብርሃን ሲታይ በጣም የገዘፈ ነው፡፡ በሕንፃው የመጀመሪያው የመግቢያ በር በኩል በደቃቃው ከሚበሩ ትናንሽ አምፖሎች በቀር በሕንፃው የውስጥ ክፍሎች ብርሃን የለም፡፡ እንደ ሲኦል የከበደውን ሕንፃ ፊት ለፊት እየተመለከተ የመኪናውን አፍንጫ ወደዚያው አቅጣጫ አደረገ፡፡

አካባቢው ጭር ከማለቱ የተነሳ እንደ መቃብር ይከብዳል፡፡ ሁሉም ነገር እንደ በረዶ የቀዘቀዘና የሚከብድ ነው፡፡ ጠብደል የጥበቃ ሠራተኛ ትልቁን የብረት በር በሃዲድ ላይ እየተጎተተ በግማሽ ሲከፍተው እንዲገባ የተፈቀደ መሆኑ ገባው፡፡ ፔጆዋ ወደ ውስጥ ዘልቃ በስተጀርባ በኩል በተዘጋጀው የመኪና ማቆሚያ ስፍራ አመራች፡፡ በርከት ያሉ መኪናዎች ቆመውበታል፡፡ መሪውን እንደ ጨበጠ በመስኮት የሚገባውን አየር በኃይል ስቦ ወደ ሳምባው አስገባው፡፡

ሕይወቱ ከአደጋ ውስጥ መሆኑን የተረዳው ዘግይቶ በመሆኑ ተመልሶ ለመውጣት አልቻለም፡፡ የሚመጣውን ለመቀበል ወደ ፊት መቀጠል ግዴታው ነበር፡፡ ወደ ኋላ መመለሻው እንደ ራቀው ተረድቷል፡፡

ጭንቀት እየተሰማው ለራሱ ግልፅ ባልሆነ ምክንያት ተዳክሟል፡፡ ሰውነቱ ብቻ ሳይሆን መንፈሱም እንደዚሁ ልትት ብሎ ልቡ እየታወከች ነው፡፡ ከፊት ለፊቱ እየመጣ ያለው ረጅም የመከራ ቀን ሳይሠራ እያደከመው መሆኑን እየነገረው ነው፡፡ ቀጠሮው ያለ አንዳች ምክንያት እንዳልተሰረዘ ያውቃል፡፡ በስልኩ ብዙ ማብራሪያ ሊሠጠው ያለ መፈለጉ በራሱ ችግር ነው፡፡ ነገሩ መበላሸት ጀምሯል ማለት ነው፡፡

የመኪናዋ መስታወት ሲመታ ቀና ብሎ ተመለከተ፡፡ በጨለማው ውስጥ የቆመው ሰው አካሉ እጅግ ገዘፎ ነበር የታየው፡፡ እንዲወጣ ምልክት እየሰጠው መሆኑ ገባው፡፡ በግራ እጁ እየደጋገመ ምልክት በሚሰጥበት ሰዓት የቀኝ እጁ ያለው በለበሰው ቆዳ ካፖርት ኪስ ውስጥ ስለ ነበር ሽጉጥ የያዘ መሆኑን ተረዳ፡፡

አስፈሪ ቅርጽ ያለውን ተክለ ሰውነቱን ተመለከተው ረዘም ያለ መጣጣ ፊት የጨልሌ መንቁር መሳይ አፍንጫ ነበረው፡፡ በስፖርት የተገነባ ሰውነት ወታደር የሚመስል የተስተካከለ አቋም ያለው ሰው ነው፡፡

ከአሁን በፊት በአካል አይቶት እንደማያውቅ እርግጠኛ ነበር፡፡ እየደጋገመ ፊቱን ለማየት ሞከረ፡፡ ትክክል ነው፡፡ ሰውየውን ከአሁን በፊት በአካለ ሥጋ አይቶት አያውቅም፡፡ እንደ ንስር አሞራ ክንፎች የረዘሙት እጆቹን ሲመለከት የበለጠ ቀፈፈው፡፡... ወደ ማጅራቱ እየሸሸ ያለው ስስ ፀጉሩ ዕድሜውን ያበስራል፡፡





"እንድፈትሽህ ትፈቅድልኛለህ?" በደብዛዛው ብርሃን ፊቱን ለማየት እየሞከረ ጠየቀው፡፡

"መሣሪያ ታጥቆም ሆነ የሞባይል ስልክ ይዞ ወደ ሕንፃው መግባት አጥብቆ የተከለከለ ነው፡፡ ፊትክን አዙርና እጅህን ሽቅብ ዘርግተህ በጉልበትህ ለመቆም ሞክር"፡፡

ሲናገር የረጋ ቢመስልም ሽብርን የሚለቅ ዓይነት ሰው ነው፡፡

"መሳሪያ አልያዝኩም፡፡" አለ ዘሩባቤል "ሞባይል ስልኬንም ከሆነ አጥፍቼ ከመኪናዋ ኪስ ትቼው ልሄድ እችላለሁ፡፡" በራሱ ፈቃድ መጥቶ መማረኩ እያበሸቀው ነበር፡፡

"እራሴ ፈትሼ ማረጋገጥ ይኖርብኛል፡፡ ሞባይሉን ግን ከመኪናዋ ኪስ ልትተወው ትችላለህ፡፡ በቅድሚያ ተፈተሽ" አነጋገሩ ብቻ ሳይሆን እጆቹም እንደ ብረት የጠነከሩ ነበሩ፡፡

እንደ ተባለው አድርጎ ፍተሻውን እንዳጠናቀቀ የመኪናዋን ቁልፍ ተቀበለው፡፡

"ምን እየተደረገ ነው ያለው?" አቋረጠው፡፡

"ዝም ብለህ እኔን ተከተለኝ፡፡ ወደ ሕንፃው ከገባን በኋላ መነጋገር በጥብቅ የተከለከለ ነው፡፡ ምንም ዓይነት ቃላት እንዳታሰማ መጠንቀቅ አለብህ፡፡" በትክሻው ገፍተር ሲያደርገው መኪና የገጨው ያህል ተሰማው ዘሩባቤልን፡፡

የሕንፃውን ደረጃ እየወጡ በነበረበት ወቅት በመስተዋቱ ከሚገባው ነፀብራቅ በቀር መብራት አልነበረውም፡፡ በደረጃው በኩል ያለው የሕንፃው ግድግዳ በመስታወት የተገጠመ በመሆኑ በድቅድቅ ጨለማ ከመዋጥ አድኖታል፡፡

ሦስተኛ ፎቅ ላይ ሲደርሱ ወደ ጆሮው ተጠግቶ "በእግርህ ያደክምኩህ የሕንፃው አሳንሰር በኤሌክትሪክ መቋረጥ ምክንያት በመበላሸቱ ነው፡፡" ሲል አንሾካሾከለት፡፡

የአሳንሰሩ አይደለም የሱም እስትንፋስ ቢቋረጥ ግድ አልነበረውም፡፡ መልስ ሳይሰጠው ወደ ፊት ቀጠለ ዘሩባቤል፡፡ ምንም ምርጫ አልነበረውም፡፡

እንደሚታረድ ሰንጋ ከመረባቸው ከትተውታል፡፡ "አበቃ" አለ ለራሱ፡፡

"በቅርብ ነው አሳንሰሩ ሥራው የተቋረጠው ደጋግመን ብናሳስብም መልሰው በመጠገን ሥራው እንዲቀጥል አላስቻሉትም፡፡" መለፍለፍ ጀምሯል፡፡

"በምን ምክንያት ሲቋረጥ እንደቻለና እንዴት መልሰው መጠገን እንዳልቻሉ መረዳት ነበረባችሁ፡፡"

"መልስ መስጠት የሚችል አካል ያለ አይመስለኝም፡፡ የማውቀው ለበርካታ ወራቶች አለዚያም ዓመት በዚህ ሕንፃ ላይ መብራት በተገቢው

መንገድ መሥራት እንደማይችል ብቻ ነው።" ትከሻውን ነቅነቅ እያደረገ ተናገረ።

"እስገራሚ ነው..." በረጅሙ እየተነፈሰ መለሰለት ዘሩባቤል።

"መገረሙን ለሌላ ጊዜ ተወው። በመጠኑ ከኔ ራቅ ብለህ ተከተለኝ። ወደኔ እንድትጠጋኝ አልፈቅድልህም።" መልስ ሳይጠብቅ ሽቅብ መገስገሱን ቀጠለ።

በነጭ ሴራሚክስ የተሠራው ደረጃ በጨለማ የተዋጠ ቢሆንም ለእርምጃ ያህል ይታያል።

ዓራተኛ ፎቅ ሲደርሱ ዜሮ አምፖሎች በኮሪደሩ ጣራ ተራርቀው ተሰቅለው ሲመለከት መብራት የለውም ማለቱ ዘሩባቤልን አናደደው። በኮሪደሩ ግራ ቀኝ አራት ያህል ክፍሎችን አልፈው እንደ ሄዱ በግራ በኩል ያለውን በር በሽጉጡ ጫፍ እያመለከተው ነጠላ ቁልፍ ከኪሱ አውጥቶ ዘረጋለትና እንዲከፍት ምልክት ሰጠው። መጠነኛ ስፋት ያለው የስብሰባ አዳራሽ በብርሃን ኩሬ የተሞላ ነበር። በግማሽ የተከፈተውን በር በትከሻው ገፋ አድርጎት ወደ ውስጥ ሲዘልቅ ተከትሎት ገባ ዘሩባቤል።

የክፍሎቹ መስኮቶች መስታወቶቹ ቀለም መቀባታቸው ብርሃኑ እንዳይወጣ አድርጎታል። የሕንፃው ውጫዊ አካል በጨለማ እንዲዋጥ ያደረገውም በዚህ ምክንያት መሆኑ ገባው።

ከአንድ ጥግ በኩል ከተቀመጠ በኋላ የተሰበሰቡትን ሰዎች ለማየት ሞከረ። ያልተያዙ በርከት ያሉ ፎቴ ወንበሮችን በማየቱም የሚመጡ ሰዎች ሊኖሩ እንደሚችሉ ገምቶ ነበር። በክፍሉ የበራው ባለ ቀለም አምፑል የሁሉንም ልብስና መልክ ወደ ሮዝ ቀይሮታል። ይዞት የመጣው ሰው ስብሰባውን እየመሩ ካሉት ሰዎች አጠገብ ከነበረው ትርፍ ወንበር ላይ ተቀምጧል። ጥሩ ወፌፌ ነህ ሲል አሰበ። ወፌፌ ብቻ ሳይሆን ለቡድኑ አንድ ቁልፍ ሰው ሊሆን እንደሚችል አልተጠራጠረም። ከውጭ የነበረው እንቅስቃሴውና ልበ ሙሉነት የበለጠ የጨመረ እስኪመስል ድረስ ትከሻው ሽቅብ ያበጠ መሰለው። ከአረማመዱ ጀምሮ ያለው እንቅስቃሴ ከኃላፊዎቹ እኩል የሥራ ኃላፊነት ያለው መሆኑን ለሌሎች ማሳየት የሚፈልግ መሆኑን ይጠቁማል። አብዛኞዎቹ ሙሉ ሱፍ የለበሱና ከረቫት ያሰሩ ሲሆኑ ሁለት ሰዎች ብቻ ሌዘር ጃኬት የደረቡ ናቸው።

ለተወሰኑ ደቂቃዎች ያህል እርስ በርስ ከተያዩ በኋላ ውይይቱ በነበረበት ቀጠለ። አንዳንዶቹ በቀኝ ሌሎቹ በግራ እጅ ጣቶቻቸው ላይ ያጠለቋቸው የአልማዝ ቀለበቶችም ለደብዛዛው ብርሃን ልዩ ህብር የፈጠሩ ነበሩ። ከአለባበሳቸው ጀምሮ ተክለ አቋማቸው ጭምር ቱጃርነታቸውን የሚመሰክር ይመስል የበለጠ እያገነናቸው መሰለው ዘሩባቤል።

ውይይቱን በሚመሩት ሰዎች የተመሰጠ ቢመስልም እይታው ያለው በሁሉም ቦታ ነበር። ይዞት የመጣው ከአንድ ሰው ጋር ትክሻ





ለትክሻ ገጥመው በሹክሹክታ ያወራል። ሌላ ሰው ወደ አዳራሹ ሲገባ ውይይቱ ተቋረጠ። የገባው ሰው በሩን በጥንቃቄ መልሶ ዘጋና በዝግታ እየተራመደ እሱን ይዞት ከገባው ሰው አጠገብ ከነበረ ትርፍ ወንበር ላይ አረፍ ብሎ ከራቫቱን እያስተካለ በክፍሉ የነበሩትን ታዳሚዎች በአይኑ ይፈትሽ ጀመር። ዙሪያ ጥጉን እየፈተሸ ቆይቶም እይታው ከዘሩባቤል ላይ አረፈ። የሚለው ባይሰማውም ስለ እሱ እየጠየቀው እንደሆነ ለመገመት አልተቸገረም። አንዳንድ ጊዜም የቀኝ ሌባ ጣቱን የሚጠቁም ይመስላል። ተናግሮ ሲጨርስ ቀና ብሎ አንገቱን በመነቅነቅ ፈገግ ሲል ከፊት ጥርሶቹ መካከል የተሰኩት ሁለት የወርቅ ጥርሶች እንደ አልማዝ ፈርጥ ያብረቀርቃሉ።

አንድ ሰው ገባና እንዳትንቀሳቀስ ተብሎ ትእዛዝ እንደ ተሠጠው ሁሉ ከወለሉ መሀል ብዙ ደቂቃዎች አሳለፈ። ክፍሉን በጥንቃቄ ሲቃኝ ቆይቶ ዘሩባቤልን ተመለከተው። ሁሉም ሰዎች የእሱን መምጣት እየጠበቁ እንደሆነ ሲረዳ ሁሉም ነገር ያከተመለት መስሎ ተሰማው።

እይታውን ሳይነቅል ሲመለከተው ቆይቶ እንደ መንጠር እየከጀለው ዘሩባቤል ወደ ተቀመጠበት አቅጣጫ አመራ። እንቅስቃሴው ስለ ከበደው ይመስላል የዘሩባቤል ልብ ክፉኛ ተረበሸበት።

ሳይቀመጥ ትከሻውን ሲይዘው " ምን ነበር?"አለው።

"በዚህ ስብሰባ ላይ ከአሁን በፊት ተካፍለህ ታውቃለህ?" ሲል ጠየቀው።

ያንን ከሚያክል ግዙፍ ሰውነት የወጣው ድምጽ እንደ ፊሽካ ጥርት ያለና እንደ እባብ ፉጨት የቀጠነ መሆኑም በራሱ የሚቀፍ ነበር።

"የመጀመሪያዬ ነው።" ሲል መለሰለት።

የቀይ ዳማ የፊት ቀለም አለው። ቅርጽ ቅርጽ ያበጀው አንገቱ በድሎት ለመኖሩ ምስክርነት እየሰጠ ይመስላል። ወዘናውም እንደዚሁ ቅባት እንደ በዛበት ትኩስ የሸክላ ዕቃ ከውስጥ ወደ ውጭ ርጥበት እያመነጨ ነው።

"ከውጭ ስገባ መቀመጫ አገኛለሁ የሚል ግምት አልነበረኝም።" ትክሻውን የበለጠ እያስጠጋው ክብደቱን ቀለለበት። ከጐኑ ተቀመጠ።

"ብዙ ሰዎች ይመጡ ነበር?" ለመራቅ እየሞከረ ጠየቀው።

"ሁሉም አባሎች ቢመጡ ኖሮ ይህች አዳራሽ ተጨናንቃ ልትፈነዳ ትደርስ ነበር። በዚያም ላይ አባሎቹ ሁሉም የተዋጣላቸው ቱጃሮች በመሆናቸው ተጨናንቀው መቀመጥ አይሆንላቸውም" እንደ ሸንበቆ ቀጥ ብሎ ወርዶ ከወደ ጫፉ የተጎረደ ወፍራም አፍንጫውን ሶፍት አውጥቶ እያፀዳዳ ንግግሩን ቀጠለ።

"ጉንፋን ይዞኝ ... አዲስ አበባ አልጸዳ ብላ እኛም ከጉንፋን የጸዳ አፍንጫ እንዳይኖረን ፈርዳብናለች። በየደረስክበት መጥፎ ሽታ ይተነፍግሃል። ሰውም ግድ ስሌለው ከተማቅ እንድትጸዳ አይፈልግም። የራሱን የቤት ጥራጊ በሌላው ቤት ደጃፍ ይጥላል። ሕዝቡ ለጽዳት

ያለው ግምት እጅግ ዝቅተኛ ነው። የራሱን ቤት አጸዳሁ ሲል ሌላውን ከአደጋ ላይ ይጥላል። በተዘዋዋሪ መንገድም ራሱን አለዚያም ቤተሰቡን ከጽዳት ጉድለት ለሚመጡ በሽታዎች ያጋልጣል። አቅም ቢኖረኝ ኖሮ ምን እንደማደርግ ታውቃለህ?" እንደመገልፈጥ ብሎ አፍንጫውን የጠራረገበትን ሶፍት ወደ ኪሱ በመመለስ አዘቅዝቆ ተመለከተው።

"ምን ታደርግ ነበር?" አለው ዘሩባቤል።

"የከተማዋን ከንቲባ ጋሼ አበራ ሞላን አድርጌ እሹመው ነበር" ራሱ ተናግሮ ለራሱ የበቃውን ያህል ሲንከተከት የበለጠ አስጠላው።

"ምኞትህ አይከፋም።" እየተሰላቸ መለሰለት።

"አሁን የተመረጠው ከንቲባማ እጅግ የባሰበት ደነዝ ነው። ስለ ከተማዋ መሠረታዊ ችግሮች ከመወያየትና መፍትሔ ከመሻት ይልቅ ያልረባ ትርኪ ምርኪ ተረት ሲያወራ ብዙ ጊዜውን ይፈጃል። እነሱ ከገቡ የተወለደ ልጅ ዩኒቨርሲቲ ጨርሶ ሥራ ቢይዝም አሁንም ስለ ደርግ ክፋትና ስለ ጫካ ትግል እየተረኩልን ነው። ሰውን ገድሎ ሥልጣን መያዝን እንደ ትልቅ ጀብድ ይተርካሉ። ያልታደሉ ከንቱዎች። ይህቺ ሀገር ከጦረኝነት በዘለለ በዲፕሎማሲያዊ እውቀት ሥልጣን የሚጨብጥ መሪ የምታገኘው መቼ ይመጣ ይሆን እያልኩ አስባለሁ።

የአዲስ አበባ ከተማ መሠረታዊ ይዘት መበላሸት ምክንያቱ ያለፉት መጥፎ የሥርዓቱ አሠራሮች መሆኑን ማስረዳት እኛ ምን አገባን ሊሉን ይዳዳቸዋል። የነሱን ደካማነት የሚያካክሱት ያለፉትን ሥርዓቶች በመውቀስና በመኮነን ነው። ስለ አፄው ድክመት ደርግ ሲያወራ በችግሮቹ ሁሉ ተወቃሽ የፊውዳሉ ሥርዓት እንደተደረገ በርካታ ዓመታት ተቆጠሩ። እነዚህም ደርግን ሲከሱና ሲወቅሱ ምንም ሳይሠሩ ጊዜያቸው ወደ ፊት እየተሽቀዳደመ ሩጫውን ጨርሶ መቆሚያው ሊደርስ ነው።

ለትችት እንጂ ለሥራ የሚሆን አእምሮ አልፈጠረባቸውም። በዚህ ስብሰባ የምትመለከታቸው አንዳንዶቹ ጥቅም ለማግኘት ከእኛ ጋር የተጣመሩ የዚህች ሀገር ተጠሪዎች ናቸው። በትክክል ይግባህ። ይህ ቡድን የዘረፋ ቡድን ነው። የምትመለከታቸው አንዳንዶቹ በተሰጣቸው እንጀራ ያልጠገቡ ከድሀው ጉሮሮ የሚነጥቁ አሁን ደግሞ በዝርፊያ የተሰማሩ ከሃዲዎች ናቸው።"

ስለ ሰውየው ለመገመት የተቸገረ መሰለ አንተስ ከዚህ የመጣኸው ምን ፍለጋ ይሆን? ለመሆኑ አንተ ማነህ? ይህ አስቸጋሪ የሆነ አስተያየት ነው። ከዚህ ውጭ ምንም ሊሆን አይችልም። ምንም ዓይነት መልስ ከመስጠት መቆጠብ እንደሚኖርበት ተገነዘበ ዘሩባቤል።

"ምነው ዝም አልክ?" በመገረም ዓይነት እያስተዋለ ጠየቀው።

"የምትለው አልገባኝም" ቀና ብሎ ተመለከተው።





"የነገርኩህን ሁሉ አልሰማሁህም ለማለት ነው? እንደዚያ ከሆነ አስገራሚ ሰው ነህ።"

በቅሬታ አለዚያም በትዝብት እራሱን ነቀነቀ ሰውዬው።

"አንዳንዶች የመንግሥት ባለሥልጣኖች ናቸው እያልከኝ መሰለኝ" ድምጹን ቀንሶ ጠየቀው።

"ትክክል ነህ።" አለው እራሱን እየወዘወዘ።

"ምን ሊሠሩ መጡ?" አለው።

"እየተመለመሉ።" ሳቅ አለና መለሰለት።

"ማነው የመለመላቸው?" ግራ መጋባቱ ጨመረ።

"አንተን የመለመሉህ" ትክሻውን ጭምር ናጠበት።

"እኔም ተመልምያለሁ እንዴ?" ግራ መጋባቱ ወደ መገረም ተሰወጠና ሳቅ ብሎ አስተዋለው።

"ተመልምለሃል ከዛሬ ጀምረህ የሙሉ አባልነት መታወቂያ ይሠጥሃል።" ተናግሮ ሲጨርስ በሳቅ አጀበው።

"ወደዚህ መምጣትህን አታምንበትም ማለት ነው ለምን ምሥጢር ለማባከን ፈለግህ?" ከንግግሩ ጀርባ የተዘረጋ የተንኮል መረብ ስለ መኖሩ ለማረጋገጥ ያቀረበው ጥያቄ ነበር።

"እየነገርኩህ ያለሁት ስለ ራሴ አይደለም።" አለ ሰውየው።

የነገሩ ውል እንደ ልቃቂት ከንዝርቱ እራስ እንደሚጀምር ሲገምት የመጨነቅ ስሜት እየተሰማው ውስጡን አንዳች ኃይል ሲንጠው ታወቀው ዘሩባቤል።

ሕዝብን ለማገልገል ኃላፊነት የተጣለባቸው አካላት የመረጣቸውን ሕዝብ ለመጉዳት ከሕገ-ወጦች ጋር የሚያደርጉት የክህደት ሴራ ሰብአዊ ባህሪውን ሲፈታተነው ልቡን እንደማቅለሽለሽ አደረገው። የእሱስ ምርጫና መጨረሻ ምን ይሆን።

"የሚመጡት በሙሉ የተለያዩ ጥቅም ፈላጊ ባለ ሥልጣኖች ናቸው እያልከኝ መሠለኝ?" እውነቱን የበለጠ ለማረጋገጥ ፈለገ።

"ሙሉ በሙሉ ናቸው የሚል ቃል አልወጣኝም። አንዳንዶቹ ግን ናቸው። ወደዚህ ድርጅት እንዲቀላቀሉ የተደረጉት በሙሉ ከተጣለባቸው የሀገር ኃላፊነት አንፃር አልተቃወሙም።"

"ለቅቀው ቢጠፉ የሚከታተላቸው የለም እንዴ? ማለቴ የሀብት ጥቅሙን ለመካፈል ካልጓጉ" ይህ ጥያቄ በቀላሉ የሚመለስ አልነበረም። ሰውየው ለደቂቃዎች አሰበ። ከገቡ በኋላ ለመውጣት ሕይወትን እንደሚያስከፍል ያውቃል።

"በቤርሙዳ የባህር ክልል በኩል የተሳፈርክባት መርከብህ እንዳትቀዝፍ ተጠንቀቅ። በዚያ የባህር ክልል አቅራቢያ ከተቃረበች ሁሉም ነገር ያበቃል።"

ማስጠንቀቂያ ይሁን ወይም የድርጅቱን ደንብ ማስተዋወቅ በውል

ሲገባው ባይችልም የሚናገረው እውነትና ትክክልም ስለመሆኑ አልተጠራጠረም። የነገሩ ማብቂያ እሱ እየነገረው ካለው ውጭ ሊሆን አይችልም። ስለዚህ እሱም ወንበር ገፊ ባለ ሳምንት ነው። በርግጥ አዲስ ምልምል በመሆኑ በሁሉም ነገር ግር እንደሚሰኝ ያውቃል።

ነገ እኔም እንዱ ከሃዲ ነኝ እራሱን ከተጠያቂዎቹ ተርታ በራሱ ፈቃድ መደበው። እርግጠኛነት እየተሰማው ስለ ነበር ሌሎቹን ለመውቀስ የነበረው ፍላጎቱ ቀስ በቀስ እንደ ጉም ተንኖ ከላዩ ሲገፈፍ ተሰማው። ሌሎችን መውቀስ ቀላል ሲሆን መሆን ግን እጅግ ከባዱ ነገር ነው። ማንን ማን ይወቅሳል። እኔም የነገው የመድረኩ መሪ ልሆን እችላለሁ። በመኖርና ባለመኖር መካከል የተሰጡ ሁለት ምርጫዎች አሉ። እነዚህ ምርጫዎች የነገው የመኖርና ያለመኖር ወሳኝ ዕጣዬ ሆነው ከቀረቡልኝ የቱን ቀድሜ ማንሳት እንዳለብኝ መወሰን የምችለው ሲቀርብልኝ ብቻ ነው።

"ተጫወት አትተክዝ እየለመድከው ስትሄድ ሁሉም ነገር ይቀልሃል።"

"ምን አልከኝ?" ቀና ብሎ ተመለከተው ዘሩባቤል።

"ትለምደዋለህ።"

"የመንፈስ ጥንካሬን ሳይጠይቅ የሚቀር አይመስለኝም። ፈቃደኛ ሆነህ ብትቀጥልም እያንዳንዱ እርምጃህ ከአደጋ ጋር የተቆራኘች ከሆነ ከሞት የተለየ አይመስለኝም።"

"እንደምነግርህ ሁሉም ነገር ከችግር ጋር የተቆራኘ ይመስላል። እንደገመትከው ሁሉም ውሳኔዎች ከአደጋ ጋር የተቆራኙ ናቸው። ቢሆንም መስማማቱ ዕድሜን የሚሰጥ በመሆኑ እንደ ተሻለ አማራጭ ይወሰዳል" በሳቅ የታጀበ መልስ ሰጠው።

"ለመቀበልም እኮ ድፍረትን የሚጠይቅ ከባድ ምርጫ ይመስለኛል" አለ ዘሩባቤል።

"ለአንተ የሚጠቅምህ መስማማቱ ስለሆነ አብረህ ለመቀጠል አሁኑኑ መወሰን ይኖርብሃል።"

እረጅም እጁን ከትከሻው ላይ ሲጭንበት እንደ ማንዘፍዘፍ ያለ ስሜት ተሰማው።

"ትእዛዝ እየሰጠኸኝ መሰለኝ" ወፍራም ክንዱን ከትከሻው ለማንሳት በእጁ ጨበጠው።

"ትእዛዝ አይደለም። ቀጣዩን ምን መወሰን እንደሚገባህ እንድታስብበት ለማድረግ እየመከርኩህ ነው። የምነግርህ ወደ ፊት ለሚቀርብልህ ማንኛውም ጥያቄ መልስ ለመስጠት ይረዳሃል። በአንተ አገላለጥ ቀጥተኛ የሆነ ትዕዛዝ እየሠጠሁህ አይደለም። የእምነት ሰባኪ በጽድቅና በኩነኔ መካከል ያለውን ልዩነት ያስረዳሃል እንጂ ይህንን ተከተል ያንተው እያለ አያስገድድህም። የተሻለውን መምረጥ የአድማጩ በመሆኑ የመምህሩ ድርሻ ሁለቱን በንጽጽር ማስረዳት ነው። በሁለቱ መካከል ያለውን ልዩነት





አስረዳሃለሁ። የተሻለውን መምረጥ የአንተ ድርሻ ስለሆነ በዚያ በኩል አልጨነቅም። አባባሌ ግልጽ ካልሆነልህ ልትጠይቀኝ ትችላለህ።" ወፍራም ክንዱን ከትከሻው አንስቶ ትክ ብሎ ተመለከተው።

አውቀህ ግባ ማለት ምን ማለት ነው? አልቀጥልም ቢላቸው እንደ ሰለጠነ ፖለቲከኛ አትገደድም ብለው ያሰናብቱታል? ወይስ... በፍጹም የማይታሰብ ጉዳይ ነው።

ለሰጠው ምክር መልስ ከመስጠት ይልቅ ዝምታን በመምረጡ እይታውን ወደ መድረኩ አደረገ። ይዞት የመጣው ሰው ከጐኑ ከነበረው ሰው ጋር በጥልቅ ውይይት ላይ ነበር። የሌዘር ጃኬት የለበሰው ሰው ወደሱ አቅጣጫ እየደጋገመ ይመለከታል። ወደሱ አቅጣጫ እየተመለከተ በመሆኑም አንድ ነገር እየነገረው እንደሚሆን ገመተ። ሁለቱም ሰዎች ወደሱ አቅጣጫ እየተመለከቱ በሹክሹክታ እየተነጋገሩ ናቸው። ከአጠገቡ የነበረው ሰውም ውይይት አልቀበተ አለዚያም ረስቶት የሱም እይታ እሱ ከሚመለከታቸው ሁለቱ ሰዎች ላይ ሆኖ ነበር።

"ከውጭ አንድ ሰው በመምጣት ላይ ስለሆነ የምትጠይቀኝ ነገር ካለህ? መድረኩ ክፍት ነው። በተወያየንባቸው ዙሪያ ያልገባህ ካለ ዕድሉን ልስጥህ ብዬ ነው።" ጸጥታውን በድንገት ገመሰው።

"ከተጠቀምኩባቸው ከበቂዬ በላይ ይመስለኛል።" ትክሻውን እንደ ማንጠር አደረገ ዘሩባቤል።

በሩ ተከፈተና አንድ ሰው ወደ ውስጥ ገባ ሸክ ብሎ ለብሷል። እያንዳንዳቸው የሚመጡበት ሰዓት የተለመደና ተመሳሳይ እንደ ሆነም ገባው። በሩን ከውጭ የሚከፍቱበት ተመሳሳይ ቁልፍ አላቸው።

ሲገቡ የሚያሳዩት ተግባርም እንዲሁ የተመሳሰለ ነው። የከፈቱትን በር በዝግታ ዘግተው ይቀልፉና ለአንድ ደቂቃ ያህል ቆመው ሁሉንም ነገር በማጥናት በአዳራሹ መቀመጫ ፈልገው ይቀመጣሉ። ሲቀመጡም ቢሆን እጅግ ተረጋግተውና ሁሉንም ነገር በጥንቃቄ ተመልክተው ነው። በማንኛውም እንቅስቃሴ ላይ ይጠነቀቃሉ።

ሥነ-አዊ ባሕርያቸው በዚህ መልኩ የተገነባ ሳይሆን አይቀርም። የአዳራሹን ዙሪያ ክብ በጥንቃቄ ሲቃኝ ቆይቶ በአንድ ጥግ በኩል ብቻውን ከነበረ ሰው አጠገብ ተቀመጠ። ስብሰባው ወደ መጠናቀቁ ሲደርስ ሲል የአዲስ መጪዎቹ ቁጥር ከሰዓት ወደ ሰዓት እየጨመረ መምጣት ለምን ይሆን? መጥተውም ምንም የሚሉት ነገር የለም።

"እየጠበቅኸኝ ነበር መሰለኝ" ከጎኑ ተስተካክሎ ከተቀመጠ በኋላ እንግዳውን እየተመለከተ ጠየቀው አዲስ መጪው ሰው።

"ከተለመደው ሰዓትህ የዘገየህ መሰለኝ" ሰውየው መለሰለት።

"ጠዋት ነበር ስብሰባ ስለ መኖሩ የተነገረኝ። በስብሰባው ላይ አንድ እንግዳ እንደሚገኝም ተገልጦልኝ ስለ ነበር አንተን አስታወስሁ።

እንግዳው ወንድማችን ይህ መሆን አለበት፡፡ ከአንተ ጋር መሆኑን ስመለከት በጣም ተደስቻለሁ፡፡ ማብራሪያውን በሙሉ አስረዳኸው?" እንግዳውን እየተመለከተ በሹክሹክታ አናገረው አዲሱ የገባው ሰው፡፡

"ቅድመሁኔታዎችን ነግሬዋለሁ፡፡ የሚቀረውን አንተ አስረዳው" እሱም በተመሳሳይ ፊቱን ወደ እንግዳው እየጠመዘዘ መለሰለት፡፡

የሚቀረው ማብራሪያ ምንን በተመለከተ ይሆን? ሲል እንግዳው ራሱን እየደጋገመ ለመጠየቅ ተገደደ፡፡

"እንደምታስረዳው ስለገመትሁ ከኔ ጋር ባይወያይ መርጬ ነበር" በተረጋጋ ስሜት እያስተዋለው መለሰለት፡፡

"በአለፈው ስብሰባችን እንደምመጣ ነግሬህ ነበር እኮ ይቀራል ብለህ ሰግተህ ነው ስልክ የደወልክልኝ!" አለና ሳቅ ሲል ፍንጭቱ ታየ፡፡

"የሚገጥምህን ነገር ስለማላውቅ ነው የደወልኩልህ፡፡ በዚያም ላይ እንደዚህ በተፋጠነ ሁኔታ ይሳካለታል ብለህ እንደማትገምት አስብ ነበር፡፡"

"ያልከው ኃሳብ በልቤ ውስጥ ሲያጭር ነበር የሰነበተው፡፡ ቢሳካልህም በተፋጠነ መልኩ ይሆናል የሚል እምነት አልነበረኝም፡፡ በተለመደው የተረጋጋ ስሜቱ ፊቱን በትኩረት እየተመለከተ መለሰለት፡፡

"አመሰግናለሁ፡፡" እንደ መሳቅ ብሎ ትከሻውን ለአመል ያህል በመዳፉ መታ አደረገው፡፡

"የምትለውን በተግባር ላይ የሚያውለው ይመስልሃል?" እንግዳውን ሰው በግዴለሽነት እየተመለከተ ጠየቀ፡፡

"ወደ ፊት የሚታይ ይሆናል" ወደ እንግዳው በግማሽ እየተመለከተ መለሰለት፡፡

"የምቾት ኑሮን የሚጠላው አይመስለኝም፡፡ እሱስ ምን ይላል"፡፡ የሰውየው ሁኔታ ከሽማኔ መወርወሪያ የፈጠነ ነው፡፡

"የገመትኩት አንተ ከምትለው ተመሳሳይ ነበር"፡፡

እነዚህ እብዶች ስለ ምን እያወሩ ናቸው የለየላቸው ወፈፌዎች ለመሆናቸው ተግባራቸው ይመሰክራል ሲል ለራሱ አረጋገጠ ዘሩባቤል፡፡

"ያስቸግራል የሚል ግምት አድሮብኝ ነበር" በትከሻው ላይ ተንጠራርቶ የእንግዳውን ፊት ትክ ብሎ ተመለከተው፡፡

ዘሩባቤል በተስፋ መቁረጥ ስሜት ተወጣጠረና ቢሰድበው ወደደ፡፡ ያም ሆኖ እንደዚያ አላደረገም፡፡ የመጣውን ነገር በትዕግሥት መቀበል ይኖርበታል፡፡ ያለው ከነብር ስርግ ውስጥ ነው፡፡ መናገር የሚገባውን ከመናገሩ በፊት ማሰብ ስለ ነበረበት ዝምታን መረጠ፡፡ 'ከወደቁ በኋላ መፈራገጥ ለመላላጥ ነው' የሚለው የአባቶችን ተረት አስታውሶ በውስጡ ፈገግ አለ፡፡ ዝምታ ለጊዜውም ቢሆን ትክክለኛ ምርጫ ነው፡፡ ለመናገር አስገዳጅ ሁኔታ እስከ አልተፈጠረ ድረስ ልክ እንደቆቅ አንገቱን ወደ ውስጡ መቅበር ይኖርበታል፡፡





"ወደ አሜሪካ ለመብረር ፓስፖርቱን አስመትቶ እንደ ነበር ነግሮሃል?" ዓይኑን ከእንግዳው ሳይነቅል ጓደኛውን ጠየቀው፡፡

"አልነገረኝም፡፡ እንደዚያ አስቦ ነበር እንዴ?"ሲል ጠየቀው፡፡

"ይህንን አታውቅም ነበር እንዴ?" አንገቱን የበለጠ እያረዘመ በስሜት እየተጫነው ወሬውን ቀጠለ፡፡

"የተረበሸ ስለ መሰለኝ ይህንን ጥያቄ ለጊዜው ትቼው ነው እንጂ ለመብረር ተዘጋጅቶ እንደ ነበር አውቃለሁ፡፡"

"በርግጥም የምትናገረው ትክክል ሊሆን ይችላል፡፡ በድንገት ሲመጣ ቢረበሽ አይፈረድበትም፡፡"

እንደ ግኡዝ ነገር አስቀምጠውት ያለምንም ይሉኝታ እየተነጋገሩበት ነው፡፡ እነዚህ ወፈፌዎች ስነ ልቦናዬን ለማቃወስ እየጣሩ ናቸው ሲል አሰበ፡፡ የአስተሳሰብ ምህዋሩን በማቃወስ ሊያሳብዱት እየጣሩ ናቸው፡፡ ከአጠገባቸው በተቀመጠ ሰው ጉዳይ እየተነጋገሩ ፍጹም የማይሰማ ማስመሰላቸው የተራቀቁበት አደገኛ ውንብድናቸው መሆን አለበት፡፡ በርግጥም የአስተሳሰብ ምህዋሩን ጭምር እያናጉበት ስለመሆናቸው አልተጠራጠረም፡፡ ከወሮበላ ቡድን ከዚህ የተሻለ የሚጠበቅ ነገር ባይኖርም እጅግ ተበሳጨ፡፡ ስለሱ በሚያወሩበት ወቅት አጠገባቸው እንደ ነበረ ሰው ሳይሆን ፍጹም በሌለበት የአንድን ሰው ህፀፅ እየነቀሱ የሚያብጠለጥሉ ነው የሚመስሉት፡፡ ጠማማው አስተሳሰባቸውን ሊረዳ የሚችለው አባታቸው ሳጥናኤል ብቻ ነው፡፡ እንደዚህ ያለው አመለካከት ለማንም የሚገባ አይደለም፡፡

"በአሜሪካንና በእንግሊዝ የስለላ ድርጅት ውስጥ በጥምር ስለምትሠራው ፍቅረኛው አንስተህበት ነበር" ፊቱን በቅሬታ ከስክሶ እንግዳውን እየተመለከተ ጓደኛውን ጠየቀው፡፡

"በዚህ ዙሪያ አልተነጋገርንም፡፡ እረጋ እያልን ብንነጋገር ይሻላል በማለት ነው እስከ አሁን ያላነሳሁበት፡፡ በጥብቅ እንደሚፈለግ ስነግረው ተረብሾ ስለ ነበር ጥያቄ እያበዛሁ ላስጨንቀው አልፈለግሁም፡፡" ታዛዥነትን በሚያበስር የድምጽ ቃና መለሰለት፡፡

"ጓዳችን ይዞት መጣ ወይስ አንተም አብረህ ሄደህ ተቀበልከው?" መንቀባረሩ እየጨመረ ነበር፡፡

ዘሩባቤል ግራ እየተጋባ ነው፡፡ ወደ አሜሪካ ሊሄድ መዘጋጀቱን ለማንም እንዳልነገረ ያውቃል ምን መንፈስ አምጥቶ ነገራቸው ታድያ? ይህ የማይታመን ጉዳይ ነው፡፡ እነዚህ ሰዎች እንዳሉትም የሚንቀሳቀሱት በመንፈሱ መሆን አለበት፡፡

"ብቻውን ነው ይዞት የመጣው፡፡ እኔ ከዚህ የደረስኩት እነሱ ከገቡ ትንሽ ሰዓት ዘግየት ብዬ ይመስለኛል፡፡"

"ይዞት ሲመጣ መንገላታት እንዳልደረሰበት ነግሮሃል? አልሄድም

በማለት አበሳጭቶት ከሆነ ለምን አትጠይቀውም” አንገቱን እያስረዘመ የበለጠ ተጫነው።

“የደረሰበት ችግር አልነበረም። እስከዚህ ድረስ የመጣው በራሱ ፈቃድ መሆኑን ነግሮኛል።”

“ትህትና ያላቸው እንግዶች በሚመጡበት ጊዜ ከፍተኛ እንክብካቤና ለጤንነታቸውም ልዩ ጥንቃቄ የማድረግ ኃላፊነት እንዳለብን መዘንጋት የለበትም። ሕግና ደንባችን የሚያዘን ይህንኑ ቀና አስተሳሰብና ሥነ-ምግባር ነው። ጥሩ የሆነ ሥነ-ምግባር ማሳየትና ማስተማር እንደኛ ካለ አካል የሚጠበቅ ነው።”

“እየነገርኩት ያለሁት ይህንን ነበር። ድርጅታችን ለሰው ልጅ ሰብአዊ መብትና ጤንነት ምን ያህል ግምት ሰጥቶ እንደሚሰራ ሳስረዳው አምሽቻለሁ። እሱም ቢሆን እንዲህ ያለው ምክር የሚገባው ሆኖ ነው ያገኘሁት።”

“በራሱ መኪና ነው የመጣው አልከኝ?” እየተጀነነበት ጠየቀው።

“መኪና ይዟል። ይከራያት ወይም እራሱ ይግዛት የማውቀው አለዚያም የጠየቅሁት ነገር የለም።”

“መኪና የሚገዛ አቅም አለው ብሎ መገመት የሚከብድ ይመስላል። ተከራይቷትም ይሁን ተውሷት ጉዳዩ የራሱ ስለሆነ በዚህ ዙሪያ ትኩረት መስጠቱ አስፈላጊ አይመስለኝም።”

“ያችን ወፈፌ ጓደኛውን የሚያክለፈልፋት ምክንያት ምን እንደሆነ መጠየቅ ነበረብህ። ስለሷ ጉዳይ በደንብ ማወቅ ይኖርበታል። እብደቷን አቁማ የማትቀመጥ ከሆነ መጨረሻዋ ሞት ነው የሚሆነው። ያገኘችውን ሁሉ እየነካካች የምትበጠብጥበትን እጇን ልትሰበስብ እንደሚገባት ሊመክራትና ሊያስጠነቅቃት ይገባዋል። እሷን ካጣ ኃዘኑ ሊከብድበት ይችላል።”

“ሁሉንም ነገር ልናስረዳው እንሞክራለን” ወደ እንግዳው ፊቱን አዙሮ እየተመለከተው መለሰለት የመጀመሪያው ሰው።

የአዕምሮ ችግር ይኖርባቸው ይሆን? ሲል አሰበ ዘሩባቤል። ከአጠገባቸው ተቀምጬ እያለሁ በሌለሁበት የማማት ዓይነት ወሬ ምን ዓይነት ጋጠወጥነት ይሆን ሲል ራሱን ጠየቀ። ሁኔታቸው ሁሉ እሱ ከሚገምተውና ከሚያስበው በላይ መጥቆ የወጣ ነው። ድንጋዩን ዳቦ ብለው ሊያሳምኑት እየሞከሩ ናቸው። ያደረባቸው እርኩስ መንፈስ እንዳለ ያጠራጥራል። መረን የወጣው እብሪታቸው እንዳስከራቸው ተረዳ። እብሪተኛ ቁራኛቸው ከጋጠወጥነት ወደ ሞልቃቃነት ከሞልቃቃነት ወደ ወፈፌነት የሚለዋወጥ ኪናዊ ድራማ እየተወነባቸው ነው።

“ጓደኛው ያልበላትን የምታክክ ዓይነት ሞጥሟጣ መሆኗን ተረድቶ አደብ እንድትገዛ መምከር ይኖርበታል። እንደዚያ ካላደረገ የሷ





መዘዝ ለሱም እንደሚተርፈው ልናስረዳው እንሞክራለን” አለ ሰውየው።

“በቀጥታ እኔኑ አናግረኝ” ሊለው አሰበና በተለመደው ትዕግሥቱ ዝምታውን ወደደ ዘሩባቤል።

“እናስረዳዋለን። ይገባዋል የሚል ግምት አለኝ። የድርጅቱን ሕግና ደንብ ማወቅ ይኖርበታል። ደንቡን ጥሶ ቢገኝም ዕድሜ ልክ ዘብጥያ እንደሚወርድ በጥሞና ማስረዳት የኛ ድርሻ ነው። ጓደኛውን በተመለከተም ከሱ የሚቀርባት እንደሌላት ተገንዝቦ ከድርጊቷ እንድትታቀብ ሲያስጠነቅቃት ይገባዋል። መንቀዥቀዧን ካላቆመች የፀሐይ ጨረር ሳታይ ተቀብራ ትበሰብሳለች። በዚህ ከቀጠለች የሚጠብቃት ይህ ብቻ ነው። በጣም እየፈጠነች ያለች ቢራቢሮ ሆናለች። የሳት ራት።

ለእንጀራዋ የሚበቃትን ያህል መሥራት ይኖርባታል። እንደ ቀበጥ አይጥ በተከፈተው ሁሉ አንገቷን የምታስገባ ከሆነ መጨረሻዋ መታነቅ ነው። እወድሻለሁ አፈቅርሻለሁ... እያለ በቃላት መሸንገሉ ፋይዳ ቢስ ነው። የሚወዱትን ሰው ከአደጋ ለመጠበቅ እንደ መጀመሪያ እርዳታ የሚቆጠረው የወዳጅነት ምክር ነው። መምከር ይገባዋል ፊቱን ከእንግዳው መልሶ ጓደኛውን አስተዋለው።

“መኪናዋ የራስህ ነች ወይስ ተከራይተህ?” ትከሻውን ጨመቅ አድርጎ እየያዘ ጠየቀው።

“ተከራይቼ ነው።” ትከሻውን ለማስለቀቅ እየሞከረ መለሰለት ዘሩባቤል።

“ለምን እንደምትከራይ አልጠየቁህም? ወደዚህ ስትመጣ መኪና መከራየትህ ትልቅ ስህተት ነው።”

“እውነተኛውን ቦታ አልነገርኳቸውም።”

“ምን ምክንያት ሰጣኃቸው ከረሜላ እገዛላችኋለሁ ገበያ ደርሼ ልምጣ ብለህ እንደ ሕፃን አሞኘኻቸው”።

“ቤተሰብ ወደ ውጭ ለመሸኘት ኤርፖርት ልሄድ እንደሆነ ነው የነገርኳቸው።”

“እንደዚህ ያለ ምክንያት መስጠት አልነበረብህም። ወደ አውሮፕላን ጣቢያ በመሄድ ፈንታ ወደዚህ ስትመጣ ብትታይ አከራዩ ድርጅት ሊጠራጠርህና ክትትል ሊያደርግብህ ይችል ነበር። ለምንድነው መዋሸት የፈለግኸው? የምትሄድበትን በትክክል መንገር ነበረብህ። ውሸት በጣም መጥፎ ነገር ነው። መዋሸት ያስቀጣል። ከአሁን በኋላ አቅጣጫ የሌለው ውሸት እንዳትዋሽ። ወደ ፒያሳ እየወጣህ ወደ ቦሌ መሄዴ ነው ብሎ መዋሸት ምን ማለት ነው? ለምን ሊመስል የሚችል ውሸት አትዋሽም?። ውሸትም በመንገዱ ከሆነ ከእውነት ይቆጠራል።” ኮስተር ብሎ አስተዋለው።

“ባይታመንም የሚሻለው ይህ ብቻ ነው።”

ሰውየው እንደ ተረዳው ለመራስ ብዙ መታጀል እንዳለበት ነው። በጀመሩት የምርመራ ዘዴ ልቡን እንደ ጨው ለማቅለጥ የተጠቀሙበት

ዘዴ ያልሠራ መሆኑን ተገነዘበ። በቀላሉ የሚገባው አይደለም።

"የተናገርከውን ማለት አልነበረብህም።" አለ ሰውየው።

"በደንብ መገራት የሚያስፈልገው ይመስላል። እናሸዋለን" አለ የመጀመሪያው ሰው።

"ጓደኞቹ መኪና እንደ ሽሚዝ ይቀያይራሉ። እሱ በትውስት መኪና ይሄዳል። ግትር" አለው ሳቅ ብሎ።

"እኔም የተረዳሁት ይህንኑ ነው።" አለ የመጀመሪያው ሰው።

ይዞት የገባው ሰው በተቀመጠበት እንዳለ እጁን ከፍ አድርጎ የሆነ ምልክት ሲሰጣቸው እርስ በርስ ተያይተው በሃሳብ ተነጋገሩ። የመጀመሪያው ሰው ከተቀመጠበት ተነስቶ እነሱ አጠገብ የደረሠው በኩራት እየተጀነነ ነበር።

"ወደ ውጭ ወጥተን የምንወያየው አለን" የጎድን እየተመለከተ ትዕዛዝ ሲሰጠው ዘሩባቤል ግራ ተጋባ።

"የአእምሮ ምግብ ስለሚያሥፈልግህ ከአሁን በኋላ ያለውን ጊዜህን በመዝናናት እንድታሳልፍ ተፈቅዶልሃል። ወደ አንድ የምሽት ክበብ ትሄዳለህ።" አለው ከጐኑ የነበረው ሰው።

የምሽት ክበብ ምን ማለት ይሆን? ይህ ቃል የኮድ ቃላቸው ሊሆን ይችላል። የተለያዩ ተግባራትን እየፈጸሙ ሊያስቃዩት እንደሆነ ገባው።

"ውጭ ወጥተን ትንሽ የምንነጋገረው ጉዳይ ይኖረናል።"

የተቆራረጡ ቃላቶች በጥርሱ መካከል አፈትልከው ቢወጡም ያለውን በትክክል ለመስማት ያስቸግር ነበር።

"ስብሰባው አብቅቷል እንዴ?" አለ ዘሩባቤል።

"ከኔ ጋር ሌላ ቦታ ጉዳይ ይኖረናል። በሚኖርህ ቆይታ ሁለታችን የምናከናውናቸው ጉዳዮች አሉን።" ወደፊት ሲቀድም ከተቀመጠበት ተነስቶ ተከተለው።

በኮሪደሩ በግራ በኩል ከታጠፉ በኋላ እንደገና ወደ ቀኝ በመዞር ጎን ለጎን እየተራመዱ በደረጃው መውረድ ጀመሩ።

የሕንፃው ደረጃ ሲገቡ የወጡበት አይደለም። አራትና ከዚያም በላይ ሰዎችን በአንድ ጊዜ የሚያስተላልፍ ሰፊ ደረጃ ነው።

ያመሩት ወደ መኪና ማቆሚያ ፓርኩ ነበር። ተጠጋግተው ከቆሙት የቤት መኪናዎች ጥቁር ቀለም ያለውን ማርሴዲስ ከፍቶ እንዲገባ ጋበዘው። በጥንቃቄ አሽከርክሮ ወደ ዳር ካወጣት በኋላ ወደ መውጫው በር ሲጠመዝዛት በትኩረት እየተከታተለው ነበር።

የት እንደሚሄድ መገመት ባይችልም ለማሽከርከር አልተደናገረም። የታዘዘውን ያለመደነጋገር የሚፈጽመው ልክ እንደ ለማዳ ውሻ ነው።

"የት ነው እየሄድን ያለነው?" አለ ዘሩባቤል።

"ወደ ፊት ነው ዝም በልና ንዳ" ሲል ገሰፀው።





"መልካም ነው" አለው ሳቅ ብሎ።

"በፍጥነት ንዳ።" አለው ከረር ባለ ድምጽ።

"እሺ እነዳለሁ" አለው ያለተቃውሞ።

"ቀኝህን ያዝና ታጠፍ። እንደ ኤሊ ተንቀርፍፈሃል።" ወደ ጆሮው ተጠግቶ ሲያንሾካሽክበት ውስጡን ረበሸው ።

የነዳጅ መስጫውን በኃይል ተጭኖ እልህ በተቀላቀለበት ስሜት አስፈተለካት። ብዙ ከሄዱ በኋላ ወደ ግራ የሚታጠፍና ወደ መንደሩ የሚገባ መንገድ አገኙ። ፍጥነቱን ሳይቀንስ ከድንጋይ ንጣፉ በተሠራው መንገድ ሲጨምራት መላ አካላቷ እንደ አሮጌ እቃ ተንኳኳ። እየተንቃቀለች በየጎዳናው ስትወድቅ ቢመለከት ግድ አልነበረውም። በነበረው ፍጥነት ቀጠለ። ወደ መንደሩ በገቡ ቁጥር አካባቢው በጥቁር ጨለማ ተውጦ በድንጋይ የተነጠፈው መንገድም የበለጠ እየጠበበ መጣ የመኪናዋ መብራት ጥቁሩን ጨለማ እንደ መብረቅ እየሰነጠቀው ቢሆንም ትርክምክሙ ሰፈር ከመቃብር የከበደ ጨለማ ነው።

ወደ ግራው ታጥፎ አስፋልቱን እንዲይዝ ነገረው። የተባለውን አደረገ። "አስፋልቱን ልቀቅና ወደ መዝናኛው ተጠጋ መደነጋገር የለብህም። እንደ ሠለጠነ ሰው ማሰብ እንደ ለማዳ እንስሳ መሹለክለክ አለብህ። የምንሄደው ከአንተ አስተሳሰብ ውጭ ወደ ሆኑ የተለያዩ ፍጡራን ነው" ስለ ምን እንደሚያወራ አልገባውም ዘሩባቤል።

"የምንሄድበት ደርሰናል ማለት ነው?" አልመለሰለትም። ፍጥነቱን ቀንሶ ከአስፋልቱ ዳር አንሸራትቶ እንዲያቆማት ምልክት ሰጠው።

ሽጉጡን እያስተካከለ እንዲወርድ ሲነግረው ፍጥነቱ ሳያስደንቀው አልቀረም። ፈጠን ብሎ በመውረድ በሚነግረው አቅጣጫ ቀደመ። ወደ ምሽት ክበቡ ተጠግተው ከበሩ ላይ ሲደርሱ የጥበቃ ሠራተኛው በታላቅ ትህትና ጎንበስ እንደ ማለት ብሎ ወደ ውስጥ እንዲገቡ በእጁ ጭምር ምልክት እየሰጠ ጋበዛቸው።

ወደ መጡበት አቅጣጫ ፊቱን መልሶ እየተመለከተ

"ከበሩ ላይ ኃይለኛ ፍተሻ አለ። ቀልጠፍ በል።" ሲል አስጠነቀቀው። ሁሉም ነገር ከሰዓት ወደ ሰዓት እየፈጠነ ነው።

"እንዳታስደነግጣት..." ወደ ፈታሹ አንገቱን በማቅረብ ነገረው።

ፈታሹ የተነገረውን ለማክበር ሳይፈትሽ ነበር ያሳለፈው።

"ከሚደንሱት ሰዎች መሃል መቀላቀል አለብን። ከኋላችን የጸጥታ ሠራተኞች እየተከታተሉን ናቸው። በመንገድ ላይ እንዳለን በመኪና እየተከታተሉን እንደ ነበር እጠረጥራለሁ። በጉራንጉሩ መንገድ ስንመጣ አንድ መኪና በቅርብ ርቀት እየተከተለን ነበር። ከሚደንሱት ሰዎች ጋር በተረጋጋ መንፈስ መደነስ አለብህ" ከጐኑ እየተራመደ ቃላቱን አንዱን በአንዱ ላይ በመደራረብ ያጣድፈው ያዘ።

"ደኅንነቶቹ የሚከታተሉን..." አቋረጠው፡፡

"እንዲህ ያለው ሁኔታ አንተን የሚያሳስብህ አይደለም ዝም በልና የተባልከውን አድርግ" ስለ ሁሉም ነገር ለማወቅ አትቸገር፡፡ የደህንነቶቹ ጉዳይ አንተን የሚያስጨንቅህ አይሆንም፡፡" ትከሻውን በትከሻው ገፍትሮ ወደ ፊት እየገፋው በጨለማ ወደ ተዋጠው አዳራሽ ይዞት ገሰገሰ፡፡

በአዳራሹ በተለያየ አቅጣጫ ያለው እንቅስቃሴ መጠነኛ መሟሟቅ እያሳየ ነው፡፡ ውስጡም ከሲኦል ይከፋል፡፡

"ለምን?..." አሁንም ኃይለኛ የትከሻ ግፍተራ አቅምሶት አቋረጠው፡፡

አስገራሚ ነው ፍተሻውን ያለፈው ፍቅረኛው እንደሆነ ለፈታሹ ነግሮ ስለ ነበር ዘገነነው የግብረ ሰዶማውያን መናኸሪያ ነው ማለት ነው፡፡ እኔ የማላውቃቸው ከየት ስለመጡት ደኅንነቶች ነው እየነገረኝ ያለው? ሲል አሰበ፡፡ እኔ ምርኮኛው ስለሆንኩ ደኅንነት አልመሰልኩትም፡፡

"ጥያቄህ ይገባኛል፡፡ ያም ሆኖ አንተን ለማስረዳት ቆሜ የምነታረክበት ጊዜ የለኝም..." እየገፈተረ ከቀለጠው ዳንስ ውስጥ ይዞት ከገባ በኋላ እጁን ይዞ ያስደንሰው ጀመር፡፡





# ምእራፍ አስራ አራት

ከወንበር ነጻ የሆነው ሰፊ የክበቡ አዳራሽ በዳንኪራ ቀልጦ አንዱ አንደኛውን አይመለከትም፡፡ ጽልመቱም የሲኦል ተመሳሳይ ነበር፡፡ የተለያየ መጠን ያለው ቀጭን ወፍራምና ረጅም ሳቅ፡፡ ፉጨት ኡኡታና የለቅሶ ዓይነት ዜማ... ያንን በጥልመት የተዋጠ አዳራሽ አስጨንቆት ሊፈነዳ የተቃረበ አስመስሎታል፡፡ የሽቶ የሲጋራና የአሸሸ ሽታ ከሰዎች ጠረን ጋር ተደበላልቆ እንደ እሳተ ገሞራ ጭስ ሲትጉለጉል ጠረኑ አፍንጫውን ተነፈገው፡፡

ራሱን የሳተ ያህል እየተሰማው ግራ ቀኙን ለማየት ሞከረ፡፡ የማይሆን የማይታሰብ ከንቱ ሙከራ ነበር፡፡ የመብራቱ ቀለም የአንጐል ድሮችን የመበጣጠስ ያህል ኃይል አለው፡፡ የተደበላለቀው ጠረን ሳይጠጡ አስክሮ ሳያብዱ ጨርቅን ያስጥላል፡፡ ሁሉም አብዶ ጨርቁን ጥሎ ዳንኪራውን ያስነካዋል፡፡ የምጽአት ቀን መዳረሻ እስኪመስል ድረስ ዓለም ጸጥታዋ ደፍርሶባታል፡፡ ሳቅ፣ ለቅሶ፣ ኡኡታ፣ እልልታ ሁሉም ይሰማል፡፡ የሲኦል ደጆች ተከፍተው የተጠሩት ርኩሳን መናፍስት ወደ ውስጥ ይጎርፋሉ፡፡ ስስ የጡት ማስያዣ ቀጫጭን ኃፍረትን ያልሸፈነ ፓንት ለአመል ያህል በሴቶቹ ኃፍረት ላይ ቢኖርም አንዳንዶቹ በስልት እያወለቁ እያንሸራተቱ ወደ ሕዝቡ ይወረውራሉ፡፡

"ደንስ በደንብ ደንስ..." ሁለት እጁን ይዞ እንዲደንስ እየመራው ያመናትለው ጀመር፡፡ የዓለም ክፋቷ ሁሉ ተጠራቅሞ በዚያ የተከመረ መሰለው፡፡ ሰዶመ ገሞራውያን እዚህ ይገኛሉ፡፡

"ግራ ቀኝ አትመልከት፡፡ የራስክህን ለራስህ ተግብር በዚህ ስፍራ እርስ በርስ መተያየት ፋራ ያስመስላል፡፡"

የአሸሹ ሽታ ሳይሆን አይቀርም በኃይል ሲተነፍገው እየደጋገመ አስነጠሰውና አይኖቹ እምባ አቆረዘዙ፡፡ ነገር ግን እጁን ይዞ እያስደነሰው ነው፡፡ እምባር መዋያውን ከሽጉጡ ጋር በአንድነት አጥብቆ ስለ ያዘው ሕመም እየተሰማው ነበር፡፡ ዳንስ የሚያለማምድ በሚመስል አኳኋን ሲያወዛውዘው አብሮት ስልቱን ተከትሎ ይመናተላል፡፡

"ግራ ቀኝ በጥንቃቄ እየተመለከትህ ደንስ፡፡ ሁሉን ነገር በጥንቃቄ ተመልከተው፡፡"

"ስፍራው ምን ተብሎ እንደሚጠራ ታውቃለህ? ተሰሎንቄ ነው፡፡ የግሪክ ጥንታዊ ከተማ እንዳትመስልህ አይደለችም፡፡ የሚመሳሰሉት በስምና በግብር ብቻ ነው፡፡ ተሰሎንቄን ያፈረሳት ሐዋሪያው ጳውሎስ እንደ ነበር ቅዱስ መጽሐፍ ይተርካል፡፡"

"ለምንድነው የምመለከተው?" ግራ ተጋብቶ ጠየቀው ዘሩባቤል፡፡

"የምታያቸው ሰዎች ክላሉ ነው ወደዚህ ያመጣሁህ... ሁሉንም

ነገር በጥንቃቄ ተመልከት። መድረኩንም አሻግረህ እየው። አልገባህም አይደል? ሁሉም ነገር እያደር ይገባሀል። ፈታሹ ለምን እንዳልፈተሸህ ታውቃለህ? ፍቅረኛዬን እንዳታስቸግርብኝ ስለአልኩት ነው" ቃሉን ሲሰማ ዘገነነው።

"ምን ዓይነት ሰዎችን ነው የምታሳየኝ?"

"ሟርተኞቹን። የተለያዩ ሟርተኞች መድረክ ላይ ናቸው። አብዛኛዎቹ ሟርተኞች ጨርሰው አልገቡም። ትንሽ ቆይተው ተጠናቅቀው ስለሚመጡ ሁሉንም ታያቸዋለህ። የምንገኘው ሁለተኛውና የመጨረሻው የሰዶም ከተማ ውስጥ ነው። የኖህ ከተማም በዚሁ ትገኛለች።"

"የምን ሟርት ነው የምትነግረኝ?። በዳንሱ መሃል በተቆራረጠ ድምጽ ሰውነቱ በፍርኃት እየተሽማቀቀበት ጠየቀው ዘሩባቤል።

"አሁን የምትመለከተውን ዓይነት ሟርት ነው የምነግርህ። እያደረግህ ያለኸው ምን ይመስልሃል? ሟርት አይደለም እንዴ? ፍጠን በደንብ ለመደነስ ሞክር። በደንብ ማሟረት አለብህ።"

"ሟርት እያለማመድከኝ ነው ማለት ነው?" በመገረም አለዚያም በመበሳጨት ጠየቀው ዘሩባቤል።

"አይደለም። እኔ ሟርቱን እያሳየሁህ ነው። የኔ ድርሻ ማሳየት ብቻ ነው። ከተመቸህ ራስህ ትለማመደዋለህ። አሁን ግን ፍቅረኛዬ ነህ።" ይህንን ቃል በመድገሙ ተበሳጨ።

"ለምንድነው ይህንን እንዳይ የምታደርገኝ?" ምክንያቱን ለማወቅ ጠየቀው።

"ልታየው የሚገባህ ፍሬ ነገር ነው። በደንብ አድርገህ ተመልከት። ስምና ምግባሯ የማይጣጣም ሀገር እንዳለችህ ማወቅና መረዳት አለብህ" ኮስተር አለ። "ማወቅ የለብህም እንዴ? ቅር ካለህ ቅራሬ ጠጣ። ቅራሬ ታውቃለህ? ጠላው አልቆ ውኃ ተጨምሮበት የሚጠጣ ነው።"

"ማወቅ ያስፈልገኛል ማለት ነው?"

"ማወቅ የለብህም? የጸጥታ ሠራተኛ አይደለህም እንዴ? አንድ የመረጃ ባለ ሙያ በሀገሩ ውስጥ ያለ ማንኛውንም ነገር የማወቅ ኃላፊነት እንዳለበት እንዴት አልተረዳህም?" "ፍቅረኛሞች እየገቡ ናቸው" በትክሻው አሳልፎ ወደ በሩ አቅጣጫ እየተመለከተ ተናገረ።

"የሥራ ፈቶችና የወሮበላዎች ተግባር ነው።"

"ተሳስተሃል። አገርን ከአደጋ ላይ ሊጥሉ የሚችሉ አደገኛ ሰዎች ተፈልፍለው የሚወጡት እንደዚህ ካለ ቦታ ነው። የተጣለባቸውን ኃላፊነት ትተው ሕዝብን የሚበድሉም የመሸሸጊያ ዋሻቸው በዚሁ ውስጥ ነው። ሁሉንም በዚሁ ታገኛቸዋለህ። እየገቡ ያሉትን ተመልከት።" ትክሻውን አሽከርክሮ ወንበሩን መለሰው።

"አልገባኝም" የትኞቹ በዳዮች ናቸው በዚህ ስፍራ የሚሸሸጉት





እነዚህስ ምን እየሆኑ ናቸው?" ከውጭ ወደ ውስጥ እየገቡ ያሉትን ሰዎች ተመለከተ።

"በሰሩት ተንኮል መንፈሳቸው የተቃወሰባቸው በሙሉ በዚህ ስፍራ ይገኛሉ። እነዚህ ግን ቀውሶች አይደሉም። የሚሠሩትን ያውቃሉ።"

"በርግጥ በዚህ ቦታ የተገኘ ማንኛውም ሰው እንዳልከው ትክክለኛ መንፈስ አለው ለማለት ይከብዳል።" በጥንድ ተቃቅፈው የሚላላሱትን ሰዶማውያን ሲመለከት ልቡን አጥወለወለው።

"እየደነስህ... እየደነስህ ... እእ እየደነስህ የምትጠይቀኝን ጠይቀኝ። እኛውልህ በርካታ ሰዎች በበሩ በኩል እየገቡ ናቸው። ሁሉም ከሴት ጋር ነው የመጡት። ሴቶቹን እስከሚያገኙ ነበር የዘገዩት። እየነገርኩህ ያልኩት በጥንድ እየገቡ ስላሉት ነው። ሴት ለሴት ወንድ ለወንድ።

"አ . . . እእ አምላኬ ምን እየተሠራ ነው ያለው እባክህ ከዚህ ስፍራ እንድጠፋ ፍቀድልኝ. . ." አላስጨረሰውም።

"በመግባት ላይ ናቸው። በድንገት ሊያዩህ ስለሚችሉ መደነስክን ማቋረጥ የለብህም መንፈስህ እንዳይታወክ ስሜትክን አታስጨንቀው።"

ትንንሽ በጣም ትንንሽ የሚመስሉ ሴቶች ልጆችን ወገባቸውን ጭምቅ አድርገው አቅፈው ወደ ዳንሱ መሃል እየመጡ ያሉ በርከት ያሉ ወንዶችን አስተዋለ። ወንዶች የወንዶችን ሴቶች የሴቶችንም ወገብ አቅፈዋል። እ. . . እነዚህ የተረገሙ . . . ።"

ሴቶቹ ከፓንትና ከጡት ማስያዣ በቀር እርቃናቸውን መለመላቸውን ነበሩ። ወንዶቹ በሱሪና በሸሚዝ ብቻ ናቸው።

በዳንስ ስልት እየተንቀሳቀሱ ወደ አዳራሹ መሃል እየገቡ ናቸው። በውል የማይለይ ጩኸት ። ለቅሶ አለዚያም ሳቅ ያሰማሉ።

"የውሻ ልጆች እነዚህን..." አቋረጠው ዝም በልና ደንስ። መሳደብ ነውር ስለሆነ ያስቀጣል። ራስክን አታስጨንቅ። እንደዚያ የምታስብ ከሆነ አዕምሮህ ሊቃወስ ይችላል። ውሾች ሳይሆኑ ተኩላዎች ናቸው። በደንብ መደነስክን አትዘንጋው። በመምጣት ላይ ያሉት የተለያየ ኃላፊነት ያላቸው የሀገሪቱ ምርጥ የተባሉት ሰዎች ናቸው።"

አዲስ ወደ ገቡት ሰዎች በጣቱ ጠቆመው።

"አልገባኝም" አፍና ዓይኑን ከፍቶ ተመለከተ ዘሩባቤል።

"ይግባህ። ከሃይማኖት እስከ ሥልጣናት በዚህ ስፍራ ሁሉም ነገር ይገኛል።"

"የምን የሃይማኖት አባት ነው የምትነግረኝ?" ግራ ገባው።

"የመንግሥት መሥርያ ቤት የሕዝብ መሪዎችን፣ ሃይማኖት ሰባኪዎችን፣ የዕምነት አባቶች... ።"

"የምትለኝ ግልጽ አይደለም።"

"መመልከት አለብህ። ትኝሽ ቆይተህ የራስክን እይታ አለዚያም

የቅርብ የሥራ ባልደረባህን ታየዋለህ አትቸኩል::"

"ምንድነው የሚሠሩት? ምን እየሆኑ ናቸው?" ግራ መጋባቱ ጨመረ::

"ሰውየው ሳቀበት የምታየውን የምትመለከተውን እያደረጉ ናቸው::"

ራቁታቸውን ርቃነሥጋቸውን ሙሉ በሙሉ ያጋለጡ ሴቶች ወደ መድረክ ሲወጡ አዳራሹ በጩኸትና በፉጨት ቀለጠ:: ሁሉም ነገር የተደበላለቀ ያህል ተሰማው:: ሴቶቹ በላያቸው ላይ ያለችውን ስስ ፓንት በልዩ ስልት እያወለቁ ወደ ሕዝቡ ወርውረው ራቁታቸውን ይደንሱ ጀመር:: አጥንት ያልፈጠረባቸው እስኪመስሉ ድረስ በመድረኩ ላይ እየወደቁና እየተነሱ እንደ እንዝርት ይሽከረከራሉ:: ቀይ አረንጓዴ ሰማያዊ እና ቢጫ ቀለም ያለው የባውዛ መብራትም አብሮአቸው እየተሽከረከረ ራቁት ገላቸው ያስሰውና ያልፋል::

ራቁትና ኃፍረተሥጋ በዚያን ስፍራ ነውር እንደሌለበት ተገነዘበ:: ሰው ይሉኝታውን እራሱ አውልቆ ከጣለው ከእንስሳ የባሰ ፍጥረት ነው:: ምን እየተደረገ ነው ያለው? እነዚህ ሰዎች በውነት ምን እየሆኑና እየሠሩ ነው ያሉት? ከመድረኩ ፊት ለፊት በመብራት ከደመቀው ስፍራ ላይ ለዓይን ደስ የማይል የእንስሳ ግብር እየተፈጸመ ነው:: ዓይኑን ከመድረኩ ዙሪያ ወደ አሉት እብዶች መለሰ:: እነሱም በተመሳሳይ ሁኔታ ላይ ናቸው:: ከንቱ አስቀያሚዎች... እነሱንም ራሱንም ረገመ::

"እባክህ እንውጣ:: ልቤን አቅለሸለሸኝ:: ከዚህ በላይ መመልከት አልችልም::" ዳንሱን አቁሞ ተማጸነው::

"የምታየውን እስከምታይ እና በደንብ እስከምትረዳ ድረስ አንወጣም::"

"አይቻለሁ:: ብዙዎቹን አይቻለሁ::"

"የትኞቹን ብዙዎች ነው ያየኸው?" በዝግታ እያንቀሳቀሰው ወደ ጆሮው ተጠግቶ ጠየቀው::

ሴቶች ልጆቹን ይዘው ከገቡት አብዛኛዎቹን አውቃቸዋለሁ::"

"እና ይበቃኛል እያልከኝ ነው?" ሰውየው እንደመሳቅ አለ::

"ይብቃኝ:: አዕምሮዬ እየታወከ ይመስለኛል:: ከዚህ ስፍራ ቶሎ ብዬ መውጣት አለብኝ" ዓይኖቹ ተርገበገቡ::

ሽጉጥ በጨበጠበት እጁ ደረቱን በግራው ወገቡን አቅፎት ከአዳራሹ ይዞት ሲወጡ በዳንስ ስልት እየተሽከረከሩ ነበር::

"ከመኪናቸው ውስጥ ገብተው ትንሽ አረፍ እንዳሉ ምን እንደተሰማው ጠየቀው::

"አዕምሮዬ ተቃውሶብኛል ትንሽ ብቆይ አብድ እንደነበር እገምታለሁ::" መስኮቱን ዝቅ አድርጎ ወፍራም ምራቅ ተፋ::

"እንሂድና መኪናህን ይዘህ ትመለሳህ:: ለተከራየህበት ድርጅት መመለስ አለብህ::"





"የምትለኝ ከምርህ ነው?" በጥርጣሬ እየተመለከተ ጠየቀው ዘሩባቤል::

የተፈለግኸው ያየኸውን አይተህ መንካት የማይገባህን ከመንካት እንድትቆጠብ ለማድረግ ነው:: ማንኛውም እንቅስቃሴህ በእኛ ክትትል ስር ስለሆነ የምትሠራውን ከአንተው እኩል እንደምናውቀው ይግባህ:: አንተ የምትጨነቅላት ሀገርም በምን ዓይነት ሰዎች እንደተሞላች ቁንጽሉን እብደቷንና ሚርቷን አይተሃል:: ከዚህ በኋላ ምርጫው የራስህ ነው::"

"ይህንን ያሳየኸኝ ሁላችሁም ተስማምታችሁበት ነው?"

"ተስማምተንበት ነው እንድታይ የተደረገው::"

"ስለ ምሽት ክበቡስ አንድ እርምጃ ለመውሰድ ብሞክር እናንተን የሚነካ ነገር አለው?" ቀና ብሎ ፊቱን ተመለከተ::

"እንደ ሰዶም በእሳት ውኃ ብታቃጥለው እንሸልምህ ነበር::"

"ለማንኛውም ማሰብ ይኖርብኛል::"

"የምታደርገውን እየተጠነቀቅህ መፈጸም ይኖርብሃል:: በጣም ተጠንቀቅ ያልከውን የምትሞክር ከሆነ ያጠፉሃል ይህንን ስትመለከት ምን ተሰማህ?"

ትከሻውን በኃይል ነቀነቀ:: "በጣም ይዘገንናል::"

"ይህ እንደሚሰማህ እገምታለሁ::"

"አንተስ ውስጥህን ምን ይሰማዋል?"

"የደነዘዝሁ ይመስለኛል:: ምንም የሚሰማኝ የተለየ ነገር የለም::"

"በመጀመሪያ ስታየው ምን ተሰምቶህ ነበር?"

"ያንተ ተመሳሳይ ሳይሆን አይቀርም::"

"ተለማመድከው ማለት ነው?"

"እየደጋገምከው ስትሄድ መርዙንም ትለምደዋለህ::"

"ወደዚህ እንዴት ልትገባ ቻልክ? የመጀመሪያ ሥራህስ ምን ነበር?"

"ማወቅህ የግድ ያስፈልግሃል?"

"ይመስለኛል::"

"ነጋዴ ነበርሁ:: የገባሁት ተመልምዬ ነው::"

"እንዴት ሊመለምሉህ ቻሉ?"

"ንግድህ ሕገወጥ ነው ብለው መለመሉኝ::"

"ምን ነበር ሕገ ወጥ ንግዱ?"

"የሐሰት ሜርኩሪ::"

"የሐሰት ሜሪኩሪ ምንድነው::"

"ከእውነተኛው ሜሪኩሪ ጋር ተመሳስሎ የተሠራው::"

"እና በሽርክና ወደዚህ ድርጅት ገባህ?"

"እንደዚህ አይደለም::"

"እና ታድያ ምን ተፈጠረብህ?"

"ሐሰተኛ ሜሪኩሪውን የገዛሁት ክሁን ካለሁበት ድርጅት ነበር::"

“መልሱ ብትላቸው እምቢ አሉህ?”

“የመልስ ጥያቄ አላቀረብኩም:: ሜሪኩሪውን ያገኘሁት በደላላ አማካኝነት ነበር:: ዕቃውን አይቼ በዋጋ ተስማማን ብሩን ከፍያቸው ሜሪኩሪውን አስረከቡኝ::”

“ታዲያ ምን ተፈጠረ?::”

“ሜሪኩሪውን ይዤ ትንሽ እንደተጓዝሁ ደኅንነቶች አስቆሙኝ መኪናዬን ሲፈትሹ ሜሪኩሪውን አገኙት:: ይዘውኝ ሄዱ:: ለሳምንት ያህል ያሰሩኝ ምንም በማላውቀው ቦታ ነበር:: የተለያዩ ማስጠንቀቂያዎችን ከሰጡኝ በኋላ ስለቀቅ የማፍያው የደኅንነት ሠራተኞች መሆናቸውን ተረዳሁ::

“የማፍያው ደኅንነቶች ስትል ምን ማለትህ ነው::”

“ማፍያው የራሱ ደኅንነቶች አሉት:: ከመንግሥት ደኅንነቶች በምንም መንገድ አትለያቸውም::”

“ወደ እነሱ የገባኸው ተገደህ ነው ማለት ነው?”

ራሱን ነቀነቀ “እንደዚያ አልነበረም ሜሪኩሪውን ወስደው በማስጠንቀቂያ ስለለቀቁኝ አልፈለጉኝም::”

“እና ለምን ገባህ ታዲያ?”

“ሙሉ በሙሉ ስለ ከሰርኩ ሌላ ምርጫ አልነበረኝም::”

“ሌላ ሥራ ብትሠራስ አይሻልም ነበር?” ሲል ጠየቀው::

“ለጊዜው የተሻለ የመሰለኝ ምርጫ ይኸው ነው::”

“አሁን ብትወጣ ያስገድዱሃል እንዴ?”

“አልችልም::”

“ለምን አትችልም?”

“ብዙ ምሥጢሮችን አውቃለሁ::”

“በመንግሥት ደኅንነቶች ላይ የሚላከኩ የወንጀል ሥራዎች በነሱ የሚፈጸሙ ይሆኑ እንዴ?”

“የተወሰኑ እንደሆኑት አውቃለሁ::”

“እኔን ትከታተሉኛላችሁ ማለት ነው?”

“ያየኸው ምሥጢር ስለሌለ ብዙ የሚያሳስበን ነገር ያለ አይመስለኝም::”

“የምሽት ክበቡን እርምጃ ብወስድበትስ::”

“እሱ እኛን አይመለከትም:: በሱ በኩል ስላለው ጉዳይ ከእኛ በበለጠ የራስክን ሰዎች ብትፈራ የተሻለ ነው::”

“እኔም የገመትኩት አንተ ያልከውን ነው::” ሲል መለሰለት ዘሩባቤል::





# ምእራፍ አሥራ አምስት

የአዲስ አበባ ሰማይ ዝናብ ባዘለ ጥቁር ደመና ተውጦ ጥቁር በርኖስ ሙስሏል:: ከትንሽ ደቂቃዎች ቀደም ብሎ በዘነበው ዝናብ የፈሉት የክረምት አሸኖች በየመንገድ ዳር በተንጠለጠሉት አምፑሎች ዙርያ ይርገበገባሉ:: ዝናብ ያዘለው ነፋስ የሚሸነቁጥ ቅዝቃዜ በመረጨት ላይ ነው::

እንደ ገበጣ መጫወቻ የተቦረቦሩት የአስፋልት መንገዶች በጐርፍ ተሞልተው መኪናዎች ለመተላለፍ ተቸግረዋል::

የቸርችል ጐዳናን ቁልቁል እንደ ቀስት እየሰነጠቁት ወደ ብሔራዊ አቅጣጫ የሚመጡት ቶዮታዎች እርስ በርሳቸው እንደሚሽቀዳደሙ ሁሉ መንገደኛውን የረጋ ውኃ በማልበስ መኪናዎቹን በማስበርገግ ተዳፋቱን ወረዱ:: አብዮት ሲደርሱ ወደ ቦሌ በሚወስደው ጎዳና ታጠፉና ፒካፑ ወደ ኋላ ቀርቶ ላንድ ክሩዘሩን ወደ ፊት አስቀድመው ላንድክሩዘር ቶዮታው ውስጥ ሹፌሩን ጨምሮ አሥር ሰዎች ሲኖሩ ፒካኘ ቶዮታ ከአሥር በላይ ልዩ ኮማንዶዎችን አሳፍሯል::

ሁለት የቪዲዮ ካሜራ ባለ ሙያና የጸጥታ ቢሮ ኃላፊውን የጫነው ቶዮታ ወደታቀደለት ስፍራ ሲቃረብ ከላንድ ክሩዘሩ በቅርብ ርቀት ረጋ ብሎ ያክተል ጀመር:: የግዳጁ ቦታ መቶ ሜትር ያህል ሲቀረው ፍጥነቱን አብርዶ ከመንገዱ ዳር ቆመ:: ላንድክሩዘሩ በመጠነኛ ፍጥነት ወደ ፊቱ ቀጥሏል:: ከዋናው አስፋልት አምስት መቶ ሜትር ያህል እርቆ በጨለማ ከተዋጠው ስፍራ ከአንድ የምሽት ክበብ የመግቢያ በር ላይ ሲደርስ በርካታ የቤት መኪናዎች ቆመው ታዩት::

ስፍራው በደብዛዛ ጨለማ ተውጧል:: ሌሎችም መኪናዎች ከበስተኋላው በተመሳሳይ ፍጥነት ወደ ምሽት ክበቡ እየተጠጉ መሆናቸውን አስተዋለ:: የክበቡ ሙዚቃ በኃይል መሰማት ጀምሮ የሰዓቱን መድረስ እያበሰረ ነው::

ላንድ ክሩዘሩ የመንገዱን ጠርዝ በመያዝ ረጋ ብሎ እየተሽከረከረ ወደ ክበቡ በሚጠጋበት ወቅት ፒካፑ ላይ ተጭነው የነበሩት ልዩ ኮማንዶዎች ያነገቱትን ትጥቅ እያስተካከሉ ከፒካፑ ጀርባ ወረዱ:: ሁሉም ነገር በተለመደው መልኩ እንደ ቀጠለ ነው:: የሕንፃው ውጭ በኮማንዶዎች ቁጥጥር ስር ሆኗል::

የኮድ ድምጾች ከአንዱ ወደ ሌላው እየተቀባበሉ መልእክት መለዋወጥ ጀመሩ::

“በአጥር ዘሎ የሚያመልጥ ካለ መመታት አለበት:: በምንም ተአምር ከነሕይወቱ የሚያመልጥ ሰው እንዳይኖር::” ዘሩባቤል ጥብቅ ተእዛዝ ሰጠ::

"ምንም የታየን እንቅስቃሴ የለም::" የቡድኑ አስተባባሪ መልስ ሰጠው::

"ሲቪል ደኅንነቶች ወደ ውስጥ አልገቡም:: ሁኔታው የሚቀየረው ወደ አዳራሹ ከገቡ በኋላ ነው:: እየሾለኩ የሚወጡ ሊኖሩ ይችላሉ:: ምናልባትም በአጥር መዝለላቸው የማይቀር ነው::"

"ኰድ አምስት... ኰማንደር ምን እየተፈጠረ ነው? እስከ አሁን ሁሉም ነገር እንደ ቀዘቀዘ ይመስለኛል?"

ከላንድ ክሩዘሩ ውስጥ የነበረው የፕሮፓጋንዳ ተጠሪው ነበር የተናገረው::

"አዳራሹ ለመግባት የመጀመርያውን በር ከፍተናል::"

"የምን በር?" ከወንበሩ ላይ ለመወራጨት ሞከረ::

"ከበሩ ላይ የነበረው ግዙፍ መዝጊያ ተከፍቷል::"

ከፊት ለፊት የነበረውን ጋርድ አፉን አፍነው እጁን በካቴና ጠፍረው እያሠሩት ነበሩ:: ሲቪል ደኅንነቶቹ ወደ መግቢያው ተጠጉ:: ደኅንነቱ ከጓደኛው ተነጥሎ ሲቀርበው ደንቡን ያላወቀ ይሆናል ብሎ ቸል አለው::

"ሴት ሳይዙ መግባት ክልክል ነው::"

ከትከሻው ላይ የተቆለለውን ክምር ሥጋ በስልት እያንቀሳቀሰ ተናገረ:: የሃረር ሰንጋን መስሏል::

"አውቃለሁ ይቻትና ጓደኛዬ::" ከአጠገቡ ፈንጠር ብሎ ወደ ቆመው አባሉ በጣቱ እየጠቆመ መለሰለት::

"ስትመጡ የመጀመሪያ ጊዜያችሁ መሆን አለበት" እንደ መገልፈጥ አለ::

"የመጀመሪያ ጊዜያችን ነው የጐደለን ካለ አስረዳን::"

"ከንፈር ለከንፈር መሳሳም አለባችሁ:: ሕጋችን ይህንን እንደ ቅድመ ማስጠንቀቂያ ያቀርባል::"

በእርምጃ ወደሱ እየተጠጋው ነበር::

"ፍቅረኛ ስለ መሆናችሁ ማወቅ አለብኛ::" ትከሻው ላይ ያለውን የሥጋ ክምር በስልት እየደጋገመ ማንቀሳቀስ ጀመረ::

"ይቅርታ አንቺ እያልክ ጥራት ፍቅረኛዬን በወንድ ፆታ ስትጠራት ይከፋኛል::"

"ፍቅረኛህ መሆኗን ማወቅ ስላለብኝ እኔ እያየሁ ተሳሳሙልኝ"

"እባክህ ትንሽ ታገሰን ሰዓቱ ገና ነው" አለው ደኅንነቱ::

"ካልፈልጋችሁም ትመለሳላችሁ::"

የጓደኛውን ትከሻ አፈፍ አድርጐ ይዞ ተሽከርክሮ ባልታሰበ ፍጥነት የሽጉጡን አፈ-ሙዝ ከዓይኑ ስር ሲተክልበት በድንጋጤ ፈጠጠ::

"ቃል እንዳትተነፍስ እንደዚያ ከአደረግህ ምላጩን እስበውና ዓይንህን አንጐልህ ውስጥ እጨምረዋለሁ::"





"እንዳታደርገው:: ምንም ዓይነት ትንፋሽ አይወጣኝም::" እየተንሸራተተ ሲወርድ እያራጠበ ነበር::

የመገናኛ ሬዲዮኑን ስለ ወሰዱት ውስጥ ከነበረው ጋርድ ጋር የነበረው ግንኙነት ተቋረጠ:: ትልቁ ትዕይንት ያለው ከመጋረጃው በስተጀርባ በመሆኑ የጸጥታ ሠራተኞቹ አልፈው ለመግባት ከመጠን በላይ ተቻኩለዋል::

ከአዳራሹ ወደ በሩ አቅጣጫ የተደበላለቀ የጭስ ሽታ መጣ መሣርያና የተለያየ የሚሰቀጥጥ የሳቅና የለቅሶ ድምጽም በአንድነት እየተደበላለቀ ይሰማል:: የሚሸተው ሁሉ ለመንፈስ ተስማሚ አይደለም:: ዘሩባቤል በአለፈው ምሽት ቀምሶታል::

ሁሉም ነገር እንደነሱ እርምጃና እንቅስቃሴ እየተፋጠነ ሲመጣ የጸጥታ ሠራተኞቹ ወደ ሲኦል አዳራሹ ለመግባት የተቃረቡ መስሎ ተሰማቸውና መንፈሳቸው በውል በማይለዩት ስሜት ተወጠረባቸው::

በመጠጥ እንፋሎት የተሞላው አዳራሽ ሽታውና ሁካታው ወደ መጡበት አቅጣጫ ቢገፈትራቸውም አልተመለሱም:: ትንፋሻቸውን ወደ ውስጥ ላለመሳብ እየታገሉ አዳራሹ ውስጥ ከነበረው ትዕይንት መካከል ገብተው ተደበላለቁ::

በራሷ ማዕበል እየተናጠች ዓለም አስቀያሚ ገጽታዋን ቀጥላለች:: ሁሉም ትዕይንት በነበረበት እንደ ቀጠለ ነው:: ሟርተኞቹ በመድረኩ ላይ የተለመደ ተግባራቸውን ቀጥለዋል::

እብዶቹም የየራሳቸውን በፍልስፍና የተሞላ ትወና በማካሄድ ላይ ናቸው:: ካሜራዎቹ የራሳቸውን ሥራ በሚያስተካክሉበት ሰዓት የጸጥታ ኃላፊው ሽጉጡን ወደ ፊት እንደ ደገነ በባውዛው ብርሃን ተመለከተ:: ሁሉም ነገር የሕልም ያህል ሆኖ ብዥታ አጥወለወለው:: የጸጥታ ኃላፊው የሚደረገውን ሲመለከት ሕሊናው ሊሸከመው የማይችል የመንፈስ እዳ ሆኖ አእምሮው ጭንቀቱን መቋቋም አልቻለም:: ከአዳራሹ በግራ ጠርዝ ላይ ወንዶቹ ከወንዶቹ ጋር በቀኝ በአንደኛ ኰርነር ጥግ ላይ ሴቶች ከሴቶች ጋር ከአዳራሹ መሃል ሴት ከወንድ ጋር ... በተያዘው የዲያቢሎስ ፍልሚያ ደስ የማይል ልክ እንደ ሳጥናኤል ፉጨት የሚያሸብር የጣር የሚመስል ድምጽ ሰፊውን አዳራሽ አውኰታል:: ከመድረኩ ላይ ሦስት ጥንድ ሰዎች ተመሳሳይ ሟርት እየፈጸሙ ናቸው::

ነጩ፣ ጥቁሩ፣ ጠይሙ፣ ቢጫው የሰው ዘሩ ተደበላልቆ በሲኦል አዳራሽ ይገኛል:: ሁሉም የሰው ዘሮች በተሰሎንቄ ከትመው እያበዱ ናቸው::

በአዳራሹ ውስጥ የነበረው የሟርት ትዕይንት ተቋርጦ ሁሉም ነገር በድባብ ጸጥታ ውስጥ ወድቆ ካሜራዎቹ ተገቢ ሥራቸውን ለመጀመር የወሰደው ጊዜ አጭር ነው:: የባውዛው መብራት ከተለቀቀ በኋላ ዳንኪረኞቹ ከሟርት ሥራቸው ነቅተው ባሉበት በተንበረከኩበት በቁም ቅዠት ላይ

ናቸው። ሁሉም ነገር ውሸት እንዲሆንላቸው በመመኘት ላይ ነበሩ።

እሳት ለመትፋት አፋቸውን የከፈቱ ጠመንጃዎችና እነሱን የደቀኑ ልዩ ኮማንዶዎች ከፊት ለፊታቸው ተገትረዋል። ምንም ዓይነት እንቅስቃሴ እንዳያደርጉ ትእዛዝ እየተሰጣቸው ናቸው። እርቃንን ለካሜራው መስጠት ከነሱ ይጠበቃል።

የቪዲዮ ካሜራዎቹ ሥራቸውን ጀምረዋል። ከትእዛዝ ሰጭዎቹ በስተቀር ዝምታ ነው።

"እባካችሁ አትቅረጹኝ የልጆች እናት ነኝ። የሚወደኝና የሚያከብረኝ ባለቤት አለኝ። ከሃዲ ውሻዋ እኔ ነኝ። ይሄ አጠገቤ የምታዩት አውሬ ነውጉድ የሠራኝ። የመሥሪያ ቤት አለቃዬ ነው። እሱም ትዳር አለው። ባለቤቴ ወደ ውጭ አገር ሲወጣ አዘውትረን መምጣት ጀመርን የመጀመሪያ ቀን አፍሬ ነበር። በኋላ ግን እየጣመኝ መጣ። አሁንም ባለቤቴ የለም። ከሶስት ቀን በኋላ ይመለሳል። ወደ ቻይና ነው የሄደው።" ሴትየዋ ያለ ምንም ጥርጥር አእምሮዋ ሥራውን ቀይሯል። በድንጋጤ አብዳለች። ካሜራው የሴትየዋን ምስልና ከአጠገቧ ያለውን ሰው እየቀረፀ ነው።

"በደንብ አድርገሽ ተናዘዥ። መለፍለፍሽን እንፈልገዋለን።" ዘሩባቤል ድምጽን ከፍ አድርጎ ሲናገር ድምጿን የበለጠ ከፍ አደረገች።

"አንተ የውሻ ልጅ ቀይ እሰራልሃለሁ! ማን መስዬህ ይሆን? በጠመንጃ አፈሙዝ አስገድደህ የምትቀርጸኝ።" ከሚርተኞቹ አንዱ በድንገት ተናገረ።

"ምንድነው እየተደረገ ያለው? አለው ምንተስኖት።"

"የገባኝ ነገር የለም" አለውና በረጅሙ ተነፈሰ ዘሩባቤል። ሊታመን የማይችል ነገር የተያዙት ሰዎች ማታውኑ ተለቀቀው ከድርጅቱ ሠራተኞች የተወሰኑት በቁጥጥር ስር ተደረጉ። ዘሩባቤል የሚይዝ የሚጨብጠውን አጥቶ በቢሮው ውስጥ ከረዳቱ ጋር እየተነታረከ ነው።





# ምእራፍ አሥራ ስድስት

የተለኮሰችውን የሻማ ብርሃን አትኩሮ ተመለከታት። እንደ ጨው እየሟሟች በማለቅ ላይ ነበረች።

የሥራ ባልደረባው አነስተኛ ጠረጴዛ ላይ ያለውን ኮምፒውተር ከፍታ የተለያዩ ዳታዎችን እየጉረጉረች ነው። በድንገት የተሰወረው የደኅንነት ሠራተኛ ጉዳይም ሕልም ሆኖባቸዋል። ከሲ አይ ኤ ጋር በተጠላለፈ ዘዴ እንዲሠራ የተቋቋመው የጠቅላይ ሚኒስቴር አዲሱ የመረጃ የኢንተርኔት መረቡን ዘርግቶ እያፈላለገው ቢሆንም የሰውየው ዱካ ሊገኝ አልቻለም። የጉዳዩ ሥረ-መሠረት መነሻና መድረሻ እንዲሁም ከበስተጀርባው ያሉት ሁኔታዎችም በረቀቀ መንገድ አንድ በአንድ እየተነቀሱ እየተመረመሩ ናቸው። ከከፍተኛ ነጋዴዎች እስከ ከፍተኛ ባለ ሥልጣኖች የተወሳሰበው ሕገ ወጥ ንግድ የብዙዎችን ድራሽ እያጠፋ ሀገሪቱ በውጥረት መናጥ ጀምራለች።

በአሁኑ ሰዓት የትም ሊሆን ይችላል። ሲል አሰበ ዓይኑን ወደ ሴቷ እየወረወረ። ይህ መዘዘኛ ሰው ከነመጨረሻው መውደም አለበት። ጠቅላላ ሃሳቧን አሰባስባ ኮምፒውተር ላይ አንገቷን እንደ ደፋች አዳዲስ መረጃዎችን በመፈለግ ላይ ነበረች። የሷን የቀጥታ ትእዛዝ ለመቀበል ሲል የሠራው ስህተት ነበር። እንዴት ተደርጎ! ያውም በሴት ታዝዥ? እኔ ራሴ ልይዘው ስችል ልቡን ኃይለኛ ጸጸት እየጫረው ነው። ይህንን የወሰነበት ዋና ምክንያት ምቀኝነት ይሁን ወይም የበላይነት ስሜት በውል አልገባህ ብሎት የከፍሉን መብራት አጥፍቶ ሻማ እንዲያበራ አስገደደው። የማይወጣው ከሚመስለው ችግር ውስጥ አዕምሮው በሚዘፈቅበት ወቅት እራሱን በሻማ ብርሃን መመልከት እንደ አንዳች ምትሃት የሚጠቀምበት ራሱ የፈጠረው የሥነ-ልቦናው መፍትሔ ነው። የጠፋበትን ኃሳብ የሚፈልገውም በደብዛዛ የሻማ ብርሃን ነው። ነገሩ በአጭር ካልተቋጨ የሚያስከትለው መዘዝ ቀላል አይደለም። ይህ መዘዘኛ ሰው መያዝ እና ከነመጨረሻው መጥፋት አለበት ሲል ለራሱ ደመደመ።

የሻማው ብርሃን እንደ ተመኘውና እንዳሰበው ለጥያቄዎቹ መልሱን የሚያሳየው አልሆነም። ሴቷም የምትጎረጉረው ኮምፒውተር አእምሮውን ለወጠረው ነገር መልስ መስጠት አልቻለም የልጆች ጭዋታ ዓይነት ከንቱ ሙከራ ነው። አንዳች ጀብዱ የፈፀመ ያህል የተጀነነው ሰው በሩን ከፍቶ ከፊት ለፊቱ ሰላምታ ሰጥቶት ሲቆም ከጠለቀበት የኃሳብ ውቅያኖስ መንጥቆ አወጣው። ከውጭ የገባው ወታደር በክፍሉ መሃል እንደ ቆመ ሁለቱንም ተራ በተራ እየተመለከተ ቆይቶ ወደ ጠረጴዛው ተራመደና እጁን ጨበጠው። የጸጥታ ፖሊሱንና ሴቷን በየተራ ተመለከተ።

“አዲስ ነገር...” ቃላቶቹን ለመጨረስ የፈራ ይመስል ሁሉንም እየቆራረጠ ተዋቸውና ከፊቱ የቆመውን ሰው ተመለከተው።

ከወንበሩ ላይ እየተመቻቸ እጁን ደረቱ ላይ አመሳቅሎ ወደ ሴቷ ተመለከተ። የገባው ሰው በኮምፒውተሩ እስክሪን ላይ እንዳቀረቀረች በአንዳች ነገር ላይ አፍጥጣ አገጯን በግራ እጇ በመደገፍ ትመለከታለች። ጠቅላላ ቀልብዋ ያለው ስክሪኑ ላይ ነው የሚመስለው።

“አዲስ ነገር ይዣለሁ።” ድምጹን ዝቅ አድርጐ ተናገረ።

“አዲስ ነገር ተገኘ?” ድምጹን ቀንሶ ጠየቀው።

“ከፌዴራል ፖሊስ ተደውሎልኝ ነበር። ካንተ ጋር በግል መነጋገር ይኖርብኛል” ወደ ሴቷ እየተመለከተ ተናገረ።

“እንውጣ እያልከኝ ነው?” ጠየቀው ዘሩባቤል።

“እንደዚያ መሰለኝ” ከአንገቱ ወደ ፊት ቀደም አለ።

“አስቸጋሪ ይመስለኛል” ራሱን እንደ መነቅነቅ አደረገ።

ያለፈውን ስህተቱን ላለመድገም ተጠነቀቀ። ከኮምፒውተሩ እስክሪን ላይ ቀና ብላ ሁለቱንም እየተመለከተቻቸው ነበረች። የተነጋገሩትን ትስማ አትስማ እርግጠኛ አልነበሩም።

“እዚሁ መነጋገር ይኖርብናል።” በጭንቀት አቃሰተ።

“ሰውየው የመነኩሴ ቀሚስ ለብሶ በአንድ ቤተ ክርስቲያን በመቃብር ቤት ውስጥ የትናንትናውን ምሽት እንዳሳለፈ በእኛ ሠራተኞች ተደርሶበታል።”

“ይህንን እኛም ደርሰንበት እየተከታተልነው ነን። ያልተረዳነው በየትኛው ቤተ-መቅደስ የመቃብር ቦታ እየኖረ ነው የሚለውን ብቻ ነው። በአዲስ አበባ በመቶ የሚቆጠሩ የተለያዩ ቤተ-መቅደሶች አሉ” አለ ዘሩባቤል።

“በምን ሰማችሁ?” ትኩር ብሎ ተመለከተው።

“የነገርከኝን በኢንተርኔት አሰራጭቶታል።”

“አየነው ብለው የተናገሩ ከኢንተርኔት ያገኙትን መረጃ ነው ማለት ነው?” የጸጥታ አስተባባሪው አመነታ።

“ለምን አታጣሩም ነበር?”

በሁለቱ መካከል ፍጹም ጸጥታ ሆነ። ሴቷ ከኮምፒውተሩ ላይ ቀና ብላ በየተራ ሁለቱንም ተመለከተቻቸው።

“ለማጣራት ሞክረን ነበር።” አለው ከዝምታ በኋላ።

“እና ምን ተጨባጭ ነገር አገኛችሁ?”

“ለሕይወቱ ዋስትና የሚሰጠው አካል ይፈልጋል። ዋስትና የሚሰጠው አካል ካገኘ ንብረቶቹን እንደ ያዘ ለመንግሥት አካላት እጁን መስጠት እንደሚፈልግና በአንድ ቤተ መቅደስ ግቢ በመቃብር ቤት ውስጥ እንደሚገኝ ሰውየው የነገረን።”





እንደ መውረግረግ እያደረጋት ወደነሱ መጣች ሴትየዋ።

“ያገኘሁት መረጃ ተመሳሳይነት ያለው ነው። የራሱን ደኅንነት እንድናስጠብቅለት ይፈልጋል። እንደምገምተው ከሆነ ጓደኞቹን ሊያምናቸው ባለመቻሉ ይመስለኛል ይህንን እርምጃ ለመውሰድ የተገደደው።” ተናግራ ስትጨርስ በየተራ ተመለከተቻቸው።

“ይህ ሁኔታ በመጠኑም ቢሆን ይመሳሰላል” ነገር ግን በእርግጠኝነት ነው ብሎ ለመናገር አይቻልም” አለ ዘሩባቤል።

“እውነት ስለመሆኑ ማረጋገጫ የለንም። ሰውየውን በአካል እስካላገኘነው ድረስ ትክክለኛ ግምት ለመስጠት አስቸጋሪ ነው” ስትል መለሰችለት።”

“የኔም ግምት እንደሱ ነው። ግን ሌላ አማራጭ ሃሳብ የለንም።” አለ ዘሩባቤል።

ፖሊሱ መልስ ከመስጠት ይልቅ ዝምታን መረጠ። “ወንጀለኛ ከዚህ ቦታ እገኛለሁ ብሎ መልእክት ሊያስተላልፍ? የማይመስል ነገር ነው።” ወደ ጠረጴዛዋ ተመልሳ የተለመደ ሥራዋን እያከናወነች ሃሳቧን ወደነሱ አደረገች።

“በኢንተርኔት እንዲሰራጭ ያደረገው የፍለጋ መስመሩን ለማጥፋት የተጠቀመበት የማስመሰያ ዘዴ ሊሆን ይችላል። በመቃብር ቤት ውስጥ እራሴን ደብቄያለሁ እያለ በአንደኛው ጠረፍ ሾልኮ ለመውጣት በዝግጅት ላይ መሆን አለበት።”

እጅግ አደገኛ ሁኔታ ነው። በሕይወት መኖር አልነበረበትም። ከበርካታ ዝምታ በኋላ የመጣለትን አሳብ እያምሰለሰለ ጭንቅላቱን ነቅንቆ ሴቷን አስተዋላት። የኮምፒውተሩን ዳታ እየጐለጐለች ነው።

ያገኘችውን መልዕክት ሰውየው ይዞት ከመጣው መረጃ ጋር ለማጣጣም እየጣረች ነበረች። በርግጥም በተወሰነ መልኩ የሚመሳሰል ነው።

የተስፋ መቁረጥ ስሜት ስለተጫነው ከተቀመጠበት በመነሳት ወደ መስኮት በመሄድ የመጋረጃ ጨርቁን ጨምድዶ ወደ ጎን አንሸራተተው። የአዲስ አበባን ግማሽ አካል ሰፊው መስኮት ለማየት እጅግ ምቹ ነበር። በስተምስራቅ በኩል ያለው የከተማዋ አካል ጨለማውን ሰንጥቀው እንደ አልማዝ ፈርጥ በሚንቦገቦጉት መብራቶች ደምቆ ይታያል።

በስተምእራብ ያለውም በተመሳሳይ ሁኔታ ደምቋል። ውጭውን ሲመለከት ቆይቶ ወደ ወንበሩ በመመለስ “መልዕክቱን ከኮምፒውተር አውጥተህ አምጥተኸዋል?” ሲል ጠየቀው።

ዝርክርክ ውሻ ጉድ እየሠራን ነው። አለ በልቡ እጁን ወደ ኮቱ የደረት ኪስ እየሰደደ።

የንባብ መብራቱን ሲጫነው ጠረጴዛው በደመቀ የብርሃን ኩሬ ተሞላ።

መነጽሩን ከትልቅ አፍንጫው ላይ የማንጠልጠል ያህል አድርጎ በጥንቃቄ ማንበቡን ቀጠለ። የሰፈረው አሳብ የድርድር ጥያቄ

ከመሆኑ በተጨማሪ በሴትዮዋ የኮምፒውተር ዳታ ላይ የተገኘው መልዕክትም ተመሳሳይ የሆነ አሳብ ያለው ነው፡፡

"ምን ይመስልሃል?" በትከሻው ላይ ተንጠራርታ ፊቱን ለማየት እየሞከረች ጠየቀችው፡፡

"ለመገመት ይከብደኛል፡፡" ቀና ብሎ ፊቷን እየተመለከተ ተናገረ፡፡

"እያምታታን የማምለጫ መንገዱን እያመቻቸ ይሆናል ወደሚለው እያመዘንሁ ነው፡፡" አጎንብሳ ጽሑፉን እየተመለከተች አንሾካሾከችለት፡፡

"የኔም ግምት እንደዚያ ነው፡፡ ያም ሆኖ እርግጠኛ አይደለሁም፡፡"

"ምናልባት ከድርጊቱ በኋላ ተጸጽቶበት አለዚያም የመውጫ ቀዳዳው ሲጠብበው ያመጣው እውነተኛ ሃሳቡ ቢሆንስ" ፡፡

"እንደ እውነተኛ ግምት አድርገን መውሰድ የጅል አሳብ ይመስለኛል" ሴቷ ኮስተር ብላ መለሰችለት፡፡

"አብዛኛዎቹ ቃላቶች እውነትን የሚጠቁሙ ይመስላሉ፡፡ ምናልባትም ተባባሪዎቹ ጥለውት ስለጠፉ በመፍራቱ ይመስለኛል ከመንግሥት ጋር የሕይወት ዋስትና ለመቀበል መደራደር የጀመረው፡፡" አለ የጸጥታ አስተባባሪው፡፡

"እውነቱን ስለመሆኑ ያጠራጥራል፡፡ የራሱን አድራሻ ከመግለጥ ይልቅ ዝም ብሎ ነው በኢንተርኔት የለቀቀው፡፡"

ዘሩባቤል እንደገና በጽሑፉ ላይ አቀርቅሮ በጥንቃቄ ቃላቶቹን ይመረምር ጀመር፡፡

ድርጊቱን ከፈጸመ በኋላ መጸጸቱን ገልጾ በአንድ ቤተ መቅደስ ግቢ በመቃብር ቦታ ከመሆኑ ሌላ የሚለው የለም፡፡ እውነቱን ቢሆን ለምን እጁን አይሰጥም? ተደራድሮ እጅ መስጠቱ ምን ያህል ዋስትና ሊኖረውስ ይችላል? የራሱን የማደናገርያ ስልት እየተጠቀመ ሊሆን ይችላል፡፡

ዘሩባቤል በረጅሙ ከተነፈሰ በኋላ ዓይኖቹን ጠረጴዛው ላይ በተቀመጠው ወረቀት ላይ ተከለ፡፡ የሰውየውን መደራደርያ በውል ለመረዳትና ለመቀበል የሚከብድ ነው፡፡ እውነት ከሆነ ለምን ያለበትን ቦታ መጥቀስ አልፈለገም? በርግጥ ወንጀል የሠራ ሰው እጁን ለመስጠት ዋስትና እስከሚሰጠው ድረስ ያለበትን መግለጽ አደጋ አለው፡፡ ያለበትን ያለመናገሩ ትክክል ነው፡፡ ከወንጀሉ ጀርባ ያሉት አካላት ምሥጢሩን ለማዳፈን ሲሉ ለሕግ ላያቀርቡት ይችላሉ፡፡ ዋስትና እስከሚሰጠው ድረስ ያለበትን መግለጽ አይችልም፡፡ አድራሻውን ያልገለጠው ሆን ብሎ ለማደናገር የተጠቀመበት የማምለጫ መንገድ ላይሆን ይችላል፡፡

በሃሳብ እንደተዋጠ ከርዳዳ ጸጉሩን ያሻሽ ያዘ፡፡ ኃሳቡ ሁሉ እርስ በርሱ ተጣረሰበት፡፡

"በአዲስ አበባ የሚገኙ ቤተ ክርስቲያኖች በጸጥታ ኃይሎች መፈተሽ ይኖርባቸዋል፡፡ አማራጩ..." ሴቷ አቋረጠችው፡፡





"እንደዚህ ሊሆን አይችልም፡፡ ይህንን ማድረግ አንችልም፡፡ በዕምነት ቦታዎች እየገቡ ሰውን ፈትሾ ማግኘት ቀላል ካለመሆኑ በተጨማሪ የመነኩሴ ቀሚስ እየገለብን እንፈትሽ ማለት ትልቅ ድፍረት ነው፡፡ ከእምነት ጋር ሊያጋጭ የሚችል ይመስለኛል፡፡ በመቃብር ቤት ውስጥ እየኖረ ከሆነ የተለያዩ የማሳሳቻ ዘዴዎችን መጠቀሙ እውን ነው፡፡ ከአርቴፊሻል ጺም ጀምሮ አለባበሱን ጭምር መነኩሴ ለመምሰል ይጠቀማል..." ሁለቱም ራሳቸውን ነቀነቁ፡፡

"የምትይው እኔንም አሳስቦኛል፡፡ ወደ ቤተ መቅደሶች እየገባን መፈተሽ ባንችልም በአዲስ አበባ የሚገኙት አብያተ ክርስቲያናት በራሷ የደኅንነት ሠራተኞች እንዲፈተሹ እንድታደርግ ለቤተ ክርስቲያኗ ጠቅላይ ጽሕፈት ቤት ማሳወቅ ይቻላል፡፡"

"ይህ አሳብ ከሌሎቹ የተሻለ የሚመስል መልክ አለው፡፡ ያም ሆኖ ጥንቃቄ ያስፈልገዋል" አለ ዘሩባቤል፡፡

"ሊያስኬድ የሚችል መንገድ አይመስለኝም"፡፡ ቤተ ክርስቲያንን የመፈተሽ ሥራ አንሠራም፡፡ የእምነት ቦታዎችን እየበጠበጥን ሕዝብን ማሸበር የለብንም፡፡ ሕዝቡ በእምነቱ በኩል ሲመጡበት ቁጣው ሊገነፍል ይችላል፡፡ በየቤተ-መቅደሱ እየገቡ የዕምነት አባቶችን ፈትሼ ወንጀለኛ እይዛለሁ ብሎ ማሰብ ያልተጠበቀ አደጋን የሚቀሰቅስ ነው፡፡ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ቢሆን ኖሮ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እገኛለሁ ብሎ አይገልጽም ነበር" ወገቧን ለቅቃ እጇን አጣመረች፡፡

"የማምለጫ መንገዶችን እየተጠቀመ ሊሆን ይችላል ነው የምትይው በርግጥ አንቺ የምትይውን እጋራዋለሁ" ዘሩባቤል አሳቧን በግማሽ የደገፈ መሰለው፡፡

"እንደዚያ እያደረገ ይሆናል ባይ ነኝ፡፡ ደግሞም እያደረገ ነው፡፡ ከቤተ ክርስቲያን ውስጥ ቢሆን ኖሮ ያለበት ሁኔታ አይናገርም ነበር፡፡ ያዋጣውም አያዋጣው አለባበሱን ጭምር ቀይሮ ተደብቋል፡፡ እንበልና መነኩሴ መስሎ ነው ተደብቆ ያለው፡፡ እንደዚያ ከሆነ ደግሞ የማስመሰያ ዘዴውን ይናገራል ብሎ ማሰብ የጅል ዘዴ ነው፡፡ በፍጹም ይህንን አያደርግም፡፡ አለዚያም እራሱን መነኩሴ አስመስሎ በመቀየር ቤተ ክርስቲያን አልገባም፡፡ እውነቱ ከነዚህ ሁለት መላ ምቶች አይዘልም፡፡" በርግጠኝነት ተናገረች፡፡

የጸጥታ ሹሙ እራሱን በአዎንታ ከነቀነቀ በኋላ ትኩር ብሎ እየተመለከታት "ያቀረብሽው ግምት ወደ እውነት ይቀርባል፡፡ ሆኖም ነው ብሎ መደምደም አይቻልም፡፡" አላት፡፡

ያልሠራ ድራማ ነው አለ ለራሱ፡፡ ሁሉም ነገር እየተበላሸ ነው፡፡ ከአለቃው ጋር የሠሩት ማስመሰያ በዘሩባቤልና በሴቷ ተቀባይነት አላገኘም፡፡ ጉድ ያደረገው የሰው ነገር የማይገባው ግትር አለቃው ነው፡፡

ማስመሰያው እንደማይሠራ ሲያሳምነው ብዙ ጥረት አድርጓል። እንዳለውም ጫን ብሎ እየሠራ አይደለም።

"ለዛሬው ጨርሰናል" አለው ዘሩባቤል።"

"እየተከታተልኩ የደረስኩበትን እገልጽላችኋለሁ።" መውጣቱን ስታረጋግጥ ከተቀመጠችበት ተነስታ ወደ ዘሩባቤል መጣች።

"ምን ይመስልሻል?" አላት ፊቷን እያጠና። ትክሻዋን ነቅነቅ አደረገች "ይህቺ ፌጠራ የሱና የዚያ ጠማማ ይሁዳ አስቃው እንደምትሆን አልጠራጠርም።"

በመስማማት ራሱን ነቀነቀ። ዘሩባቤል ሁሉንም ነገር ነካክቶ ራሱን አጣብቂኝ ውስጥ ከትቷል። ወሮበላዎቹና ከምሽት ክበብ ያያቸው ሰዎች ሁሉ ነፍሱን የሚፈልጉ ሆነዋል።





# ምእራፍ አሥራ ሰባት

በየደቂቃው በሚንጫረር የስልክ ጩኸት የመረጃ ቁርጥራጭ ጥንቅራቸው እንዲቆራረጥና ስሜት እንዲያጣ አይፈልግም። አዕምሮው ክፉኛ ተወጥሯል። በምንም ነገር መረበሽ የለበትም።

"የደላላ ስልክ ይመስል" አለ ዘሩባቤል በመነጫነጭ ስሜት። ደቅርታ በሚጠይቅ መልኩ ከአስተዋላቸው በኋላ ከተቀመጠበት ተነስቶ ከሳሎኑ ፊት ለፊት ያለውን የገላ መታጠቢያ ከፍቶ ወደ ውስጥ ገባ። መደወል በነበረበት ሰዓት ነው የደወለለት። ሁሉም ነገር ተጠናቅቶ መሆን አለበት። ሙሉ የአንድ ሰዓት ጊዜ ተጠቅመዋል። "ፈጣሪ -ኧ-ኧ-ኧ ሳጥናኤል አንተ መልካም ነገር ለጆሮዬ አሰማኝ" በልቡ አጉተመተመ። ብዙ ሚሊዮን ዶላር ከፊት ለፊቱ ተደቅኖበት ከተደበላለቀው ስሜቱ ጋር ተፋጠጠ። ቶሎ ደውሎ ውጤቱን ማወቅ አለበት። በግብርህ ለመጀመሪያ ጊዜም ቢሆን ሰውን ለማስደሰት ሞክር እባክህ ደግ ነገር አሰማኝ። የተማጸነው ሳጥናኤልን ነበር። ቁጥሩን እየደጋገመ በጥንቃቄ አስተዋለው። እርግጠኛ ነው።

ብሔራዊ ባንክ ለሚሠራው የሥራ ባልደረባው ነው የደወለው።

ከትንሽ ሰኮንዶች በኋላ ስልኩ ተነሳና ድምጽ ከወድያኛው ጫፍ እየተቆራረጠ ወደ ጆሮው መጣ።

"ከዋናው ብሔራዊ ባንክ ጊዜያዊ የጸጥታ ቢሮ..." ንግግሩን ቆም አድርጐ አደመጠ።

የሚጠብቀው ጥሪ ነበር። የሚለውን ለመስማት ጆሮውን ብቻ ሳይሆን ልቡንም ከፈተና አቆበቆበ።

"አዲስ ነገር አለ እንዴ? ዝም አልከኝ እሳ?" አለው።

"ጉዳዩ አብቅቷል" ባጭሩ መለሰለትና በረጅሙ ተነፈሰ።

"ተሳክቷል እያልከኝ ነው..." ልቡ ክፉኛ እየደለቀበት ጠየቀው።

"በታቀደለት መንገድ ተጠናቅቋል።"

የሚጠብቀው ቢሆንም መላ ሰውነቱ ሲረበሽበት ውስጡ ሲናጥ ተሰማው። አደገኛ ውቅያኖስ ውስጥ ለምን እራሱን መወርወር እንደ ፈለገ በርግጠኝነት የተረዳው ዘግይቶ ነው። አፉን የመረረ ወፍራም ምራቅ ሲሞላው ታወቀው። ልግ የተባለው ወፍራም ምራቅ ነበር። በመጸዳጃ ሳህኑ ውስጥ ተፋ። ሁሉም ነገር በፊት እንዳሰበው ቀላል አልነበረም። ከፊት ለፊቱ ከተሰቀለው መስታወት ላይ ለሰከንድ አፍጥጦ የገዛ ምስሉን ተመለከተ። መጣጣ ሪዛም ፊቱ የመከራ ያህል ከብዶ በተቆጣጠረ ሪዙ ተሸፍኖ ሲመለከት ደነገጠ።

ስህተት ሰርተሃል እያለ የሚያስፈራራው እስኪመስለው ድረስ የገዛ ገጹ አሸማቀቀው። በዚህ ሁኔታ ሲመለከተው እራሱን ለራሱ ሳያስጠላው አልቀረም።